# ክፍል ስድስት

## መንግሥቲ ተድላ የተድላ ባይሩ መንግሥት

## (መስከረም 1952 - ሐምሌ 1955)

ገጽ


1. ተድላ ባይሩ የመጀመሪያው የኤርትራ መሪ ........ 360
2. የበዓሉ አከባበር ........ 366
3. ንጉሠ ነገሥቱ መረብን ከፈቱ ........ 370
4. መንግሥቲ ተድላ ........ 372
5. ተድላና ወልደአብ ሁለት ባለጋራዎች ........ 378
6. ኤርትራ የኢትዮጵያ አይደለችም (ወ.ወ.ማ) ........ 382
7. የተከበሩ ስደተኛ ........ 384
8. ድሮ ዳቦ ........ 391
9. ደጃዝማች ፌዴራሊስት ........ 399
10. ያዝልቅልዎ! ........ 405
11. ጫማ በእግር ልክ ካልሆነ ........ 408
12. ፌዴሬሽኑ በሕይወት አለ ወይ? ........ 413
13. ፌዴሬሽኑ ቢፈርስልኝ? (ተድላ ባይሩ) ........ 417
14. ፌዴሬሽኑ ይቀጥል ....... (የጃንሆይ ውሳኔ) ........ 422
15. ብቸኛው ተድላ ........ 437
16. ተድላ ከወልደጊዮርጊስ በኋላ! ........ 440
17. የመሰናበቻው ዋዜማ ........ 441
18. አልቻልኩም! ያውላችሁ ........ 445
19. ወራሽ ማን ነው? ........ 450
20. ደጀጠኒው ደጃዝማች ........ 453



ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የኤርትራን ሕገ መንግሥት ሲያጸድቁ፤

(ነሐሴ 1952)

# ተድላ ባይሩ
# የመጀመሪያው የኤርትራ መሪ

« ...... የኤርትራን ሕገ መንግሥት ለማክበርና ፍጹም በሆነ ታማኝነት ለማገልገል በእግዚአብሔር ስም ቃሌን እሰጣለሁ:: ...... »

ይህ ቃል የተገለጸው የመጀመሪያው የኤርትራ መሪ ሆነው የተመረጡት አቶ ተድላ ባይሩ፣ ካቢኔያቸውን ካቋቋሙ በኋላ፣ መስከረም 13 ቀን 1952 ዓ.ም በአሥመራ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ በተገኙበት፣ በፓርላማው አዳራሽ ሥርዓተ መሀላቸውን ሲፈጽሙ ነው::

ይህች የመስከረም 13ቀን 1952 ዓ.ም ቅዳሜ፣ ለተድላ ባይሩ «የአዲስ ዓለም» መጀመሪያ ዕለት ተብላ ልትሰየም ይገባል ሲሉ አንድ የሀማሴን አዛውንት ተናግረው ነበር ይባላል:: እንደ አውነቱ ከሆነም፣ የአዲስ ዓለም መጀመሪያ የሆነው፣ ለተድላ ባይሩ ብቻ ሳይሆን፣ በሕግ በተመሠረተ አቶኖሚ ባለው መንግሥት እንዲተዳደር ለተደረገው፣ ለኤርትራ ሕዝብ ጭምር ነው ቢባል ስህተት አይሆንም:: ኤርትራ ተብሎ ከስልሣ ዓመት በፊት በኮሎኒያሊስት ጣልያን ለተሰየመውና ከዚያም በፊት « መረብ ምላሽ » ወይም « ብሀረ ሀማሴን » ይባል ለነበረው ሕዝብ፣ ይህን የመሰለ አስተዳደር ሲመሠረትለት በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ መሆኑን የሚክድ የለም:: ያገር ፍቅር ግንባር ዋና ጸሐፊ በመሆን፣ ለኤርትራና ለኢትዮጵያ አንድነት ያደረጉት ተጋድሎና የፈጸሙት ሥራ፣ ተድላ ባይሩን የመጀመሪያው የኤርትራ አስተዳዳሪ እንዲሆኑ ሊያስመርጣቸው ይገባል በማለት፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና መንግሥታቸው ከልብ የሆነ ጥረት አድርገውበታል::

ኤርትራ በፌዴራሲዮን ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል ታህሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት ሲወስን፣ የፍጹም አንድነት ታጋይ የሆኑት አቶ ተድላ ባይሩ፣ የኤርትራ ሕዝብ ጥያቄ ይኸ አልነበረም በማለት ቅሬታቸውን በይፋ የገለጹ ናቸው:: ኋላም ሕገ መንግሥቱ በሚተነባበርበት ጊዜ፣ የኤርትራ አስተዳደር ከኢትዮጵያና ከንጉሠ ነገሥቷ ሥልጣን የተለየ ወይም ያፈነገጠ እንዳይሆን፣ በፓርላማው ላይ ያደረጉት ጥረት የተደበቀ አልነበረም:: በዚህ፣ ተድላ ባሳዩት ቀጥታ የሆነ የኢትዮጵያዊነት አቋም፣ እንኳንስ ተቃዋሚዎቻቸው እንግሊዞቹም ቢሆኑ አልተደሰቱም:: ይህ ሰው፣ በዚህ መንፈሱ የኤርትራን መሪነት ሥልጣን ሲያገኝ፣ <u>ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ፈረስ አቅራቢ ይሆናልና ተጠንቀቁ</u> የሚል ፕሮፓጋንዳ በሰፊው ተነዛ::

ሕገ መንግሥቱ ጸድቆ፣ ለቺፍ ኤግዜኩቲፍነት ምርጫ ሲደረግ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እንደተመኙት ተድላ ባይሩ ብቸኛ ተወዳዳሪ አልነበሩም:: ከዚሁ የተነሳ የምርጫው የመጀመሪያው ዙር ሲከናወን፣ ተድላ ባይሩ 38 ሠላሣ ስምንት፣ አብርሃ ተሰማ 28 (ሀያ ስምንት) የድጋፍ ድምፅ በማግኘታቸው፣ የአንድነቶች እሬቤ፣ ሕጉ የሚጠይቀውን የሁለት ሶስተኛውን ቁጥር ብልጫ ማምጣት ሳይችሉ ቀሩ:: የሁለተኛው ዙር ሲደረግ ግን፣ አንድነቶች ከመቸውም የበለጠ የውስጥ ኃይላቸውን ለማስተባበርና ከተቃዋሚዎቹም ወገኖች አንዳንዶቹን ለመማረክ



ተድላ ባይሩ
የኤርትራ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ

(1952 - 1955)

እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር በ1914 ገደማ በሀማሴን አውራጃ የተወለዱት አቶ ተድላ ባይሩ፣ በጣልያን ኮሎኒያሊስት ዘመን በትምህርት ለመግፋት ዕድል አላገኙም። ለጥቂት ጊዜ ጣልያኖች ወደ ፍሎራንስ የላኳቸው፣ ጠቅላላ ትምህርት ለመቅሰም እንጂ ለአካዳሚ ትምህርት አልነበረም። በሥራ ዓለም ኤክስፔሪያንሳቸው የዳበረው በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህርነትና በአድሚኒስትራሲዮን ነው። ከ1941 ዓ.ም እስከ 1952 ድረስ ለኤርትራና ለኢትዮጵያ አንድነት ያደረጉት ተጋድሎ ከፍ ያለ ዝና ሰጥቷቸዋል። ከመስከረም 12ቀን 1952 እስከ ሐምሌ 29 ቀን 1955 ዓ.ም ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ሆነው ኤርትራን አስተዳድረዋል። ይህን ሥልጣን በፈቃዳቸው ለቅቀው ከወጡ በኋላ፣ በስዊድን የግርማዊነታቸው ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሆነው ተሾመዋል። በመጨረሻም ኢትዮጵያን እስከ ለቀቁበት እስከ 1964 ዓ.ም ድረስ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል ነበሩ።

በመቻላቸው፣ ተድላ ባይሩ በ42 ድምፅ ብልጫ ባለጋራቸውን ደጃዝማች አብርሃ ተሰማን አሸንፈው፣ የቺፍ ኤግዜኩቲፍነቱን ሥልጣን አገኙ።

ግምደሚካኤል ደሣለኝ በኤርትራ የግርማዊነታቸው ላይዘን አፊስር፣ የተድላ ባይሩአሸናፊነት በተረጋገጠ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፣ ለንጉሠ ልዑል ቤተመንግሥት ባስተላለፉት ቴሌግራም፣ «..... ጃንሆይ! ድሉ አሁንም የርስዎ ነው..... » በሚል ቃል መልካሙን ዜና አቀረቡ። ከዚህም አያይዘው፣ ኮንስቲቱሽኑ በሚጠናበት ጊዜ፣ የምክር ቤቱ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው ለኢትዮጵያ መልካም አስተያየት ያሳዩት፡ የቀድሞው ተቃዋሚያችን ሼህ ዓሊ ሙሣ ራዳይ፣ አሁን የፓርላማው ፕሬዚዳንት ሆነው በከፍተኛ ድምፅ መመረጣቸውን ገለጹ። የተድላ ባይሩና የዓሊ ራዳይ መመረጥ ለኢትዮጵያ በጣም ጥሩ በመሆኑ፣ ንጉሠ ነገሥቱ፣ ንጉሣዊው ቤተሰባቸውና ሚኒስትሮቻቸው፣ እጅግ ደስ አላቸው።

አዲሶቹ የሕዝብ ተመራጮች፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ እና የፓርላማው ፕሬዚዳንት፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የፌዴሬሽኑን አክት በፊርማቸው በሚያጸድቁበትና መላው ኢትዮጵያ የአንድነቱን ታላቅ በዓል በሚያከብርበት ዕለት ተካፋይ ለመሆን አዲስ አበባ ሲገቡ፣ ስለሚደረግላቸው አቀባበል፣ የግርማዊነታቸው ልዩ ጽሕፈት ቤት ብዙ ተጨነቀበት። እቶ አክሊሉ ሀብተወልድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እና ምክትላቸው ብላታ ዳዊት እቁበ እግዚእ፣ አውሮፕላን ጣቢያ ሄደው ቢቀበሏቸው የተገባ ይመስለኛል ሲሉ፣ የጃንሆይ ልዩ ፀሐፊ ያቀረቡትን ሀሳብ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ሳያምኑቱ፣ ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስንም ሳይጠይቁ፣ በቀጥታ በዚሁ ይፈጸም አሉ። ወዲያውኑ በዚያን ጊዜ ሲሣይ ለውጤ የተባለው ረዳት ልዩ ጸሐፊ፣ አቶ ተፈራወርቅ ኪዳነወልድን ይቀድምና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ስልክ ደውሎ « ..... ከብላታ ዳዊት እቁበ እግዚእ ጋር ሆናችሁ መስከረም 10 ቀን 1952 አውሮፕላን ጣቢያ ተገኝታችሁ፣ አቶ ተድላ ባይሩንና ሼክ ዓሊ ራዳይን እንድትቀበሉ ከጌቶቹ መታዘዙን አስታውቃለሁ ... » ይላቸዋል። አቶ አክሊሉ በስውየው አነጋገር ይበሳጩና፣ « ..... የኤርትራን ቺፍ እግዜኩቲፍ እንደ ውጭ አገር የክብር እንግዳ፣ የንጉሠ ነገሥቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አውሮፕላን ጣቢያ ሄዶ አይቀበልም። ለነ ተድላ የተለየ አቀባበል ሊደረግላቸው ያስፈልጋል ከተባለ፣ ተገቢውን ተቀባይና አውቶሞቢል መመደብ ያለበት የግቢ ሚኒስቴር ነው። ..... » ብለው ስልኩን ይዘጉበታል።

ይህ ያቶ አክሊሉ የእልህ አነጋገር ከጃንሆይ ጆሮ የደረሰው፣ የበለጠ ተጨማምሮና ተቀምሞ፣ ትእዛዝ አልቀበልም ባይ መስሎ ስለሆነ፣ ንጉሠ ነገሥቱ በጣም ተቆጥተው አክሊሉን ጥሩት ይላሉ። በዳቦ ላይ ሙልሙል እንደሚባለው፣ አቶ አክሊሉ ተፈልገው ሳይገኙ ይቀራሉ። ይኸው የፍሙ አራጋቢ የሆነው ረዳት ልዩ ፀሐፊ፣ እንደገና ወደ ጃንሆይ ይሄድና፣
« ...... ሚኒስትሩ ከቢሮአቸው የሉም። ዋና ለመዋኘት ወደ ቢሾፍቱ ሳይሄዱ አልቀሩም። የሚመለሱትም ለበዓሉ ፕሮግራም ለመገኘት ነው እንጂ፣ ከዚያ በፊት አይደለም ይባላል ..... » የሚል፣ የበለጠ የሚያናድድ ዜና ያቀርብላቸዋል።

ጃንሆይ በቁጣ የጽሕፈት ሚኒስትራቸውን ያስጠራሉ። ለተድላ ባይሩ እንደ ውጭ አገር እንግዳ የተለየ አቀባበል ሊደረግለት አይገባም ብለው፣ አቶ አክሊሉ የተናገሩት ትክክለኛ አስተያየት መሆኑን ለማሳመን፣ ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ከጃንሆይ ጋር በብዙ ይከራከራሉ። ከዚያም አያይዘው የኤርትራ በዓል አከባበር፣



ቢትወደድ አንዳርጋቸው መሳይ በኤርትራ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ
የመጀመሪያው እንደራሴ፤

(1952 - 1959)

ፕሮግራሙ አምስት ሙሉ ቀናት ስለሚፈጅና አቶ አክሊሉም 1ኛ/ የፌዴራሉን አክት ግርማዊነትዎ በአፌሴል እንዲፈርም አስፈላጊውን ንግግር በማሰናዳት፣ 2ኛ/ ከዓለም የመንግሥታት መሪዎች ለግርማዊነትዎ የሚጐርፉትን የደስታ መግለጫዎች በመቀበልና ወዲያውኑ መልስ በመስጠት፣ 3ኛ/ በተለይ ከተባበሩት መንግሥታት የተላኩትን ከፍተኛ መልዕክተኞችና ኤርትራን ሲያስተዳድሩ የቆዩትን የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች አነጋገር በማሰናዳት፣ 4ኛ/ ለኢትዮጵያ የተወከሉ የውጭ አገር መንግሥታት አምባሳደሮችንና ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትሮችን አንድ በአንድ እየተቀበሉ በማነጋገር፣ ፋታ የማይሰጡ ሥራዎች ተደራርበው ስለሚጠብቁች፣ ለ24 ሰዓት ቢሾፍቱ ንፋስ ተቀብሎ እንዲመጣ፣ ጃንሆይን ሳላማክር፣ ጃንሆይ ፈቅደዋል ብዬ የገፋፋሁት እኔ ስለሆንኩ፣ ጥፋት ከሆነ እኔ እቀበላለሁ አሉ።

ቀዳማዊ ኃይሥላሴ ምንም እንኳን ወልደጊዮርጊስ እንዳሰረዱት፣ የአክሊሉ አስተያየት ትክክል መሆኑን ቢገነዘቡም፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው ቤተመንግሥት መጥተው ሀሳባቸውን በቀጥታ ለጃንሆይ ሳያስረዱ በመቅረታቸውና፣ ከዚያም አልፎ ጃንሆይን ሳይጠይቁ፣ በጽሕፈት ሚኒስትሩ ፈቃድ፣ ቢሮአቸውን ትተው ወደ ቢሾፍቱ በመሄዳቸው የተሰማቸውን ቅሬታ ሊሰርዙት አልቻሉም።

ለታላቁ በዓል፣ ንጉሠ ነገሥቱ ለመላው ሕዝቦቸውና ለዓለም የሚያሰሙት ንግግር፣ የመጨረሻው አርማት ተጠናቅቆ፣ በቁም ጽሑፍ ተገልብጦ ሲደርሳቸው፣ አንድ ዐረፍተ ነገር እንዲታረም፣ በቀይ እርሳስ አሻሽለው ምልክት አደረጉበት። ይኸውም፣ « ..... የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችን አክሊሉ ሀብተወልድ፣ የጣልንበትን አደራ እና የሰጠነውን ትእዛዝ በሚገባ ተከትሎ፣ የኤርትራን ጉዳይ ለስባት ዓመታት በዓለም ጉባኤ ፊት በሰፊው ተከራክረበት ...... » የሚለው ዓረፍተ ነገር ተሰርዞ፣ « ..... <u>የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችን ወደ ጉባኤው እየተመላለሰ ለትክክለኛው ፍርድ ያለንን ጥያቄ በእኛ ስም እንዲያቀርብ አዘዝን</u> ..... » በሚል ቃል እንዲለወጥ የጃንሆይ ውሳኔ ሆነ።

አክሊሉ ሀብተወልድ በኤርትራ ጉዳይ የፈጸሙት አገልግሎት፣ በታላቁ ዲስኩራቸው ውስጥ እንዲጠቀስ፣ በዝግጅቱ ጊዜ ትእዛዝ የሰጡት ራሳቸው ጃንሆይ ቢሆኑም፣ ካንዴም ሁለቴ በቀረበላቸው ረቂቅ ላይ «...... የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችን ለሰባት ዓመታት በዓለም ጉባኤ ፊት በሰፊው ተከራክረበት .... » የምትለዋን ቃል ሳያርሟት ያሳለፏት ቅር እያላቸው መሆኑ አይጠረጠርም። ነገር ግን በበዓሉ ዋዜማ ማታ፣ የመጨረሻው ዝግጅት ተጠናቅቆ ሲቀርብላቸው፣ በአክሊሉ ላይ የተበሳጩበት ጊዜ ስለሆነ፣ ያችን የማይወዷትን አቀራረብ ለማጻከምና ለመለወጥ አመቻቸው።

አቶ አክሊሉ ከዚያ ከረዳት ልዩ ጸሐፊ ጋር በረዥሙ ከመነጋገር ይልቅ ሀሳባቸውን በቀጥታ ለጃንሆይ ቢገልጹ ኖሮ፣ ቀጥሎም ሳያስፈቅዱ ለመዝናናት ወደ ቢሾፍቱ ከመሄድ ቢታገሡ ኖሮ፣ የኤርትራን ጉዳይ ለሰባት ዓመታት በዓለም ጉባኤ ፊት በሰፊው መከራከራቸውን ንጉሠ ነገሥቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያስረዱላቸው ነበር። ሆኖም በልማድ እንደሚታወቀው ይህን የመሰለ ከፍተኛ ዲስኩር ሲደረግ፣ ማናቸውንም ጉዳይ ንጉሠ ነገሥቱ መሥራታቸውን እንጂ፣ ከሚኒስትሮቻቸው መካከል ስም እየተጠራ ገብረማርያም ይህን አደረገ፣ ወልደማርያም ይህን ፈጸመ፣ እየተባለ አይነገርም። በኤርትራ ጉዳይ ግን ንጉሠ ነገሥቱ ባደረጉት ታሪካዊ



ሼህ ዓሊ መሐመድ ሙሳ ራዳይ
የኤርትራ ፓርለማ ፕሬዚዳንት

(1952 - 1955)

እጅግ የታወቁት የኤርትራ ምዕራባዊ ቆላ ተወላጅ፣ ሼህ ዓሊ ሙሣ ራዳይ በ1952 ዓ.ም ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ስትቀላቀል ዕድሜያቸው አርባ ዓመት እንዳልደረሰ ይነገራል።

ዓሊ ራዳይ በትግሉ ዘመን የኢትዮጵያንና የኤርትራን አንድነት ይቃወሙ እንደነበረ የታወቀ ነው። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴራሲዮን እንድትቀላቀል ከወሰነ በኋላ ተቃዋሚነታቸውን አቋርጠው ኢትዮጵያዊነታቸውን አምነውበታል። ጃንሆይ የኤርትራን ፓርለማ ሲጐበኙ፣ ፕሬዚዳንት ዓሊ ራዳይ የተቀበሏቸው « ...... ከሞት ወደ ሕይወት የተሻገረው የኤርትራ ሕዝብ፣ ለዚህ ዕድል የበቃው በታላቁ መሪነትዎ ነው ...... » በሚል ቃል ነው።

ዲስኩር ውስጥ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችን ወደ ጉባኤው እየተመላለሰ በእኛ ስም እንዲሠራ አደረግን ብለው መናገራቸው፣ በዘመነ መንግሥታቸው ለማንም ያላደረጉት ስለሆነ፤ በዚህ ረገድ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ የተለየ ዕድል አግኝተዋል ለማለት ይቻላል::

# የበዓሉ አከባበር


ሐሙስ መስከረም 11 ቀን 1952 ዓ.ም (በኢ.ት.አቆ.መስከረም 1ቀን 1945) የኤርትራን የፌዴራል አክት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በፊርማቸው ሲያጸድቁ፣ አዲስ አበባ በዳግማዊ ምኒልክ ቤተመንግሥት የተደረገው በዓል፣ በስፋቱም ሆነ በድምቀቱ ከዚህ ቀደም ታይቶ የማይታወቅ ነበር::

አዲሱ የኤርትራ መሪ አቶ ተድላ ባይሩ፣ በሕይወታቸው ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ በሞርኒግ ኮት ልብስ ደምቀው፣ « ክቡር » ተብለው፣ ከሚኒስትሮቹና ከመኳንንቶቹ የተለየ የፕሮቶኮል ቦታ ተሰጣቸው:: እንደዚሁም የፓርላማው ፕሬዚዳንት ሆነው የተመረጡት ክቡር ሼህ ዓሊ ሙሣ ራዳይ፣ በነጭ ደበላ ጥምጥማቸውን አሳምረው፣ ከቺፍ ኤግዜኩቲፉ ቀጥሎ ሥፍራቸውን ያዙ:: ከንጉሠ ነገሥቱና ከእቴጌይቱ ጀምሮ ንጉሣዊው ቤተሰብ በሙሉ፣ መሣፍንቱና መኳንንቱ፣ ሚኒስትሮቹና የጦር አለቆቹ፣ የውጭ አገር መንግሥታት እንደራሴዎችና የተባበሩት መንግሥታት ባለሥልጣኖች በተገኙበት፣ በምኒልክ አዳራሽ ውስጥ ሥነ በዓሉ ሲከናወን፣ የጃንሆይ ፕሮቶኮል ለተድላ ባይሩና ለዓሊ ራዳይ የሚያደርግላቸው መንከባከብ ከዚህ ቀደም ተደርጎ የማይታወቅ ነው ተባለ:: ባጭሩ፣ ተድላ ባይሩ የተሰጣቸው የፕሮቶኮል ደረጃ ሲታይ፣ ለመላዋ ኢትዮጵያ ሥልጣን የተጐናጸፉ እንጂ፣ ለአንዲቷ የኢትዮጵያ አካል ለሆነችው ለኤርትራ ግዛት ብቻ የተመረጡ አይመስሉም ነበር::

በሻምፓኙ ግብዣ ላይ፣ ተድላ ባይሩ እና ዓሊ ራዳይ ተራ በተራ እየተጠሩ ከጃንሆይ ጋር ለመነጋገር ሲቀርቡ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የሚያደርጉላቸው ፈገግታ፣ ንጉሣዊው ቤተሰብና መሣፍንቱ የሚያሳዩዋቸው የደስታ ገጽታ፣ ከዚህ ቀደም ለማንም ያልተደረገ በመሆኑ ያልተገረመ አልነበረም:: በተለይ የምዕራባዊው ቆላ ሕዝብ ተጠሪ ሼህ ዓሊ ራዳይ፣ ይህን ሁሉ የተሰጣቸውን ክብርና ወግ ሲያዩ፣ በዚያ በትግሉ ዘመን ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀል የለባትም በማለት፣ ሲቃወሙ መኖራቸው፣ ትክክል አልነበረም ብለው ራሳቸውን ሳይወቅሱ አልቀሩም:: ከብዙ ዓመታት በኋላ ቢትወደድ አስፍሐ የዘመኑን ታሪክ ሲያስታውሱ፣ « ..... የቆላ ሰዎች አንድ ጊዜ ካመኑ አይክዱም:: በዚያ በዳግማዊ ምኒልክ አዳራሽ በተከናወነው የኤርትራና የኢትዮጵያ መቀላቀል ክብረ በዓል ላይ፣ ሼህ ዓሊ ራዳይ የተሰማቸውን ፍጹም ኢትዮጵያዊነት እስከ መጨረሻው ጠብቀው የኖሩ ናቸው .. » ብለዋል::

ለዚህ ታላቅ በዓል በተዘጋጀው ስፌ በሆነው ፕሮግራም መሠረት፣

1.--- ንጉሠ ነገሥቱ፣ ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ፣ በዘመነ መንግሥታቸው ያደረጉትን ድካም ለሕዝባቸውና ለመላው ዓለም ለማስማት፣



አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣

*« …… የፌዴራሉን አዋጅ የሚያጸድቀው ፍሉፍና እንዲሁም የኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን መቀላቀል የሚገልጠው አዋጅ የግርማዊነትዎን መልካም ፈቃድና ፊርማ ይጠብቃል …… »*

2.— ጸሐፊ ትእዛዙ፣ የኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀል የሚያበስረውን አዋጅ ለሕዝብ ለማስታወቅ፣

3.— የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ፣ የፌዴራሉን አክት ንጉሠ ነገሥቱ በፊርማቸው እንዲያጸድቁት በኦፊሴል ለመጠየቅ፣

4.— የኮር ዲፕሎማቲኮች ተቀዳሚ የውጭ አገር መንግሥታቶችን የደስታ መግለጫ ለማቅረብ፣ ~

5.— የኤርትራ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ፣ ዛሬ ኢትዮጵያንታቸው የተመለሰላቸውን የመረብ ምላሽ ሕዝቦች ስሜት ለመግለጽ፣ልዩ ልዩ ዲስኩሮች ተደርገዋል።

ከነዚህ ሁሉ ዲስኩሮች ውስጥ፣ ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌይቱ በተጠንቀቅ በቆሙበት በዚያ በደመቀ ሥነ ሥርዓት ላይ፣ ስሜትኛ ሁኔታ የተደመጠው፣ የተድላ ባይሩ ንግግር ነበር። « ..... የስልሣ ስድሳን ዓመት ትግል ፈጽመን፣ ይኸው ዛሬ ፍሬውን ስናይ፣ ኤርትራ እንደገና ተፈጠረች። ወይም ተወለደች። ብሎ የሚያሳምን ሆኗል ..... » በማለት አዲሱ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ የኤርትራን ሕዝብ ስሜት ገለጡ። ንጉሠ ነገሥቱም ሲመልሱ፣ ሕገ መንግሥቱ በሚመከርበት ጊዜ፣ ተድላ ባይሩ የሕዝብ እንደራሴዎቹ ፕሬዚዳንት ሆነው ያሳዩትን የመሪነት ችሎታና ቅን አስተያየት ካደነቁ በኋላ፣ « .... አሁንም የኤርትራ ዋና አስተዳዳሪ በመሆን ያለበትን ኃላፊነት በታላቅ ችሎታው እንደሚፈጽም እናምናለን .... » አሉ። ይህ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት አንደበት ለተድላ ባይሩ የተሰጠው « ታላቅ የመሪነት ችሎታ » ግምት፣ እስከመቼ ድረስ እየታመነበት እንደሚቀጥል ወደፊት እናያለን።

በዚህ በዓል ላይ ተካፋይ የሆነው የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር አንሴ ማቲየንሶ፣ (ANZE MATIENZO) ለተድላ ባይሩ የተሰጠው ፕሮቶኮል በጣም ከፍ ያለ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው ? ሲል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ጠየቃቸው። አቶ አክሊሉም ሲመልሱለት፣ « የቤተ መንግሥቱ ፕሮቶኮል ያከበረው የተባበሩት መንግሥታትንና አንተ የደከምክበትን ሕገ መንግሥት ነው እንጂ፣ አዲሱን ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ከሌሎቹ ሚኒስትሮች የተለየ ለማድረግ ታስቦ አይደለም » አሉት። እንደዚሁም በበዓሉ ላይ ከተገኙት መኳንንት፣ አንዱ ወደ ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ጠጋ ብለው፣ « ..... ከሚገባ በላይ፣ ትግሬን ሲያቃብጡት የበለጠ አሸሹት..... » እንደተባለው፣ ለዚህ ሀማሴን የሚደረግለት ሽር ጉድ አልበዛም ወይ ? ወደፊትስ እንደዚህ መቀጠል ይቻላል ወይ ? ብዬ ስጋቻለሁ አሏቸው። እንደተለመደው ወልደጊዮርጊስ ለመልሱ ጊዜ አልፈጁም። « ...... እኛ ቤት እኮ፣ ስንወድ መሸከሙን፣ ስንጠላ ማውረዱን፣ በሚገባ ስለምናውቅበት የዛሬው አይከብደንም፣ የነገውም አያስጨንቀንም ..... » አሉ ይባላል።

ከሐሙስ መስከረም 11 ቀን እስከ ሰኞ መስከረም 15 ቀን 1952 ዓ.ም ድረስ፣ ለአምስት ቀናት ስለ ኤርትራ መቀላቀል በመላ ኢትዮጵያ የተደረገው በዓል ወደር አልነበረውም። በንጉሠ ነገሥቱ ቤተመንግሥት እና በተለይም በኢትዮጵያ ሕዝብ ያገር ፍቅር ማህበር የተደረጉት ግብዣዎችና የደስታ መግለጫዎች ከዚህ ቀደም ያልታዩ ናቸው።



ንጉሠ ነገሥቱ የኤርትራን ፌዴራል አክት ሲያጸድቁ፣

*« ...... ዛሬ በወንድማማችነት የተቀላቀላችሁ ታማኞቻችን እናንተ የኢትዮጵያና የኤርትራ ተወላጆች ዜጎቻችን፥ እኛ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነታችን፣ የኤርትራንና የኢትዮጵያን በፌዴራሲዮን መቀላቀል ዛሬ ለታማኝ ዜጎቻችን የምንገልጽበት ጊዜ ታሪካዊ የሆነ ሰዓት ነው። ...... ይህን ቀን አባቶቻችንና አባቶቻችሁ ለማየት ተመኙ፥ አልቻሉም። ለመስማትም ለመኙ አልሆነላቸውም። እኛና እናንተ ግን፥ ለማየትም ልንደርስበትም ስለቻልን ታላቅ ዕድል አገኘን ...... »*

(ቀ.ኃ.ሥ መስከረም 11 ቀን 1952 ዓ.ም)

አዲሲቷ ሬፑብሊክ ከተባለችው ከጣልያን በስተቀር፣ የዓለም መንግሥታት መሪዎችና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች፣ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እና ላቶ አክሊሉ ሀብተወልድ በላኳቸው የደስታ መግለጫ መልዕክቶች፣ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ሕዝብ ደህንነት መልካም አስተያየታቸውንና ስሜታቸውን ገልጸዋል:: በዚያን ጊዜ ምንም እንኳ በጣልያንና በኢትዮጵያ መካከል ዕርቅ ተመሥርቶ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት የተዘረጋ ቢሆንም፣ የሮማ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ የሚፈጽመውን ከፍተኛ ተንኮል አላቆመም:: በዋሽንግቶን ያለው የጣልያን አምባሳደር አልቤርቶ ታርኪያኒ፣ የአሜሪካ ፕሬዚዳንትና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ፣ ለንጉሠ ነገሥቱና ላቶ አክሊሉ የደስታ መግለጫ መልዕክት እንዳያስተላልፉ ለማገድ ልዩ ጥረት አድርጉ እንደነበረ የፈረንሣይ አምባሳደር ለአገሩ በላከው ልዩ ራፖር ገልጾታል:: ነገር ግን ፕሬዚዳንት ትሩማንና የዲፕሎማሲው መሪ ዲን አቼሰን፣ የሮማን መንግሥት ፍላጐት አልተከተሉም:: ለንጉሠ ነገሥቱና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በላኩት ቴሌግራም፣ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በመቀላቀሏ የተሰማቸውን ደስታና መልካም ምኞታቸውን ገልጠዋል::

## ንጉሠ ነገሥቱ መረብን ከፉቱ

የኤርትራንና የኢትዮጵያን ግዛት ለመለየት በጣልያን የተከለለውን የመረብን ወሰን ሰርዘው፣ ወደ ኤርትራ ከመሻገራቸው በፊት፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለመጀመሪያ ጊዜ አክሱምን ተሳለሙ::

« ..... ሀገረ ሙላድዎና ብሔረ ነገድዎ የሆነውን አክሱምን፣ ለመሳለም እንኳን አበቃዎ ..... » በሚል የቡራኬ ቃል ንቡረዕድ ገብረመስቀል ተቀበሏቸው:: የአክሱም ንቡረዕድ ባደረጉት ንግግር፣ መሠረታዊውን የኢትዮጵያን ታሪክ ባጭሩ አበጥረው የሚያስረዱ ቃላቶች ስለአሉበት፣ ዋና ዋናዎቹን መመልከት ጠቃሚ ይሆናል::

« .... አክሱም፣ የእናትዎ የማክዳ፣ የአባትዎ የምኒልክ፣ የመንግሥታቸው መንበር ብቻ ሳትሆን የትውልድ አገራቸውም ናት:: ....... አክሱሞች መንግሥታቸውን ለማስፋፋት በዚያን ዘመን ሸዋን ሁለተኛ የሁሉን መንበራቸው አድርገውታል:: ከዚህም የተነሣ፣ አብርሃ በትግሬ፣ አጽብሃ በሸዋ ሆነው፣ መንግሥታቸውን ሲያስከብሩ ኖረዋል:: ...... በአፄ ድልነዓድ ዘመነ መንግሥት፣ ጉዲት (ዮዲት) የቀዳማዊ ምኒልክን ዘር ለማጥፋት በጠላትነት ተነሥታ፣ ብዙ ደም ስታፈስና የታሪክ ምስክር የሆኑትን ቅርሶች ሁሉ ስታጠፋ፣ አፄ ድልነዓድ ሕይወታቸው ለመዳን የቻለው ከትግሬ ተነስተው፣ ወደ ጥንት አገራቸው ወደ ሸዋ ሄደው በመስፈር ነው:: ..... ቀጥሎም የድልነዓድ ልጅ አፄ አንበሳ አውድም፣ ከሸዋ ወደ ትግሬ ተመልሶ ጉዲት ያቃጠለቻቸውን ቤተክርስቲያኖችና የታሪክ ቅርሶች እንደገና ለመሥራትና ለማደስ ችሏል:: ...... ግራኝ መሐመድም አክሱምን ባቃጠለ ጊዜ፣ አፄ ፋሲል ከጐንደር መጥተው የጥንት አገራቸውን የአክሱምን አብያተ ክርስቲያናት እንደገና ለመሥራትና ለማደስ በቅተዋል::

...... ይህን ሁሉ ታሪክ ለመናገር ያነሳሳኝ፣ አክሱምና ሸዋ ከጥንት ጀምረው የኢትዮጵያ ነገሥታቶች መዲና መሆናቸውን ማስታወስ ተገቢ ስለሆነ ነው:: ...... የቅርቦቹ ዘመን አባቶችም፣ አፄ ዮሐንስና አፄ ምኒልክ በሥጋ ቢሞቱም፣ በነፍስ

ሕያዋን ስለሆኑ፣ ደማቸውን አፍስሰው ከጠላት እጅ ያላዳኗትን ኤርትራን ዛሬ እርስዎ ልጃቸው፣ አቀድሞ ታሪኳና እቦታዋ መመለስዎን መለኮት ሲያሰማቸው፣ ምን ያህል ይደንቃቸው ይሆን ? ከእነሱ ዕድል የበለጠ ለርስዎ የተሰጠው ዕድል እንደምን ያስገርማቸው ይሆን? ..... ነቢዩ መንገድህን የሚጠርግ መልዕክ፣ በፊትህ እልክልሃለሁ እንዳለው፣ ንጉሠ ምድር ሆነው የኖሩት ንጉሠ ነገሥት፣ ዛሬ ንጉሠ ባሕርም ለመሆን ገጽዎን ወደ ምፅዋ ስለመለሱ፣ እግዚአብሔር ጉዞዎን እንዲባርክልዎ እንለምነዋለን:: .... »

ንቡረዕድ ገብረመስቀል ያዘጋጁት የደመቀ አቀባበልና የተናገሩት ውበት ያለው ታሪክ፣ እጅግ የሚደነቅ ቢሆንም፣ ለኤርትራ አፄ ዮሐንስና አፄ ምኒልክ ደማቸውን አፍስሰው ያልሆኑላቸውን እርስዎ በዕድል አገኟት የሚል ትርጉም የሚሰጠው ንግግር፣ ንጉሠ ነገሥቱን አላስደሰተም:: ...... አፄ ዮሐንስ ኤርትራን ከጣልያን ለማዳን ያቀዱትን ውጊያ ሳይፈጽሙ ሞቱ:: አፄ ምኒልክ ደግሞ በኃይል የተወሰደችውን ኤርትራን ለማስመለስ አልሞከሩም:: ታሪክን እቦታው ለመመለስ ለብዙ ዓመታት የፖለቲካ ጦርነት ያደረግኩት እኔ ብቻ ነኝ፣ ብለው አባ ጠቅል ስለሚያምኑ፣ ንብረዕዱ የጠቀሱት ከታሪኩ ውጭ ሆኖ አግኝተውታል:: ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በልማዳቸው በዙፋናቸው ፊት ለሚደረግ ዲስኩር ሁሉ መልስ ሳይሰጡ አያልፉም:: ለንቡረዕድ ገብረመስቀል ታሪካዊ ንግግር መልስ ሳይሰጡ፣ ለአክሱም መተዳደሪያ ሠላሣ ጋሻ መሬት ሰጦታ አበርክተው በዝምታ መመለሳቸው፣ ቅሬታ ስለተሰማቸው ነው ተብሎ ታምኖበታል::

ጥቅምት 4 ቀን 1952 ዓ.ም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በመረብ ድልድይ ላይ የተዘረጋውን ጥብጣብ በወርቅ መቀስ ቆርጠው ለው ለራሹን ወሰን ሲደመስሱ፣ « ... ለብዙ ዓመታት የሁለቱን ወንድማማች ሕዝቦች የለየውን የመከራ ምዕራፍ በዛሬው ቀን ለዘለዓለሙ እንዘጋለን ...... » አሉ:: አባ ጠቅል ይህችን ቃል ከተናገሩ ከአርባ ዓመታት በኋላ፣ መረብ ተመ[illegible]ሶ የኢትዮጵያና የኤርትራ ወሰን መሆንዋን፣ እንደ ንቡረዕድ ገብረመስቀል አስተሳሰብ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በሥጋ ቢሞቱም፣ ነፍሳቸው ሕያው ስለሆነ መለኮት ሲነግራቸው፣ ምን ብለው ይሆን ? የሚል ጥያቄ ያስቀርባል::

ጃንሆይ መረብን ተሻግረው የኤርትራን መሬት በጫማቸው ሲረግጡ፣ በመረብ ምላሽ ሕዝብ ስም ሆነው ለመቀበል የተገኙት ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ተድላ ባይሩ፣ በድንገተኛ አፐንዲክስ (APPENDIX) ሕመም ይሰቃዩ ነበር:: ይሁን እንጂ ይህ መረብ ላይ የተዘጋጀው በዓል በታሪክ ላይ ከፍተኛ ቦታ ያለው ነው በማለት፣ አቶ ተድላ ሕመሙ እያሰቃያቸው ፕሮግራሙን ለመፈጸም ጠነከሩ::

ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ለንጉሠ ነገሥቱ የክብር አቀባበል ያደረጉት፣ « ..... ባለፈው የባርነትና የመከራ ዘመን፣ ደተሰጠው ክፉ ስም ተፍቆለት፣ የአዲስ ሕይወት መክፈቻ ለመሆን በታደለው በዚህ ታሪካዊ ስፍራ ተገኝቼ፣ በታማኝ ዜጐችዎ በኤርትራውያኖች ስም ሆኜ፣ እንኳን ደህና መጡልን እላለሁ:: ...... » በሚል ቃል ነበር:: አቶ ተድላ በንግግራቸው መጨረሻ ላይ፣ « ..... ወሰን በሌለው የአባትነት ቸርነትዎ እያጽናኑን፣ ተወዳዳሪ በሌለው ዕውቀትዎ እየመሩን፣ ለዚህ ታላቅ ክብር ስለአደረሱን፣ ለዛሬውና ለመጭው ትውልዳችን ግርማዊነትዎ የጣለብንን ውለታ ለዘለዓለሙ አንረሳውም .... » አሉ:: ጃንሆይም ለተድላ ሲመልሱ፣ ለሁለቱ ወንድማማች ለሆኑት ሕዝቦቻችን የከፈትነው ነፃ መገናኛ፣

ዘለዓለማዊ የተቀደሰና ምንጊዜም የማይደመሰስ መሆኑን ለመላው ዓለም ገልጠ የሚያሳይ ነው ብለዋል::

መረብ ተከፍቶ ንጉሣዊው ጉዞ ወደ አሥመራ ሲያመራ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ተድላ በተዘጋጀላቸው ልዩ ሔሊኮፕተር፣ « ራዲዮ ማሪና » (ኋላ ቃኘው ስቴሽን) በተባለው የአሜሪካኖች ኮሙኒኬሽን ሴንተር ከሚገኘው ክሊኒክ ተወስደው፣ ዘአስቸኳይ ኦፕራሲዮን ተደረገ:: ንጉሠ ነገሥቱም ሳይውሉ ሳያድሩ በዚያኑ ዕለት ከተኙበት ክሊኒክ ሄደው ሲጠይቋቸው፣ ለሕመምተኛው ትልቅ ሞራልና ደስታ ሆነ::

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በታላቅ አጀብ ከመረብ ተነስተው አሥመራ እስኪደርሱ፣ እጅግ የጋለ አቀባበል ያደረገላቸው ሕዝብ፣ ከብዛቱ የተነሣ ቁጥሩ ምን ያህል እንደሆነ ትክክለኛ ግምት መስጠት አልተቻለም:: ከቤተመንግሥቱ ሰገነት ላይ ሆነው፣ « .... ከአፄ ዮሐንስ ወዲህ፣ ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ከፍተኛ ገዢያችሁ፣ የኤርትራና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆነን፣ በኤርትራ መሬት ላይ እንገኛለን .... » የሚለውን ንጉሣዊ ቃል በድምፅ ማጉሊያ ባሰሙት ጊዜ፣ ያ ሰፍር ቁጥር የሌለው ሕዝብ የደስታ መግለጫ ጭብጨባውንና እልልታውን ያለማቋረጥ ስለቀጠለ፣ ጃንሆይ የጀመሩትን ዲስኩር መፈጸም ሳይችሉ ቀሩ:: በሰፊው የተዘጋጀው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዲስኩር ዋና ግቡ፣ የኤርትራን ኢትዮጵያነት መሠረታዊ ታሪክ ለሕዝቡ ለማስረዳትና፣ በንጉሠ ነገሥትነት ዘመናቸውም፣ ይህን ጥንት ምድረ ሀማሴን፣ ዛሬ ኤርትራ እየተባለ የሚጠራውን ሕዝብ፣ ወደ እናት አገሩ ለማስመለስ ያደረጉት ጥረት እንዲታወቅ ለማድረግ ነበር::

ጃንሆይ ኤርትራን ለመጀመሪያ ጊዜ በኦፊሴል በመጐብኘት ለሀያ አምስት ቀናት በቆዩበት ሰሞን፣ በየአውራጃውና በየከተማው ሲዘዋወሩ በብዛት የተደረጉት ዲስኩሮች ሁሉ፣ ይህንኑ የሁለቱን ሕዝቦች የአንድነት ታሪክ በየመልኩ የሚያወሱ በመሆናቸው፣ ጥቅምት 4 ቀን 1952 ዓ.ም ከሕዝቡ የደስታ መግለጫ ብዛት የተቋረጠው ንጉሣዊ መልዕክት በትክክል ደርሶላቸዋል::

## መንግሥቲ ተድላ

የኤርትራ ሕገ መንግሥት በተዘጋጀበት ጊዜ፣በእንግሊዘኛ" GOVERNMENT OF ERITREA" የሚለው ቃል ወደ ትግርኛ ሲተረጐም «መንግሥቲ ኤርትራ» ተብሎ ነው:: ኤርትራውያኖች በተድላ ባይሩ አስተዳደር ዘመን፣ ተቃውሞአቸውን ወይም ድጋፋቸውን በሚገልጡበት ጊዜ «መንግሥቲ ተድላ» እያሉ እንደነበር ይታወሳል::

ተድላ ባይሩ፣ መስከረም 13 ቀን 1952 ዓ.ም፣ ካቢኔያቸውን አቋቁመው መሀላቸውን ከፈጸሙ በኋላ፣ የመንግሥቲ ተድላን ተግባር በቀጥታ ከመጀመራቸው በፊት፣ ለስድስት ሣምንታት በሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ተይዘው ነበር:: ይኸውም፣ የመጀመሪያው ሁለት ሳምንት ተኩል፣ የኤርትራና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የሆኑት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ለሚያደርጉት ታሪካዊ ጉብኝት አስፈላጊዎቹን ፕሮግራሞች በማዘጋጀት፣ ቀጥሎ ደግሞ ለሶስት ሳምንት ተኩል ንጉሠ ነገሥቱ በመላ ኤርትራ በሚዘዋወሩበት ጊዜ፣ ከእሳቸው ሳይለዩ ፕሮግራሞቻቸውን



ንጉሠ ነገሥቱ አሥመራ ሲገቡ

*« ....... ከአጼ ዮሐንስ ዘመን ወዲህ ገና ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ንጉሠ ነገሥታችሁና ከፍተኛ ገዥያችሁ፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ንጉሠ ነገሥት በመሆናችን በኤርትራ መሬት ላይ እንገኛለን። ....... »*

(ቀ.ኃ.ሥ ጥቅምት 1952)

በማስፈጸም፣ ፋታ የማይሰጡ ሥራዎች አጋጥሟቸው ነበር። በነዚህ ምክንያቶች ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ተድላ፣ አዲሱን የኤርትራ አስተዳደር ማህደር ከፍተው ሥራቸውን የጀመሩት፣ ከተሾሙ ከአንድ ወር ተኩል በኋላ ነው።

በመጀመሪያዎቹ ወራቶች ተድላ ባይሩ ያሳዩት እንቅስቃሴ፣ የወገኖቻቸውን የአንድነት ፓርቲ አባሎችን ምክር ለመከተልና ከፍተኛ አስተያየት ያሳደሩባቸውን የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ልባዊ ምኞት ለማስፈጸም ቆርጠው የተነሱ መስለው ነው። የኤርትራው መሪ በጃንሆይ ብቻ ሳይሆን፣ በትልቁ ባለሥልጣን በወልደጊዮርጊስም እጅግ የተደገፉ በመሆናቸው፣ ከአዲስ አበባ የሚፈልጉትን ሁሉ እንደልብ ከማግኘት በስተቀር፣ እንቅፋት እንዳይገጥማቸው አርግጠኛ ሆኑ። ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስም ከቢትወደድ አንዳርጋቸው መሣይ ጋር ስለማይጣጣሙ፣ በኤርትራ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ፤ በቺፍ ኤግዜኩቲፉ ሥራ ውስጥ እየገቡ እንዳያስቸግሩ፣ እኔ አለሁልህ በማለት የተድላን ሞራልና ተስፋ አዳብረዋል። በመሠረቱ ጸሐፊ ትእዛዝ አውነት አላቸው። በሕገ መንግሥቱ እንደተገለጸው የግርማዊነታቸው እንደራሴ፣ በቺፍ ኤግዜኩቲፉ የሥልጣን ክልል ውስጥ መግባት አይችልም። ተድላ ግን፣ ከቢትወደድ አንዳርጋቸው ይልቅ በጣም የሚፈሩት ፊታውራሪ አስፍሐ ወልደሚካኤልን ነበር። ገና ከመጀመሪያው የታወቁት የቀድሞ የናዚ አነጋጋሪ፣ እንዴት በኤርትራ የዘውዱ እንደራሴ ምክትል ሆነው ይሾማሉ ? ..... በማለት ተድላ ቅሬታቸውን አልሸሸጉም። ከዚህም በላይ አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ በኤርትራ ውስጥ የክርስቲያኑም የእስላሙም ባላባቶች ወዳጅ፣ በተለይ ደግሞ የሸዋ መኳንንት ባለሟል፣ በተጨማሪም ታሪክ አዋቂና ተንኮል አርቃቂ፣ ናቸው በማለት ተድላ ባይሩ አጅግ ይሰጋሉ።

ፊታውራሪ አስፍሐ ደግሞ፣ ተድላ ባይሩ ምንም እንከን በሌለው ኢትዮጵያዊነት ለአንድነት ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረጉ ቢሆንም፤ የፖለቲካ ስልትና ከሰዎች ጋር የመቀራረብ ዘዴ የሌላቸው፣ የሥልጣን አያያዝና የአመራር ችሎታ የሚያጥራቸው ናቸው በማለት፤ የሥራ ፍሬያቸውን ይጠራጠራሉ። ስለዚህ ከቢትወደድ አንዳርጋቸው ጋር ሆነን እኛ በምክርና በዘዴ እየመራናቸው፣ ፌዴሬሽኑ ሳይዘገይ በቶሎ እየላላ ፍጹም የሆነውን አንድነት፣ ከግቡ ማድረስ አለብን ብለው፣ ዓላማቸውን መሥርተዋል። ፊታውራሪ ቢትወደድን ይዘው ይህን ዕቅድ የወጠኑት፣ ከራሳቸው በመነጨ ሀሳብ ? ወይስ ከንጉሠ ነገሥቱ በተሰጣቸው አደራ ነው ? ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ ማስረጃ አልተገኘለትም። ስለ ኤርትራ አስተዳደር፤ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስም ሆኑ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ በሥራ ላይ መዋል የጀመረው የፌዴሬሽን አመራር የሚፈርስበት መንገድ እንዲጠና፣ ከጃንሆይ እንዳልተጠየቀ ተረጋግጧል። ይሁን አንጂ የልዕልት ተናኘወርቅ ኃይለሥላሴ ባለቤት፣ በንጉሣዊ ቤተሰብነታቸው፤ አስፍሐ ወልደሚካኤልም ከአሥር ዓመት ጀምሮ በተመሠረተው ባለሟልነታቸው፣ የፌዴሬሽኑን መፍረስ ወይም ማላላት በሥውር መንገድ አማክረው፣ ከአባ ጠቅል መምሪያ ሳይቀበሉ አልቀሩም ተብሎ ይነገራል። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ግን፤ ስለ ኤርትራ ጉዳይ በይፋ በሚያደርጉት ንግግር ሁሉ፣ በተባበሩት መንግሥታት የተዘጋጀውና በእሳቸው የጸደቀው ሕገ መንግሥት መከበር እንዳለበት ከማስገንዘብ አላቋረጡም።

ፌዴሬሽኑ ሩቅ ሳይጓዝ ባጭሩ እንዲቀጭ ውስጥ ውስጡን ለሚዘጋጀው ፕላን፣ መሐንዲስ የሆኑት አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ በዚያን ዘመን ትልቁ ሥጋታቸው ምን እንደነበረ ሲያስረዱ፤ « ..... <u>ፌዴሬሽኑን እያዳከምን የኤርትራ</u>

ሕዝብ ከእናቱ ከኢትዮጵያ የተለየ አስተዳደር የሌለው መሆኑን እንዲሰማው ካላደረግን፤ የማተያንሶ ኮንስቲቱሽን እየተለመደና እየጣመ፤ በመጨረሻም የፍጹም ኢትዮጵያዊነት መንፈስ እየቀዘቀዘ ስለሚሄድ ነው:: ..... » ብለዋል:: በመሠረቱ በዚህ ሀሳብ የጃንሆይ ምክትል እንደራሴ ብቻቸውን የቆሙ አልነበሩም:: የተባበሩት መንግሥታት ይህን «ፌዴሬሽን» የተባለ እንቅፋት ተከለብን በማለት፣ እጅግ ያዘኑት የኤርትራ መኳንንቶችና ወይዛዝርቶች፣ ለምሣሌ ያህል እነ ራስ ኪዳነማርያም ገብረመስቀል፣ እነ ራስ [illegible] ባራኪ፣ እነ ራስ ኃይሌ ተስፋማርያም፣ እነ ከንቲባ ኦስማን፣ እነ ሼህ አል አሚን አብድልቃድር፣ እነ መላከሠላም ዲሚጥሮስ ገብረማርያም፣ እነ ወይዘሮ አስካለማርያም የማነ እና ሌሎቹም፣ ከአስፍሐ ወልደሚካኤል ጋር ይተባበራሉ:: ይሁን እንጂ፣ ይህ በማህበረ ፍቅሬ ሀገር አባሎች የሚወጠነጠነው የፌዴሬሽን አስተዳደር ፕሮብሌም፣ በኤርትራና በኢትዮጵያ ሕዝቦች ዘንድ፣ ጥቅምና ጉዳቱ ተለይቶ የሚታወቅ አልነበረም::

ከሸዋ ሕዝብ ከመቶ ዘጠናው፣ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀሏን እንጂ፣ ፌዴሬሽን .... ፌዴራል አክት ..... ቼፍ ኤግዜኩቲፍ እየተባሉ የሚጠሩት ቃላቶች ሁሉ እያንዳንዳቸው ምን ትርጉም እንዳላቸው አልተረዳም:: በታሪክና በባሕል የሚራቀቀው የጐጃምና የጐንደር ሕዝብ «ሆግሌኖች ወደ እኛ መጥተዋል» እያለ የተለመደ ትችቱን ወረወረ እንጂ፣ ስለ ሕገ መንግሥቱ ሆነ፣ ስለአስተዳደሩ ያለውን ጣጣ አልሰማም:: በሌሎቹም ጠቅላይ ግዛቶች በከፋ ሆነ በወለጋ፣ በአሩሲ ሆነ በሲዳሞ ያለው ሕዝብ፣ ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ ተቀላቀለች ተብሎ የሚነገረውን ከመስማት በስተቀር፣ ሌላውን ጉዳይ አላወቀም:: ከንጉሠ ነገሥቱ ሚኒስትሮችና ከፍተኛ ባለሥልጣኖች መካከል አብዛኞዎቹ፤ ይህ ኤርትራ ላይ የተፈጠረ ፌዴሬሽን የተባለ ሕግ፣ ለአንዲት ኢትዮጵያ ተብሎ በብዙ ችግር ለተቋቋመው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አስተዳደር፣ አጉል ምሣሌ የሚሰጥ ነው ብለው ይጨነቃሉ:: በጣም ጥቂቶቹ ደግሞ፣ ዕድሜ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ ይህ ለኤርትራ የተሰጠው የውስጥ አስተዳደር መብት፣ ለሌሎቹም የኢትዮጵያ አውራጃዎች ዕድሉ እንዲሰጥ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ስለሚያስገድዳቸው፣ በአገራችን ላይ የሚያንሰራራውን የፊውዳልን ዳመና ለመጥረግና የልማት እድገትን ለማፋጠን ይረዳል ብለው ይደሰታሉ:: ዞሮ ዞሮ የእነዚህ የጥቂቶች አዲስ መጥ ኢንተሌክቱዌሎች፣ ሀሳባቸው ወደ ሕዝቡ የሚዛመትበት መንገድ ስለሌለውና፣ ምኞታቸውም እዚያው እቴጌ ሆቴል በሚሰበሰቡበት ባር ቀልጦ የሚቀር ስለሆነ፣ መንግሥት የእነሱን አስተያየት በቁም ነገር ለማጥናት አልተጨነቀበትም::

መስከረም 11 ቀን 1952 ዓ.ም (በኢት.አቆ. ዘመነ ማቴዎስ መስከረም 1 ቀን 1945 ዓ.ም) የኤርትራ ፌዴራል አክት ሲፈረም፣ አዲስ አበባ በተከበረው ስፊው በዓል ላይ እና፣ ከዚያም ቀጥሎ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መረብን አቋርጠው በከረሙባቸው ጊዜያቶች፣ የተደረጉት ወሰን የሌላቸው ዲስኩሮች ሁሉ፣ አንድነትንና ታሪክን ከሚመለከት ውጭ፣ ስለፌዴሬሽኑ ሥርዓትና ስለ ሕገ መንግሥቱ የሚያብራሩ ቃላቶች አልተሰሙባቸውም:: ተድላ ባይሩና ካቢኔያቸውም ሥልጣን በተረከቡበት ወራት፣ የኤርትራና የኢትዮጵያ መቀላቀል በሕዝቡ ላይ ያሳደረውን ደስታ ከማፋፋምና የኢትዮጵያዊነት ስሜቱን ከማጋል በስተቀር፣ የፌዴሬሽኑ ሥርዓት ከአዲስ አበባ የተለየ አስተዳደር መሆኑን የሚያሳይ ምልክት አልሰጡም:: ሆኖም ፌዴሬሽኑ እየተዳከመ ወደ ፍጹም የውህደት ጉዳና በፍጥነት እንዲያመራ የአንድነት ታጋዮች የሚፈልጉትን፣ ሙሉ በሙሉ ለመከተልና አብሮ ለመሮጥ ተድላ ባይሩና ካቢኔያቸው አልተዘጋጁም::

የተድላ አስተያየት፣ ፌዴሬሽኑን ሰርዘን አንድነትን ለማዋሀድ በአርጋታና በሆደ ሰፊነታችን በስተቀር፣ ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል እንደሚባለው፣ በጥድፊያ የምንፈጽመው ድልድይ ሳያሻግረን፤ ገደል ወስዶ ሊጥለን ይችላል፤ የሚል ነው፡፡ የነ አስፍሐ ወገኖች ደግሞ ይህንን በአርጋታ እንራመድ የሚባለውን ነገር አይቀበሉም፡፡ እነሱ የሚሉት፣ ጊዜ መፍጀቱ የሚጠቅመው ጠላቶቻችን እንዲዘጋጁብን ዕድል ለመስጠት ብቻ ነው፡፡ ጠላቶቻችን ጊዜ ሲያገኙ፣ አሁን በጋለው በሕዝባችን ኢትዮጵያዊነት ስሜት ላይ፣ በፕሮፓጋንዳቸው ክፉ መርዝ ለመነስነስና ቅን ዓላማውን ለማስለወጥ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ፣ የተድላ፡ባይሩ አስተዳደር በአሠራሩና በአፈጻጸሙ ፌዴሬሽኑን ለመደምሰስና የሕዝቡን አንድነት ስሜት ለማፋፋም እርምጃ መውሰድ ያለበት፣ ዛሬ ነው እንጂ ነገ አይደለም፡፡ ...... ፌዴሬሽን የኤርትራ ሕዝብ ጥያቄ አይደለም፡፡ ንጉሠ ነገሥት ኃይለሥላሴ ይህን በተንኮል የተቀመመ የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ የተቀበሉት፣ ግዴታ ሆኖባቸው ነው፡፡ አሁን ለአምላክ ምሥጋና ይግባው፣ ከእንግሊዞች በሠላም ተገላግለናል፡፡ ነፃነታችንን ተቀብለን ኢትዮጵያዊነታችንን ተረክበናል፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ የሕዝቡን ፍላጐት ተከትለን ከግባችን ለመድረስ ሥልጣኑም መብቱም የኛው የኤርትራውያኖች ስለሆነ፣ ከውጭ ድንበራችንን ጥሶ ማንም ሊጠይቀን አይችልም፡፡ ...... በማለት ቺፍ ኤግዜኩቲፉን ወጥረው ያዙ፡፡

አቶ ተድላ ለዚህ መልስ ለመስጠትና በአቋማቸው ለመርጋት ከአዲስ አበባ ከስድስት ኪሎ ሠፈር* መካሪም ደጋፊም አላጡም፡፡ « .... ከፍጹም ኢትዮጵያነት ግባችን ለመድረስ ደረጃ በደረጃ እንራመድ ሲባል፣ ለጠላቶቻችን ምቹ እንሆናለን ማለት አይደለም፡፡ ..... ይልቅስ ጠላቶቻችን የውጭ አገር መንግሥታቶችን እርዳታ በማግኘት ኃይላቸውን ለማጠንከር የሚችሉት፣ እኛ አንድነቶች በሚገባ ሳንዘጋጅ ተሽቀዳድመን የተባበሩት መንግሥታትን ውሳኔ አፍራሽ ሆነን ስንገኝ ነው፡፡ ..... ይህንን ስሕተት የፈጸምን እንደሆነ፣ እጅግ አድርገን የምንጐዳው አገራችንን ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን፣ በዓለም ላይ ከፍተኛ አክብሮትና አድናቆት የተሰጣቸውን የንጉሠ ነገሥታችንን ክብር ጭምር ነው ..... » በሚል አቀራረብ፣ ፌዴሬሽኑን በጥድፊያ ለማፍረስ አልሞከርም አሉ፡፡

እንግዲህ « መንግሥቲ ኤርትራ » ሥራውን በጀመረ በጥቂት ወራቶች ውስጥ፣ በአንድነት አጥባቂ ወገኖችና በአንድነት ሞዴሬት ግሩፖች መካከል፣ የተፈጠረውን የሀሳብ ልዩነት ማን አቀራርቦ መፍትሔ ይስጠው ?

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ፊታውራሪ አስፍሐና መላከ ሠላም ዲሚጥሮስ፣ የኤርትራን ዋና ዋና ያገር ሽማግሌዎች ይዘው የሚያቀርቡላቸውን ሀሳብ፣በይፋ ሳይሆን ውስጥ ውስጡን ያበረታቻሉ እየተባለ ይነገራል፡፡ ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ደግሞ ካቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ጋር ሆነው፣ ተድላ ባይሩ ያሳዩት አቋም ትክክለኛ እና ሊደገፍ የሚገባው ነው እያሉ ለንጉሠ ነገሥቱ በየጊዜው ማስረዳታቸውን አላቋረጡም፡፡ ወልደጊዮርጊስ ተድላ ባይሩን መደገፋቸውና ፌዴሬሽኑም በቶሎ እንዲፈርስ የሚባለው ሀሳብ እንደማይጥማቸው ለማንም ግልጽ ነበር፡፡ አቶ አክሊሉም « ..... ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ ግርማዊነትዎ ቢፈቅዱ፣ ታላላቅ መንግሥታቶች፣ ገና ከመጀመሪያው የተናገርነውና የፈራነው ደረሰ በማለት፣ በብዙ ረገድ እንደሚጐዱን መታወቅ አለበት፡፡ በኤርትራ ውስጥም ቢሆን

* ከጽሕፈት ሚኒስትሩ

የውጭ እጅ ስለሚገባበት፣ ብዙ ብጥብጥ ተፈጥሮ ሕዝቡ ሊከፋፈልና ሠላም ሊጠፋ ይችላል ..... » ብለው ለጃንሆይ በየጊዜው ሀሳብ ማቅረባቸው ምሥጢር አልነበረም።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጃንሆይን በዚህ አኳኋን የመምከራቸው ዜና አሥመራ ደርሶ፣ የአንድነት አጥባቂ ወገኖች ሲሰሙት፣ በአቶ አክሊሉ ላይ እጅግ አድርገው አዘኑ። ለጃንሆይ መልካም ፈቃድ የራስ ወርቅ ያሠሩትና የደጃዝማችነት ወርቀዘቦ ካባ ያጠለቁት፣ ታላላቆቹ የኤርትራ መኳንንቶች ወዲያውኑ ለጃንሆይ በላኩት መልዕክት፣ ስለ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ የገለጹት አስተያየት ዋና ዋናው የሚከተለው ነበር።

« ..... እኛ ኤርትራውያን ታማኝ ዜጎችዎ፣ ዕድሜ ለግርማዊነትዎ እያልን ያስእንዳች ሀተታ ኢትዮጵያዊነታችንን እንልበስ፣ ኢትዮጵያዊነታችንን እናጥብቅ ስንል፣ እቶ አክሊሉ ሀብተወልድ የውጭ መንግሥቶች አገራችንን ይጉዳሉ እያለ የሚያስፈራራንን ስምተን እጅግ አዝነናል። ፈረንጆች ምን ጊዜም ለኢትዮጵያ የማይተኙላት መሆናቸውን በቂ የታሪክ ምስክር አለን። አቶ አክሊሉም ደህና አድርጐ ያውቀዋል። ደግሞስ እኛ የመረብ ምላሽ ሕዝቦች፣ መሠረታችን የሆነውን ኢትዮጵያዊነታችንን ብናጠብቅ፣ የፈረንጆቹ ጥቅም የሚነካው እምኑ ላይ እንደሆነ እቶ አክሊሉ አላስረዳንም። አቶ አክሊሉ የታላቁ ጌታችንን መልዕክት አደራ ይዞ፣ በዓለም በመዞር ብዙ እንደሠራ፣ ብዙ እንደደከመ፣ ብዙ እንደተሚገተ እናውቃለን። ነገር ግን እኛ በኢትዮጵያዊነት ያገር ፍቅር የምንታገል የኤርትራ ሕዝቦች፣ ዓላማችንና ሀሳባችን ምን እንደሆነ እቶ አክሊሉ በትክክሉ አልተረዳልንም። የዚህ ፌዴራሲዮን የተባለው ጣጣ፣ ከእናታችን ከኢትዮጵያ የተለየን አድርጐ በማሳየት ያደረሰብንን ስቃይ አቶ አክሊሉ እዚህ መጥቶ ከእኛ ጋር በሰፊው በመነጋገር እንዲገነዘብልን የጃንሆይን ፈቃድ በታላቅ ትህትና እንለምናለን። አቶ አክሊሉ እዚህ ሲመጣ፣ እንደ ጌታችን መልዕክተኛ እና እንደ ልጃችን አድርገን በመቀበል ሁሉንም ነገር ስናስረዳው፣ በትልቁ የፈረንጅ ዕውቀቱ ላይ የኛን ትምህርት ሲጨምርበት፣ ወደፊት ለጃንሆይም ለኢትዮጵያም የሚያደርገው አገልግሎት የበለጠ እና የተባረከ ይሆናል። ...... »

ታላላቆቹ የአንድነት ወገኖች ይህን ማስታወሻ በአስፍሐ ወልደሚካኤል በኩል ቢልኩም፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸውን ወደ እነሱ ልከው ፊት ለፊት ለማጋፈጥ ጃንሆይ አልፈለጉም። በመሠረቱ ከንጉሠ ነገሥቱ ሚኒስትሮች ለጃንሆይ በተለይ የሚቀርቡት ማስታወሻዎች ሁሉ ከዝጉ ልዑል ቤተ መንግሥት መውጣት የለባቸውም። ይህ የአቶ አክሊሉ አስተያየት በዘዴ ወደ አሥመራ ተልኮ ወደ አንድነት አጥባቂዎች ጆሮ እንዲደርስ የተደረገው፣ ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ የሚቀርበውን ሀሳብ ምክንያት እየፈጠሩ የሚያስናክሉና፣ ጃንሆይን የሚያስቸግሩ ሰዎች አሉ ተብሎ እንዲወራ ታስቦበት የተደረገ ዘዴ ነው ይባላል።

በዚህ አኳኋን ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ እርምጃችን ይፍጠን ብለው በተነሱትና፣ በእርጋታ እናስብበት በሚሉት መካከል፣ የተፈጠረውን ልዩነት ማቀራረቢና መፍትሔ መስጠት የሚችሉት ንጉሠ ነገሥቱ ብቻ ሲሆኑ፣ እሳቸውም አንዳችም እርምጃ ሳይወስዱ ሰነበቱ። በዚህ ማሀል፣ የአንድነት ወገኖች እርስ በርሳቸው ሲነዛነዙ፣ የኤርትራን ፌዴሬሽን አጠንክረው ወደ ነፃነት ለማሻገር እጅግ የሚጥሩት ወልደአብ ወልደማርያም፣ ፕሮፓጋንዳቸውን እያፋፋሙ መጋቢት 14

ቀን 1952 ዓ.ም በከፊል ለሚደረገው የፓርላማ ምርጫ ተወዳዳሪ ሆነው ብቅ አሉ።

በየአራቱ ዓመት የፓርላማ ጠቅላላ ምርጫ ከመደረጉ በፊት፣ አንዳንድ አባሎች ለካቢኔ ሴክረተሪነትና ለከፍተኛ ሹመት መንግሥት ሲመድባቸው፣ ወይም ደግሞ በድንገት ሲሞቱ፣ የፓርላማ ወንበራቸው ለሌሎች ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ፣ በከፊል የፓርላማ ምርጫ እንዲደረግ ሕገ መንግሥቱ ይጠይቃል።

በመጋቢት 1952 ዓ.ም የኤርትራን ሕገ መንግሥት ለማዘጋጀት የሕዝብ እንደራሴዎች ጠቅላላ ምርጫ ሲደረግ ጊዜ፣ ወልደአብ ወልደማርያም ከተሸነፉት ተወዳዳሪዎች አንዱ መሆናቸው ይታወሳል። በዚያን ጊዜ ተድላ ባይሩና ወዳጆቻቸው በእንግሊዞች እርዳታ የኢብራሂም ሡልጣንን መመረጥ ከምንም ሳይቆጥሩት፣ በወልደአብ መሸነፍ እጅግ ተደስተው ነበር። አሁን ከአንድ ዓመት በኋላ በዚህ በመጋቢት 1953 ዓ.ም ለተወሰኑ ቦታዎች የከፊል የፓርላማ ምርጫ ሲደረግ፤ ወልደአብ አሥመራ ላይ ቀርበው ለመወዳደር ያደረጉት ዝግጅት አሸናፊ እንደሚሆኑ ተገመተ። በዚህ ጊዜ፣ ተድላ ባይሩና ከነሔያቸው ይህን የወልደአብን ምርጫ ባለው አቅም ሁሉ ለማሰናከል፤ ብርቱ ጥረት ማድረግ ስለነበረበት፣ ስለ ፌዴሬሽን ሕይወት ከአንድነት አጥባቂዎች ጋር የሚያደርገውን የሀሳብ ልውውጥ አቆመ።

ከአዲስ አበባም፤ ከገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት በኩል፤ ወልደአብ ወልደማርያም ለፓርላማው ተመርጦ ቢገባ ለተድላ ባይሩ መንግሥትና ለአንድነት ወገኖች፣ ጤና የሚነሳ መሆኑ ስለታመነበት፤ እነ አስፍሐ ወልደሚካኤል ከቺፍ ኤግዜኩቲፍ ጋር ሆነው በወልደአብ ቦታ የፍቅረ ሀገር ወገን የሆነ ሰው እንዲመረጥ፣ ብርቱ ጥረት እንዲያደርጉ ተጠየቁ።

## ተድላና ወልደዓብ ሁለት ባለጋራዎች

በተድላ ባይሩና በወልደዓብ ወልደማርያም መካከል የተፈጠረው የከረረ ጠብ፣ በኤርትራ ጉዳይ ባላቸው የተለያየ አቋም ምክንያት ብቻ ሳይሆን፣ ሁለቱ ሰዎች በግል የማይጣጣሙና የሚጠላሉ በመሆናቸው ነው።

ተድላና ወልደአብ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቁት፣ በ1941 ዓ.ም አሥመራ ላይ የኤርትራና የኢትዮጵያ ያገር ፍቅር አንድነት ማህበር በተቋቋመ ጊዜ ነው። አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት፣ ከዚያ በፊት በመኖሪያም ሠፈር ሆነ በትምህርት ቤት ተያይተው አያውቁም። በዕድሜ አቶ ተድላ ይበልጣሉ። አቶ ወልደአብ ግን በቀለም ትምህርት በመግፋትና በተጨማሪም « የብዕር ሰው » በመሆን እበልጣለሁ በማለት ለተድላ ዝቅተኛ አስተያየት ነበራቸው።

ዝነኛው ያገር ፍቅር አንድነት ማህበር፣ በአቶ ገብረመስቀል ወልዱ ሊቀመንበርነት በሚመራበት ጊዜ፣ ተድላና ወልደዓብ ለማህበሩ ዓላማና ዕድገት የሚጠየቁትን የየድርሻቸውን ተግባር ከመፈጸም በስተቀር፣ እርስ በርሳቸው ፊት ለፊት የሚጋጩበት ምክንያት አልነበራቸውም። ማህበሩ በተቋቋመ በሶስተኛው ዓመት ላይ፣ ለዚህ እጅግ ከፍ ላለው ለኤርትራና ለኢትዮጵያ አንድነት ጉዳይ፣ በመሪነቱ ቦታ የኤርትራ ታላላቅ መኳንንቶችና የሀይማኖት መሪዎች ግንባር ቀደም ቢሆኑ፣ ሕዝቡን በይበልጥ ለማሰባሰብና ዓላማውን እንዲከተል ለማድረግ ይረዳል

ተብሎ፣ በመማክርቱ ጉባኤ ተወሰነ:: በዚህ ጊዜ ተድላ ባይሩ ሙሉ ድጋፋቸውን ገልጠው ለአፈጻጸሙ ጥረት ሲያደርጉ፣ ወልደአብ ወልደማርያም ከእምነቴ ጋር አይገናኝም ብለው ሀሳቡን ሳይቀበሉት ቀሩ።

| | |
|---|---|
| ራስ ኪዳነማርያም ገብረመስቀል የሹብር | ፕሬዚዳንት፣ |
| ደጃዝማች በየነ ባራኪ | ፕሬዚዳንት |
| ሡላህ አህመድ ኪኪያ | ም/ፕሬዚዳንት |
| አቶ ተድላ ባይሩ | ዋና ጸሐፊ |

እንዲሁም፣ ለየአውራጃዎቹ፤

| | |
|---|---|
| ለሠራዬ አውራጃ | ራብ ኃይሌ ተስፋማርያም |
| ለአካለ ጉዛይ | ደጃዝማች ዘውዴ ሀጐስ |
| ለምዕራባዊው ቆላ | ከንቲባ የሰማን |
| ለምሥራቃዊው ቆላ | ሼህ አላሚን |

ሆነው ሲመደቡ፣ ወልደዓብ ወልደማርያም እሳቸው የሚያምኑበትን ሀሳብ ለማስፋፋትም ሆነ ለመገንባት፣ ምንም ቦታ እንደሌላቸው ተገነዘቡ:: ከዚህም በላይ ዋና ጸሐፊ ሆነው ከተመረጡት ከተድላ ባይሩ ጋር በምንም አኳኋን ተግባብቶ ለመሥራት አይቻልም ብለው ተስፋ ቆረጡ:: ሆኖም የማህበረ ፍቅሪ ሀገርን ከመልቀቃቸው በፊት ስለ ኤርትራ የወደፊት ዕድል የራሳቸው ሀሳብ ምን እንደሆነ እንዲታወቅላቸው ብዙ ጥረት አደረጉ:: ይኸውም « ..... ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር ለማቀላቀል፣ መጀመርተያ ከአጼ ኃይለሥላሴ ጋር አንድ ውል ማድረግ ያስፈልጋል:: ይህም ውል ለኤርትራ የሚያስፈልገውን የአቶኖሚና የተለየ አስተዳደር የሚዘረዝር መሆን አለበት..... » የሚል መሆኑ ተነገረ::

የማህበረ ፍቅሪ ሀገር መሪዎቹም ሆኑ አባሎቹ፣ ለዚህ ከወልደአብ ወልደማርያም ለቀረበው ሀሳብ ከመገረም በስተቀር ምንም ዓይነት ግምት አልሰጡትም:: አንድ ጊዜ በአሥመራና በምፅዋ መካከል በሚገኘው « ቤተ ጊዮርጊስ » በተባለ ሥፍራ፣ ጥቂቶች ያገር ፍቅር ማህበር መሪዎችና አባሎች ተሰብስበው ሲወያዩ፣ ተድላና ወልደአብ የተለዋወጧቸው ቃላቶች የሁለቱን ሰዎች በሀሳብ መራራቅ ብቻ ሳይሆን፣ መጠላላታቸውንም በትክክል ያሳያል:: እንደተለመደው ወልደአብ ወልደማርያም፣ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር የምትቀላቀለው በሕግ በተደነገገ ውል መሆን አለበት፣ የሚሉትን ሀሳብ እየደጋገሙ ይናገራሉ:: የአንድነት ማህበር ዋና ጸሐፊ ደግሞ፣ ተለያይተው የኖሩ እናትና ልጆች ብዙ እፍዳ ደርሶባቸው፣ ከብዙ ዓመታት በኋላ ሲገናኙ ምን ውል ያስፈልጋቸዋል ? በማለት ለማስረዳት ሲሞክሩ፣ ወልደአብ ፊታቸውን አጥቁረው ለማዳመጥ የማይጥማቸው መሆኑን ያሳያሉ:: በዚህ ጊዜ ተድላ ግልፍ ይላቸውና፣ እረ ለመሆኑ እርስዎ መሠረተ ትውልድዎ የት ነው ? ብለው ይጠይቋቸዋል:: ትውልዴ አክሱም አጠገብ ከምትገኝ «ዓዲ ክልተ» ከምትባል ቀበሌ ነው ብለው፣ ወልደአብ ይመልሳሉ:: አቶ ተድላ ቀጠል ያደርጉና፤ ትውልድዎ አክሱም ከሆነ፣ ታዲያ የኤርትራ ጉዳይ ምን ይመለከትዎታል ? ይሏቸዋል:: ወልደአብ በኸፈለ ስሜት « ... እንኳን እኔ አክሱም አገሬ፤ በኩረ ሎሚ የማሸተው ትውልዴ ቀርቶ፤ ከናይጄሪያ የመጣ ጀዓሊ፣ ከየመን የመጣ ጀበሊ፣ በኤርትራ ኖሬአለሁ ብሎ፣ ስለ ኤርትራ ዕድል ለመናገር ችሎ የለም ወይ ? ..... » ብለው መለሱላቸው:: የአቶ ተድላ ወላጆች ሥራታቸው ከናይጄሪያ የመጣነው እየተባለ ስለሚነገር፣ የወልደአብ

አሽሙር ይህንን ለመንካት ነው ተብሎ ይተረካል:: በዚህ የአገር ፍቅር ማህበር ዓላማ ውስጥ « ኢትዮጵያ ወይም ሞት » እንጂ፣ በውል የሚፈጸም የእናትና የልጅ ግንኙነት ይኖራል ተብሎ ስለማይታሰብ፣ የወልደአብ ሰቅድ ተከታይ ሳያገኝ ቀረ::

ማህበረ ፍቅረ ሀገርን ለቅቀው ከወጡ በኋላ፣ ላይ ላዩን ኤርትራ ለኤርትራውያን እያሉ በመፎከር፣ ውስጥ ውስጡን ግን እንግሊዞች ኤርትራንና ትግራይን አጠቃለው እንዲያስተዳድሩ ከሚመኙት፣ ከነ ራስ ተሰማ አስበሮም ጋር ሲቀላቀሉ፣ « የወልደአብ ጉድ » እየተባለ በተለይ በደገኛውና በክርስቲያኑ ሕዝብ ዘንድ በብዙ ተሾቀሉ:: የአንድነት ወገኖችና ጋዜጦቻቸውም፣ « ወልደአብ ኤርትራንና እናት ኢትዮጵያን የከዳ፣ ለውጭ ጠላት በገንዘብ የተሸጠ » እያሉ በሰፊው ሲያወግዟቸው፣ ጉዳቱ ብርቱ መሆኑ ተሰማቸው:: ይህ ሁሉ የሚነዛባቸው ፕሮፖጋንዳ ሀሰት መሆኑን እና ትክክለኛውም አቋማቸው ምን እንደሆነ፣ የሚገልጽ ደብዳቤ አዘጋጅተው ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ላኩ::

የወልደዓብ ወልደማርያም ደብዳቤ፣ አሳቸው ልክ እንደተጠቀሙባቸው ቃላቶችና ዓረፍተ ነገሮች ሳይሆን፣ ባልከበደ አግርኛ በመጠኑ ሲብራራ መሠረታዊው ሀሳባቸው የሚከተለው ይሆናል:: « .... ኢትዮጵያና መንግሥቷን፣ ታላቋ ንጉሠ ነገሥቷን አፄ ኃይለሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔርን፣ የሚጠላ ነው እየተባለ የሚነገርብኝን፣ ሁሉን ከሚሰሙ ከግርማዊነትዎ ጆሮ ሳይደርስ አልቀረም::..... እኔ በንጹሕ ያገር ፍቅርና በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ያደግሁ ስለሆንኩ፣ ይህንን የመሰለው ..... ሰይጣናዊ ሀሳብ በልቤ ሊመሠረት አይችልም::

..... ግርማዊነትዎ በድል አድራጊነት ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሱ፣ ከጥቂቶች ባልንጀሮቼ ጋር ሆኜ፣ ይህችን ዛሬ ሰፊ የሆነችውን የኤርትራንና የኢትዮጵያን አንድነት ማህበር መሠረትኳት:: ..... ከሶስት ዓመት በበለጠ ዘመን፣ የዚች ማህበር መሪ ከተባሉት ሰዎች አንዱ ሆኜ በታማኝነት አገለገልኳት:: ..... የኤርትራ ሕዝብ ከጣልያን ከተላቀቀ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት መናፈቅ የጀመረው፣ ለራሴ ምሥጋና በመፈለግ ሳይሆን፣ አብዛኛው ምክንያት እኔ ባደረግኩት የጋዜጣ ስብከት ነው::

..... በ1945 ዓ.ም ከባልንጀሮቼ ጋር ሆኜ አንድ አዲስ ማህበር በማቋቋም ለኤርትራ (15) አሥራ አምስት ዓመት የትራስት ሺፕ (የሞግዚት) አስተዳደር መላመድ ያስፈልጋል ያልኩት፣ ...... የኤርትራና የኢትዮጵያ አንድነት እንዲሰምር በቂ ጊዜ ለማግኘት ነው እንጂ፣ ሀሳቡ በጠላት የታቀደና እኔም የጠላት መሣሪያ ሆኜ አይደለም:: ...... »

ይህ ወልደዓብ የጻፉት ደብዳቤ፣ ግቡ በትክክል ምን እንደሆነ አልታወቀም:: የጽሑፉ አቀራረብና የገለጹት ሀሳብ ሲታይ፣ የንጉሠ ነገሥቱን መልካም አስተያየት አግኝቶ ለመቅረብም ሆነ ከአንድነት ማህበር ጋር ያላቸውን ጠብ ለማብረድ የሚረዳ አይደለም::

የኤርትራንና የኢትዮጵያን አንድነት ማህበር የመሠረትኩትና ዛሬ ለደረሰበት ደረጃ ያበቃሁት እኔ ነኝ ለሚሉት፣ ከራሳቸው በስተቀር ሌላ ምሥክር አልተገኘላቸውም:: « ኤርትራ ለአሥራ አምስት ዓመት በባዕድ መንግሥት የሞግዚት አስተዳደር እንድትቆይ ያቀረብኩት ሀሳብ ወደፊት ከኢትዮጵያ ጋር



ወልደአብ ወልደማርያም

ለኤርትራና ለኢትዮጵያ አንድነት ለመጀመሪያ ሶስት ዓመት ደጋፊ፣
ለአርባ ዓመታት ተቃዋሚ ሆነው የኖሩ እምቢተኛ፣

የሚደረገው አንድነት እንዲሰምር ብዬ ነው » የሚሉትን፣ ማንም ሰው ሊያምናቸው አይችልም:: ማህበረ ፍቅሪ ሀገርን ለቅቀው የወጡበት የመጀመሪያው ምክንያት « አንድነት በውል » ለሚለው ሀሳባቸው የሚተባበራቸው በማጣት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የተድላን ዋና ጸሐፊነት ባለመቀበል መሆኑ የታወቀ ነው::

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በልማዳቸው፣ ለሚጻፍላቸው ሁሉ ወዲያውኑ መልስ ሰጭነታቸው የታወቀ ሲሆን፣ ከወልደአብ ለደረሳቸው ማመልከቻ ምን እንዳሉ የሚገልጽ መረጃ እስካሁን አልተገኘም:: በቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል አስተያየት ግን ወልደአብ ለንጉሠ ነገሥቱ የጻፉት ማስታወሻ ቅን አስተያየትና እውነትን የጨበጠ አይደለም በማለት፣ በጽሑፍም ሆነ በቃል ከገነተ ልዑል ቤተመንግሥት መልስ እንዲሰጥ አልተደረገም:: እንግዲህ ለጉዳዩ አልባት ለመስጠ ት፣ ወልደአብ ወልደማርያም ኢትዮጵያንና መንግሥቷን፣ ሸዋ .... አማራ .... እያሉ የሚጠሉ፤ የኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ የማይፈልጉ ናቸው ተብሉ የታመነበትን፣ ይህ የጻፉት ደብዳቤ ሊያሻሽለው ቀጅም ሊለውጠው አልቻለም፣ ብሎ ከመዝጋት በስተቀር፤ ሌላ መንገድ የለም::

# ኤርትራ የኢትዮጵያ አይደለችም

(ወልደአብ ወልደማርያም)

በእንግሊዞች ገንዘብና እርዳታ ራስ ተሰማ አስበሮምና ልጃቸው ደጃዝማች አብርሃ ተሰማ «የሊበራል ፕሮግሬሲስት ፓርቲ» መሪዎቹ ተብለው አደባባይ ሲቆሙ፣ ወልደአብ ወልደማርያም ዋና ፕላን ነዳፊና በጀርባ መሪ ሆነው፣ የመሠረትኩት እኔ ነኝ እያሉ፤ የሚፎክሩበትን የማህበረ ፍቅሪ ሀገርን ዓላማ በብርቱ ማጥቃት ቀጠሉ::

የታወቁት ፊውዳሎችና ለኮሎኒያሊስቶች ተገዥ የሆኑት የተሰማ አስበሮም ቤተሰቦች፣ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለማስጣል የቆምን ነን ብለው ካባ ደርበው በያለበት ቢፎክሩም፣ ሕዝቡ ሊያምናቸውም ሊከተላቸውም ሳይፈልግ ቀረ:: ይህ በተንኮል የተቋቋመው ፓርቲ፣ ከቀን ወደ ቀን እየተዳከመና እየመነመነ ሲሄድ፣ በጣልያን ገንዘብ አዲስ በተቋቋመውና በኢብራሂም ሡልጣን በሚመራው፣ የነፃነት ግንባር በተባለው ፓርቲ ውስጥ ተዋህዶ ለኤርትራ ነፃነት ጠያቂ ሆነ::

የአንድነትን ማህበር ከለቀቁበት ምክንያቶች አንዱ፣ የመሪዎቹ የነ ተድላ ባይሩ ችሎታ ማጣር ነው እያሉ ሲተቹ የነበሩት ወልደአብ ወልደማርያም፤ በፋሽስቶች ገንዘብ ከተቋቋመውና በታወቀው ቀላማጅ በኢብራሂም ሡልጣን በሚመራው ፓርቲ አባል ሆነው መታየታቸው፣ የሚያኮራቸው አልነበረም:: ይህ በብዙ ሚሊዮን የጣልያን ሊሬ የተቋቋመው የነፃነት ግንባር ፓርቲ ከሸፎ፣ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል ሲወሰን፤ ወልደዓብ ወልደማርያም ኤርትራ የኢትዮጵያ አይደለችም ብለው የጀመሩትን ትግል አላቋረጡም::

የኤርትራን ሕገ መንግሥት ለማዘጋጀት የሕዝብ እንደራሴዎች ምርጫ በተደረገ ጊዜ፣ ኢብራሂም ሡልጣን ቶሎ ብሎ ጣልያኖችን ከድቶ፣ እንግሊዞችን በመማፀን፣ ለፓርላማው ተመርጦ ሲገባ፤ ገትጋታው ወልደዓብ ወልደማርያም

ሁሉንም እቃወማለሁ ሲሉ፣ ሳይሳካላቸው ተሸንፈው እውጭ ቀሩ። ተድላ በይሩ ግን፣ ገና ከጠዋቱ ያምኑበት የኤርትራንና የኢትዮጵያን አንድነት እውን ለማድረግ ባለማቋረጥ በመታገላቸው፣ የኤርትራ የመጀመሪያው የኦቶኖሚ መንግሥት መሪ ሆነው ለመመረጥ በቁ። የተድላ ዋና ባለጋራ የሆኑት ወልደአብ ወልደማርያም፣ በሚቀጥለው ጊዜ ፓርላማ ተመርጠው ለመግባትና፣ ተድላ ባይሩን በፖለቲካ ትግል ለማስቃየት ሙሉ ተስፋ አደረጉ።

ተድላ ባይሩ፣ በዚያን ዘመን ከፍተኛውን የሕዝብ አስተዳደር ኃላፊነት በመቀበል ከሥልጣን ጋር ትውውቅ ያደረጉት ለመጀመሪያ ጊዜ በመሆኑ፣ በአሠራራቸው የፖለቲካና የተንኮል ጥበብ እንደጐደላቸው በግልጽ ይታይ ነበር። ከዚህ ኤክስፔሪያንስ እጥረት የተነሳ፣ የታወቁት ባለጋራቸውን ወልደአብ ወልደማርያምን በፖለቲካ ሜዳ ታግሎ በመጣል ፋንታ፣ ሕይወታቸውን በሥውር አጥፍቶ ለመገላገል፣ ስባት ጊዜ ያስደረጉት ሙከራ ሳይሰምርላቸው ቀረ። አልሞት ባይ ተጋዳይ ወልደአብ ወልደማርያምም፣ ከባለጋራቸው በየጊዜው በሚጣልባቸው የፈንጂ አደጋ፣ እየቆሰሉ መታከሙን ስለለመዱት፣ ድነው ሲወጡ ያንኑ የተቃውሞ ሥራቸውን ከመቀጠል ወደ ኋላ አላሉም። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ የተድላ መንግሥት በተቋቋመ በስድስተኛው ወር፣ ለፓርላማው በሚደረገው የከፊል ምርጫ ተወዳድሮ ለማሸነፍ ወልደአብ ወልደማርያም በስፊው ተዘጋጅተው ነበር።

« ..... የኤርትራ ሕዝብ ስማ ! ..... የመንግሥትህ መሪ የሆነው ተድላ ባይሩ፣ ከጥቂቶች የፖርላማ አባሎች ጋር በገንዘብ ተደልሎ፣ የተባበሩት መንግሥታት የሰጠህን የነፃ አስተዳደር መብት አፍርሶ፣ ለሸዋው መንግሥት ሊያስረክብህና፣ የአማሮች ተገዥ ሊያደርግህ በመዘጋጀት ላይ ነው ....... የኤርትራ ሕዝብ ንቃ ! አንድ ጊዜ ከሸዋ ወጥመድ ውስጥ ከገባህ በኋላ ለዘለዓለሙ መውጫ አይኖርህም። የዓለም ጉባዔ ፈርዶ የሰጠህን የፌዴሬሽን መብት ለማስከበር፣ ቆርጦ የሚዋጋልህን ቀጥተኛ ኤርትራዊ ለፖርላማው አባልነት ምረጥ ...... » በሚል ቃል ወልደአብ ወልደማርያም እያዘጋጁ የሚያስበትኗቸው ጽሑፎች ብዙ ደጋፊ ሰበሰቡላቸው።

መጋቢት 14 ቀን 1953 ዓ.ም በአሥመራ ከተማ "CARAVANSERAI " ከተባለው ቀበሌ በተደረገው ውድድር ወልደአብ ወልደማርያም ከፍተኛውን የድምፅ ብልጫ ማግኘታቸው ሲታወቅ፣ ተድላ ባይሩ ወዲያውኑ የፍርደ ገምድል እርምጃ በመውሰድ፣ ምርጫው የተጭበረበረ ነው ብለው አገዱት።በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 46 እንደተገለጸው፣ የተጭበረበረ ነው ተብሎ ክስ የቀረበበት ምርጫ ሊሠረዝም ሊድንም የሚችለው፣ ለፓርላማው ቀርቦ በሁለት ሶስተኛ የድምፅ ብልጫ ሲፈረድ ነው። ተድላ ባይሩ ግን ባለጋራቸው በፓርላማ ውስጥ ወንበር ይዞ ሲሞግታቸው ማየት ስለሚዘገንናቸው፣ ሕገ መንግሥቱን በመጣስ፣ የወልደአብ ምርጫ የተጭበረበረ ለመሆኑ በቂ ዶክመንት ተገኝቶበታል ብለው፣ በራሳቸው ሥልጣን ውድቅ አደረጉት። የተድላ እርምጃ በዚህ ብቻ አልቆመም። ወልደአብ ወልደማርያም ሕዝቡን እርስ በርሱ የሚያፋጅ፣ በአገሩ ላይ ጸጥታ የሚያደፈርስና ሁከት የሚፈጥር ሴራ ሲያዘጋጁና፣ ወረቀት ሲበትኑ ተደርሶባቸዋል በማለት፣ ከፍ ያለ የወንጀል ክስ መሥርተው ወህኒ ቤት ለመጨመር ፈለጉ። በዚያን ሰዓት ፓርላማው ዝግ ስለነበረ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ የሚፈልጉትን ለማድረግ፣ የአስቸኳይ ጊዜ ሕግ በትዕዛዝ አዋጅ ለማውጣትና ለመፈጸም ሥልጣን አለኝ አሉ። እንግሊዛዊው የሕግ አማካሪያቸው፣ ወልደአብን ለማጥቃት በዚህ መጠቀም እንደማይችሉ አስረዳቸው። የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 77 በትክክል ሲታይ፣

ፓርላማው ለዕረፍት በሚዘጋበት ጊዜ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ፣ ለአንዳንድ አስቸኳይ ጉዳዮች ጊዜያዊ የትዕዛዝ አዋጅ አውጥቶ ከተጠቀመበት በኋላ፣ ከሁለት ወር በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ፣ ፓርላማው እንዲያጸድቀው ማቅረብ አለበት ይላል እንጂ፣ ተድላ እንደሚሉት የፖለቲካ ባለጋራዎቻቸውን በፈለጋቸው ዓይነት እንዲያጠቁ ዲክታተራዊ ሥልጣን አይሰጣቸውም:: መቼም ይህ ሁሉ በቴዎሪ ቢነገርም፣ በዚያን ዘመንና በዚያን ሰሞን፣ በወልደአብ ወልደማርያም ላይ የተፈጸመው ሁሉ፣ ተድላ እንደፈለጉት እንጂ « የማቲየንሶ » ሕገ መንግሥት እንደሚለው አልሆነም::

ይህ በመጋቢት ወር 1953 ዓ.ም በከፊል የሚደረገው የሕዝብ እንደራሴዎች ምርጫ ከተከናወነ ከአርባ ቀናት በኋላ ፓርላማው ሲከፈት፣ የአሥመራን ሕዝብ ሲያተራምስ የሰነበተው የወልደአብ ወልደማርያም ጉዳይ እንዴት እንደነበረ፣ በምን አኳኋን እንደተወሰነ፣ አንድም የሕዝብ እንደራሴ፤ ቺፍ ኤግዜኩቲፉን ለመጠየቅና ክርክር ለመክፈት የፈለገ አልነበረም:: በመሠረቱ በፓርላማው ያሉት፣ የአንድነት ፓርቲዎች ሆኑ የተቃዋሚዎቹ የነ ኢብራሂም ሡልጣን ወገኖች፣ የወልደአብ ወልደማርያም የፓርላማ ወንበር ማጣት፣ ይቆረቁራቸዋል ወይም ያሳዝናቸዋል ተብሎ አይጠበቅም:: በተለይም እስላሞቹ የተድላና የወልደአብ ጠብ ክርስቲያን ለክርስትያን ስለሆነ፣ በዚህ ማህል መግባቱ አይጠቅመንም ባዮች ሆኑ:: ይሁን እንጂ የተድላ ባይሩ የሥልጣን አጠቃቀም፣ ነገ በእነ ኢብራሂም ሡልጣን ላይ የሚደርስ ነው በማለት፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉን ለመውቀስም ሆነ ለማስጠንቀቅ፤ ፓርላማው ሳይነጋገረበት በመቅረቱ ብዙውን ተመልካች አስገርሟል::

## የተከበሩ ስደተኛ

በመጋቢት 14 ቀን 1953 ዓ.ም ለፓርላማ አባልነት በአሥመራ ከተማ ተወዳድረው ያሸነፉት ምርጫ፣ በተጭበረበረ የድምፅ ብልጫ ነው ተብሎ ሲሠረዝባቸው፣ ወልደዓብ ወልደማርያም ከእንግዲህ ወዲህ በኤርትራ ውስጥ፣ የፖለቲካ ሕይወት ለመቀጠል እንደማይችሉ ተገነዘቡ:: ለሕይወታቸውም ምንም ዋስትና እንደሌላቸውና ማናቸውም አደጋ በማናቸውም ሰዓት ሊደርስባቸው እንደሚችል ስለተሰማቸው፣ አገሩን ለቅቆ ወደ ስደት ከማምራት በስተቀር፣ ሌላ መንገድ የለም ብለው እርግጠኛ ሆኑ::

ባለጋራቸው ተድላ ባይሩ፣ በሥልጣን ፈረስ ላይ ሆነው የፈለጋቸውን ስለሚያደርጉ፣ ወልደአብ የኤርትራን መንግሥት መሪ ለመቋቋምና የሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት እንደማይችሉ አወቁት:: ቀደም ሲል ሕይወታቸውን ለማጥፋት ሰባት ጊዜ የተደጋገመ ሙከራ ሲደረግባቸውና፣ በየጊዜው እየቆሰሉ ሆስፒታል ሲተኙ፣ በመጨረሻም ለፓርላማ ተወዳድረው ያሸነፉትን ወንበር ከሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ውጭ ሲታገድባቸው፣ በኤርትራ ያሉት የፖለቲካ መሪዎች ሆኑ የሕዝብ ድርጅቶች፣ ተገን ሆነው ስላልቆሙላቸው፣ ወልደአብ እጅግ የመረረ ሀዘንና ብስጭት አደረባቸው:: ከኤርትራ ወጥተው ወደ ሱዳን ለመሰደድ ስለሚችሉበት ጉዳይ እርዳታ የጠየቁት፣ አሥመራ የሚገኙትን የተባበሩት መንግሥታት ወኪልን እና የአሜሪካንን ቆንስል ነበር::

የተባበሩት መንግሥታት ወኪል በሰጣቸው ምክር፣ ከኢትዮጵያ መንግሥት ፓስፖርትና የመውጫ ቪዛ በኦፊሴል ጠይቀው ካልተከለከሉ በስተቀር፣ በሰውር አገሩን ለመልቀቅ የሚያደርጉት ሙከራ አደገኛ መሆኑን አስጠነቀቃቸው:: ነገር

ግን የኢትዮጵያ መንግሥት፣ የጠየቁትን ያለ በቂ ምክንያት አይቻልም ብሎ ፓስፖርት ከነፈጋቸው፣ የተባበሩት መንግሥታት ወኪል ሌላ ዘዴ ፈልጐ እንደሚረዳቸው ሙሉ ተስፋ ሰጣቸው:: ወልደአብ ይህንን ምክር በመከተል፣ ለፊታውራሪ አስፍሐ ወልደሚካኤል በኤርትራ የግርማዊነታቸው ምክትል እንደራሴ፣ ሰኔ 10 ቀን 1953 ዓ.ም ባቀረቡት ማመልከቻ፣ በሕይወታቸው ላይ የደረሰባቸውን ከባድ ችግር ከተነተኑ በኋላ፣ ወደ ውጭ አገር ተሰደው ለመኖር ፓስፖርትና የመውጫ ቪዛ እንዲሰጣቸው ጠየቁ:: አልሞት ባይ ተጋዳይ፣ አገራቸውን ለቅቀው ስደት መሄድን ሲመርጡና፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መንግሥት ፈቃድ ሲጠይቁ፣ እሳቸው እንዳቀረቡት ምክንያት፣ ለሕይወታቸው ዋስትና ለማግኘት ብቻ ሳይሆን፣ በውጭው ዓለም የፖለቲካ ትግላቸውን ለመቀጠል መሆኑን ለመረዳት አስቸጋሪ አልነበረም::

ፊታውራሪ አስፍሐ የኢትዮጵያና የኤርትራን አንድነት የሚቃወመውንና እያፈነገጠ የሚያስቸግረውን፣ በፖለቲካ ጥበብ ማቃናትና መመለስ ይቻላል ብለው ስለሚያምኑ፣ ለወልደአብ ማመልከቻ መልስ ከመስጠታቸው በፊት፣ ለጃንሆይ አንድ ሀሳብ አቀረቡ:: ወደ ኸተ ልዑል ቤተ መንግሥት በላኩት ማስታወሻ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፤ አውቆ ያጠፋን በመማር፣ የተሳሳተን ወደቀና በማስማራት፣ በመሪነታቸው የሚፈጽሙትን የተቀደሰ ሐዋርያ ተግባር ከዘረዘሩ በኋላ፣ « ወልደአብ ወልደማርያም አዲስ አበባ ተጠርተው የጋዜጣና የማስታወቂያ ምክትል ሚኒስትርነት ቢሾሙ በብዙ ረገድ ልንጠቀምባቸው እንችላለን » አሉ:: ፊታውራሪ አስተያየታቸውን በመቀጠል፣ « ..... አገር ለቅቀው ለመሄድ የጠየቁትን ፈቃድ ብንከለክል፣ በኢትዮጵያ የሰው መብት የማይጠበቅና በኤርትራም፤ ሕገ መንግሥቱ የሰጠው ዲሞክራሲ የማይከበር ነው እየተባለ፣ ለጠላቶቻችን ፕሮፓጋንዳ ምቹ እንሆናለን:: ፓስፖርቱን ሰጥተን ካገር እንዲወጡ ብንፈቅድ ደግሞ፣ ወልደአብ ለፕሮፓጋንዳ ጽሑፍ ዝግጅት ሞያ ስላላቸው፣ በየጠላቶቻችን አገር እየተዘዋወሩ በኤርትራ ጉዳይ እኛን ከማጥቃት እንደማይተኙ ማወቅ አለብን:: ለዚህ ሁሉ መድኃኒት የሚሆነው ለወልደአብ ወልደማርያም ከፍተኛ ኃላፊነት በመስጠት፣ በፖለቲካና በፕሮፓጋንዳ ሜዳ እኛን ለማጥቃት የሚያዘጋጁልንን ብዕር፤ ወደ ጠላቶቻችን አዙረው እንዲዋጉልን ብናደርግ ይሻላል:: ...... » ሲሉ አስፍሐ አስተያየታቸውን ደመደሙ::

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ የምክትል እንደራሴያቸውን ማስታወሻ ከተመለከቱ በኋላ፣ በዚያን ጊዜ ከገንዘብ ሚኒስትርነታቸው ጋር አጣምረው የጋዜጣና የማስታወቂያ መሥሪያ ቤትን ለሚመሩት ላቶ መኰንን ሀብተወልድ « .... አስፍሐ ወልደሚካኤል ይኸን ብርቱ የሆነ አስቸኳይ ሀሳብ አቅርበውልናል:: ያንተን ተናገር ...... » ብለው ላኩላቸው::

ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ፤ ከኤርትራ፣ እንደራሴ ሆነ ከምክትሉ፤ ለሚቀርቡት ጉዳዮች ሁሉ ግምት የማይሰጡ መሆናቸውንና፣ በተለይም ተድላ ባይሩን በወዳጅነት መመልከታቸውን ጃንሆይ ደህና አድርገው ስለሚያውቁ፤ ስለ አስፍሐ ሀሳብ አስተያየታቸውን አልጠየቋቸውም:: መኰንን ሀብተወልድ፣ ጃንሆይ በብዕራቸው የጠቀሱት « ብርቱ የሆነ አስቸኳይ » የሚለው ቃል በአስፍሐ ሀሳብ ለመስማማት ማዘንበላቸውን ስለሚያመለክት፤ የተጠየቁትን ከመመለሳቸው በፊት፣ ስለወልደአብ ጉዳይ የወንድማቸውን ያቶ አክሊሉን ምክር ጠየቁ::

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አስተያየታቸውን ሲሰጡ፣ « ..... ወልደአብ ወልደማርያም በተፈጥሮው " REBELLE " አምቢተኛ የሆነ ሰው ነው:: እንደዚህ የመሳሰሉት ሰዎች ሕይወታቸውን ሙሉ ማንኛውንም ነገር ሲቃወሙ የሚኖሩ ከመሆናቸው የተነሣ፣ አንዳንድ ጊዜ ከመሠረቱ ሲጥሩበት ከነበረው፣ የራሳቸው ከሆነውም ሀሳብ ጋር ሲጣሉ ይገኛሉ:: እኔ ወልደዓብን የማየው በዚህ መልክ ነው:: ስለዚህ በሹመትና በገንዘብ ተደልሎ ኢትዮጵያን ይወዳል፣ ኤርትራ መቀላቀሏን ይደግፋል ብሎ ማሰብ ከንቱ ነው:: ይልቁንም እንሹምህ፣ እንሸልምህ ቢባል፣ ተቃዋሚነቱንና ቁጣቸውን የበለጠ ያጠነክራል እንጂ አይለውጠውም:: እንደ እኔ ከሆነ፣ ከአስፍሐ የቀረበውን ሀሳብ በብዙ ምክንያት ጃንሆይ መቀበል የለባቸውም:: አንተም አጠንክረህ የማይጠቅም መሆኑን ብትነግራቸው ይሻላል ..... » አሏቸው::

አቶ መኰንን ምንም እንኳን ከወንድማቸው የሰሙት፣ ብዙ ነጥብ ያለው ቢሆንም፣ ጃንሆይን እንደዚህ በደረቀ ቃል አይሆንም ማለቱ ስለከበዳቸው፣ አጥጋቢ የሆኑ ምክንያቶችን ለመደርደር ብዙ ተጨነቁበት:: አንድ ሌሊት ሙሉ አውጥተው አውርደው፣ ያገኙትን ሀሳብ ለጃንሆይ ያቀረቡላቸው፣ በሚከተለው መልክ ነበር::

« ...... ኢትዮጵያ ሌላ ነች:: ኤርትራ ልዩ ነች:: ሁለቱም ሕዝቦች አንድ መሆን አይችሉም እያለ፣ የግርማዊነትዎን ድካም ሲቃወም የቆየው ሰው፣ ዛሬ ለጋዜጣና ለማስታወቂያ መሥሪያ ቤት ምክትል ሚኒስትር ሆኖ እንዲሾም የቀረበልዎትን ሀሳብ በጥልቅ አጠናሁት::

...... ግርማዊነትዎ ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ያለማቋረጥ በሚደክሙበት ዘመን፣ አንድነታችንን ለማግኘት እስከሞት እንሰዋለን ብለው፣ ያንን ሁሉ መከራ የሚቀበሉትን የኤርትራ ያገር ፍቅር ሰዎች፣ አቶ ወልደአብ ሲነቅፋቸውና ሀሳባቸውን ሲያወግዝ ከኖረ በኋላ፣ የጃንሆይ ጋዜጣና ራዲዮ ሚኒስትር ሆነ ሲባል፣ ሕዝቡ ምን ይላል ? ብዬ ተጨነቅሁ:: አቶ ወልደአብስ ቢሆን፣ ትናንት አላውቅሽም ብሎ የከዳትን ኢትዮጵያ፣ ዛሬ እናቴ ነሽ ብሎ፣ ልጻፍ ልናገር ቢል፣ ማን ያነብለታል? ማንስ ይሰማዋል ? ..... መቼም ያጠፋ ሰው ምህረት አይገባውም፣ የተሳሳተውም ተመልሶ ቀና መሆን አይችልም አይባልም:: አቶ ወልደአብ እስከዛሬ ባደረገው ከተጸጸተና ወደ ጃንሆይ ልመለስ ብሎ በይፋ ካመለከተ፣ ሥራም ሆነ የኑሮ መደገፊያ በጃንሆይ ቸርነት ሊሰጠው ይገባል:: ነገር ግን ለሹመት የተሰነዘረለት ደረጃ እና የተጠየቀው የሥራ ዓይነት፣ የጃንሆይ ታማኞች የሆኑትን የኤርትራን ያገር ፍቅር ሰዎች በብርቱ ስለሚያሳዝን፣ የማይቻል መሆኑ ለፊታውራሪ አስፍሐ እንዲነገረው፣ ባሪያዎ አስተያየቴን በታላቅ ትህትና አቀርባለሁ ....... »

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ከመኰንን ሀብተወልድ ከቀረበላቸው ሀሳብ ውስጥ አቶ ወልደአብ እስካሁን በሠራው ተጸጽቶ፣ ወደ ጃንሆይ ለመመለስ ካመለከተ የሚለውን ስለተስማሙበት፣ አስፍሐን በስልክ ጠርተው « .... ወልደአብ፣ የምህረት ደብዳቤ በይፋ እንዲጽፍልን አድርግና፣ አዲስ አበባ አስመጥተን አስፈላጊውን እናደርግለታለን ...... » አሏቸው::

• ለፊታውራሪ አስፍሐ፣ « አስፈላጊውን » የሚለው ንጉሣዊ ቃል፣ የጋዜጣና የማስታወቂያ ም/ሚኒስትርነቱን ይሁን፣ ወይም ደግሞ ሌላ ሥራ አልተብራራላቸውም:: ሆኖም ወዲያውኑ አቶ ወልደአብን እቢሮአቸው አስጠርተው፣ ወደ ውጭ አገር ተሰዶ በችግር ከመጠበስ ይልቅ፣ ለደጉ ንጉሠ ነገሥታችን

ችግርዎን አመልክተው አዲስ አበባ ከፍተኛ የሆነ የኃላፊነት ሥራ ቢያገኙ አይሻልም ወይ ? ብለው ጠየቋቸው:: ወልደአብ፣ እምቢ ለማለት የሴከንዶች ጊዜ አልወሰዱም:: አገሩን ለቅቀው ከመሰደድ ሌላ የሚፈልጉት ነገር እለመኖሩን በመሀላ አረጋገጡላቸው::

የግርማዊነታቸው ምክትል እንደራሴ፣ ባለጉዳዩን ሳያማክሩ፣ ሀሳባቸውን በቀጥታ ለጃንሆይ ያቀረቡት፣ ወልደአብ ወልደማርያም ሹመትና ሽልማት ሲሰጣቸው፣ በቀላሉ ወደ ኢትዮጵያዊነት ይመለሳሉ በሚል ተስፋ ነበር:: በመጨረሻው፣ የወልደአብ መልስ ያልጠበቁት ሆኖ ቢያስደነግጣቸውም፤ ፊታውራሪ ዘዴኛና ጌታቸውን የመደሰል ተሰጥዖ ስላላቸው፣ « እምቢተኛው ኤርትራን ለቅቆ መውጣቱ የሚጎዳው ራሱን ነው እንጂ እኛን አይደለም » የሚል ቴዎሪ በመፍጠ ር፣ ፓስፖርትና የመውጫ ቪዛ ለወልደአብ እንዲሰጥ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ አስፈቀዱ::

የወልደዓብ ወልደማርያም ተቃዋሚነት፣ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እና ለአንድነት ተዋጊዎች ሠላም የሚነሳ መሆኑ ቢታመንበትም፣ ተድላ ባይሩ በስውየው ላይ በየጊዜው በወሰዱት የጭካኔ እርምጃ፣ ንጉሠ ነገሥቱ አለመስማማታቸውን፣ አስፍሐ ወልደሚካኤል ያረጋግጣሉ:: ምክትል እንደራሴው፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ በወልደአብ ላይ የሚያደርጉት ሁሉ ትክክል አለመሆኑን በወዳጅነት ለመምከር በሞከሩበት ጊዜ፣ አንዳንድ ትዝ የሚላ
ቸውን እንደሚከተለው ገልጸዋል::

« ...... ፈረስ ጥሎ ይደነግጣል:: አህያ ጥሎ ይረግጣል:: እንደሚባለው ሁሉ፣ አባክዎ ፈረስ ሆነው ይታዩ ? ..... » ብዬ ተድላን ብመክራቸው « አህያ » ብለህ ሰደብከኝ ብለው በጣም ተቀየሙኝ:: እኔም በዚህ ሳልጨነቅ ወልደአብ ከአገር ለመውጣት የጠየቁት ፈቃድ እንዲሰጣቸው ደገፍኩ:: አቶ ተድላ ይህን ሲሰሙ ዱታ ነኝ ብለው እሣት ጉርሰው ሊያነጋግሩኝ መጡ:: እረጋ ብዬ የሚናገሩትን ሳዳምጥ፣ በጠላት ዘመን በጉጃሜዎች የተዘፈነች አንዲት ግጥም ትዝ አለችኝ:: ...... ሰደደኝ አልሰድም፣ ውደደኝ አልወድም፤ እንዴት እኖራለሁ ከዲያቢሎስ ወንድም፤ የሚባለውን አወጋኋቸው:: በዚህም፣ በዲያቢሎስ እስመሰለህ ሰድበሽኛል በማለት የበለጠ ተቆጡ:: እኔ ግን የማምንበትን ቀጠልኩ:: ታላቁ ጌታዬ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቅን ሀሳቤን ያውቁልኝ ስለነበረ፣ የምጠይቀውን ሁሉ አልከለከሉኝም:: በጃንሆይ ፈቃድ የወልደአብ ከአገር የመውጣት ጉዳይ በሠላም በማለቁ በጣም ደስ አለኝ:: ...... »

በሐምሌ 1953 ዓ.ም፣ ሀያ ኪሎ የማይሞላ፣ ለሱዳን ከባድ የሙቀት አየር የሚያገለግሉ ስስ ልብሶች በአንድ መጠነኛ ሻንጣ ቀርቅበው፣ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ለመሣፈር አሥመራ ኤርፖርት ሲጠባበቁ፣ አቶ ገብረአምላክ ኃይሌ የተባለ የቺፍ ኤግዜኩቲፉ ጸሐፊ፣ ስደተኛው ተቃዋሚ መሣፈራቸውን ለማየት መጣ:: አቶ ወልደአብ ጠጋ ብለው የሞቀ ሽላምታ ከሰጡት በኋላ፣ ..... ይኸውልህ ወንድሜ ! እድሜ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴና ለመንግሥታቸው፤ ደንበኛ ፓስፖርት ተሰጥቶኝ አገር ለቅቄ መሄዴ ነው:: ...... እንግዲህ የኔ ጉዳይ አንድ መንገድ ይዟል:: ወደፊት ጊዜው መቼ መሆኑን አላውቅም እንጂ፣ የዛሬዎቹ የኤርትራ መሪዎች እንደ እኔ ፈቃድ ሳያገኙ፣ ተሹለክልከው የሚሸሹ ይኖራሉ የሚል ስሜት አለኝ ...... አሉት:: ገብረአምላክ ኃይሌ በቁጣ ግሉ፣ መራህ መንግሥቴ ተድላን (የመንግሥቱ መሪ ተድላን) ተሳድቧል በማለት፣ የመውጫ ቪዛቸውን በፖሊስ ለማገድ ቀንጣ ቀንጣ አለ:: የቢትወደድ አንዳርጋቸው መሳይ የፀጥታ ሹም እድፍጠ

ይመለከተዋል። የኤርፖርቱ የደለፍ ክፍል በቺፍ ኤግዜኩቲፉ እንደማይታዘዝ ገብረእግዚአብሔር አልገባውም ነበር። ወልደዓብ « የተከበሩ ስደተኛ » ስለሆኑ፣ አገሩን ለቅቀው እስኪወጡ ድረስ መብታቸው የተጠበቀ ነው። ከብዙ ዓመታት በኋላ ቢትወደድ አስፍሐ ይህን ጉዳይ ሲያስታውሱ፣ የወልደዓብ ነቢይነት ደርሰ መታየቱ አስደንቋቸዋል። ወልደአብ ከተሰደዱ ከአሥር ዓመት በኋላ፣ ተድላ ባይሩ ተቃዋሚ ለመሆን አገር ለቅቀው የወጡት፣ በይፋ ሳይሆን ተሸልከው ነበር።

በኤርትራ ጉዳይ የፖለቲካ ትግላቸውን ለመቀጠል በወግ ፈቃድ ተሰጥቷቸው፣ አገር ለቅቀው የወጡት ወልደአብ ወልደማርያም፣ በታሪክ ላይ የመጀመሪያው ስደተኛ ተቃዋሚ ተባሉ። ኤርትራ ከጣልያን ኮሎኒነት ወጥታ ወደ እንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር ከተዛወረችበት ከ 1941 ዓ.ም ጀምሮ፣ በአሥራ ሁለት ዓመታት ውስጥ፣ የወልደአብ ወልደማርያም የፖለቲካ አቋም፣ በአንድ መሠረት ላይ የቆመ እንዳልነበረ ይታወሳል።

ኤርትራ፣ በታሪኳም በባህሏም፣ ከኢትዮጵያ ጋር የተሳሰረች ስለሆነች፣ ለሁለቱ ሕዝቦች አንድነት የቆመውን ያገር ፍቅር ማህበር « እኔ መሠረትኳት » ለሚሉት ምሥክርና ተቀባይ ባይኖራቸውም፣ የማህበሩ ሙሉ አባል ሆነው ለሰስት ዓመታት ማገልገላቸውን የከዳቸው የለም። በመጀመሪያ ለአንድነት ዓላማ የቆምኩ ነኝ ካሉ በኋላ፣ ድንገት ፈንገጥ ብለው፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ውህደት የሚከናወነው በሕግ በተሰመረ ውል መሆን አለበት አሉ። በዚህ ሀሳባቸው የሚከተላቸው ሲያጡ፣ ማህበረ ፍቅሪ ሀገርን ለቅቀው፣ ኤርትራ በእንግሊዝ የሞግዚት አስተዳደር ለአሥራ አምስት ዓመት ከቆየች በኋላ፣ ነፃነቷን ብታገኝ ይሻላል ከሚሉት፣ ከነራስ ተሰማ አስበሮም ጋር ተሰለፉ። በዚህም ዓላማ ረዥም ጉዞ ማድረግ አልቻሉም። ዋና ግቡ ኢትዮጵያን ማጥቃት በሆነው፣ በጣልያን ሊሬ በተጠነሰሰው « የነፃነት ግንባር » በተባለው ፓርቲ፣ ከኢብራሂም ሡልጣን ጋር ተደባልቀው ለኤርትራ ነፃነት ለመጠየቅ፣ ኒውዮርክና ሮም ሲመላለሱ ሰነበቱ። ይህ ሁሉ ድካምና ጥረት ውጤት ሳይሰጥ ቀርቶ፣ ኤርትራ በፌዴራሲዮን ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል የተባበሩት መንግሥታት ሲወስን፣ በሸንበቆ ላይ የተመሠረተው ፓርቲያቸው ተበታትኖ ብቻቸውን ቀሩ። ሆኖም እምቢተኛው ወልደዓብ በዚህ ተስፋ ቆርጠው ለፖለቲካ ውጊያ የታጠቁትን ቀበቶ አልፈቱም። በተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር የተዘጋጀውን የኤርትራን ሕገ መንግሥት ለማጽደቅ፣ በመጋቢት 1952 ዓ.ም የሕዝብ እንደራሴዎች ምርጫ በተደረገ ጊዜ፣ አጭበርባሪዎቹ እነ ኢብራሂም ሡልጣን ተመርጠው የፓርላማ ቦታ ሲይዙ፣ ገትጋታው ወልደአብ ደጋፊ አጥተው እውጭ ቀሩ።

የአቶኖሚው መንግሥት ተቋቁሞ ሥራውን በጀመረ በሰስተኛው ወር፣ ወልደአብ የኤርትራ ሠራተኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ሆነው ሲመረጡ፣ ድርጅቱን የፖለቲካ መሣሪያ አድርገው የቺፍ ኤግዜኩቲፉን ማንቋርጥ ለመያዝ ይበጀኛል ብለው ደስ አላቸው። የባለጋራቸው የተድላ መንግሥት ግን፣ ዴሞክራሲን የሚከተል ነው እንዲባል፣ የወልደአብን መመረጥ ሆነ ብሎ ቢያሳልፈውም፣ በድርጅቱ ውስጥ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ የሚቆጣጠር ወጥመድ ስለዘረጋባቸው፣ በዚህም በኩል የተመኙት ሁሉ ባጭሩ ተቀጠፈባቸው።

ቀደም ሲል « የነፃነት ግንባር » የተባለው የጣልያን ፓርቲ ከተበታተነ በኋላ፣ እነ ኢብራሂም ሡልጣን « የዴሞክራቲክ ግንባር » እያሉ በፓርላማው ውስጥ የሚያንቀሳቅሱት ፓርቲ፣ ደህና መሠረት የሚያስጨብጠው ሰው እግኝቶ

ጉልበት ቢያገኝ፣ ኤርትራን ከፌዴሬሽን ወደ ሙሉ ነፃነት ሊያሻግር ይችላል በማለት፣ ወልደአብ ሌላ አዲስ ተስፋ ቀየሱ:: ከዚህም ግብ ለመድረስ፣ በመጋቢት 53 ዓ.ም በከፊል በሚደረገው የሕዝብ እንደራሴዎች ምርጫ ተወዳድረው አሸናፊ መሆናቸውን፣ ከምርጫው ጣቢያ ሲሰሙ የተሰማቸውን ደስታ ለመለካት አስቸጋሪ ነበር:: ነገር ግን ቀደም ሲል ተዘርዝሮ እንደተገለጸው፣ ባለጋራቸው ተድላ ባይሩ እንኳንስ የፖለቲካ ትግላቸውን ለመቀጠል ዕድል ሊሰጧቸው ይቅርና፣ ሕይወታቸውም በሠላም እንዲቆይ አልተዋላቸውም:: ተድላ ባይሩን የሚያጅቡትም ተቃዋሚዎቻቸው በየጊዜው የለጠፏቸውን የፖለቲካ አቋሞች በመዘርዘር « ወልደአብ በአንድ ራስ አራት ምላስ » እያሉ በየጋዜጣው አወገዟቸው:: ብዙዎቹም የወልደአብን ተቃዋሚነት ሲተርኩ፣ ሥልጣን አጣሁ ብለው በመቆጨት ነው እያሉ ነቅፈዋቸዋል:: እንደ እውነቱ ከሆነ ስለተወው ያንን ሁሉ የፖለቲካ ትግል ሲያደርጉ የኖሩት፣ ለሥልጣን ፍለጋ ነበር የተባለው ትክክለኛ አስተያየት አይደለም:: ወልደዓብ ሥልጣን ፈላጊና ጥቅም አሳዳሪ ቢሆኑ ኖሮ፣ በያለበት ከሚጠነስሱት የተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በሚስለፉበት ጊዜ፣ ለሥልጣን ግንባር ቀደም ለመሆንና ምቾት ያለው ሕይወት ለማግኘት ሲጥሩ በታዩ ነበር:: ለምሣሌ የሊበራል ፕሮግሬሲስት ፓርቲ የተቋቋመው በወልደአብ ጥላንና መሪነት ነው እየተባለ ይነገርላቸዋል:: የዚህ ፓርቲ መሪዎች፣ መርማሪ ኮሚሽን ዘንድ በቀረቡ ጊዜ፣ ታላላቅ ከተባሉት ከእነ ራስ ተሰማ እና ከነ ደጃች አብርሃ ቀጥሎ የዋና ፀሐፊነቱን ደረጃ የያዙት ግራዝማች ስዩም መዓሾ ሲሆኑ፣ የወልደዓብ ስም በአባልነት ደረጃ እንኳን ለመርማሪው ኮሚሽን አልተጠቀሰም:: ከዚያም በኋላ በነፃነት ግንባር ፓርቲ ዘመን፣ በኢብራሂም ሡልጣን መሪነት ወልደአብ ኒውዮርክ ለሙግት ሲመጡ፣ ከዋና ዋና መልዕክተኞች መካከል ወንበር ይዘው አልታዩም:: የቀረው ቢቀር፣ በ1953 ዓ.ም ተቃዋሚው ወልደአብ ወደ አዲስ አበባ ሄደው ከንጉሠ ነገሥቱ ሹመትና ሽልማት እንዲያገኙ ሲመከሩ፤ <u>በህልሜም በውኔም የማላስበው ነው</u> በማለት እምቢ ማለታቸው፣ ለሥልጣንም ሆነ ለጥቅም አለመጓጓታቸውን ያሣያል:: ይልቅስ፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ወልደአብ፣ " REBELLE " ሆነው ስለተፈጠሩ፣ የሚስማሙበትንና የሚያረካቸውን ነገር ሳያገኙ፣ ለምንጊዜም በተቃዋሚነት የሚኖሩ "እምቢተኛ" ናቸው ያሉት፤ ከእምቢተኛው የታሪክ አካሄድ ጋር ሲታይ ትክክለኛ አስተያየት ነው ማለት ይቻላል::

የመጀመሪያው ኤርትራዊ ስደተኛ ሆነው አገር ለቅቀው ሲወጡ፣ ፓስፖርት ሰጥቶ መልካም መንገድ ብሎ፣ በበር ያስናበታቸው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ነው:: ይህን ያደረገው፣ የወልደአብ የፖለቲካ ትግል ምንጊዜም የማይሳካ ነው ብሎ በማመን ይሆን ? ወይስ በውጭው ዓለም፣ በተለይም በእንግሊዞችና በአሜሪካኖች ዘንድ የዴሞክራሲን ሥርዓት አክባሪ ሆኖ ለመታየት ? ትክክሉ የትኛው እንደሆነ ቢትወደድ አስፍሐ ሲጠየቁ፤ የመጀመሪያው መሆኑን አምንበታለሁ ብለዋል:: ጉዳዩን ወደ ኋላ መለስ ብለን ብናስታውስ፣ የግርማዊነታቸው ምክትል እንደራሴ፤ ወልደዓብ አገር ለቅቀው እንዲወጡ የጠየቁት እንዲፈቀድላቸው፣ ለንጉሠ ነገሥቱ ሲያመለክቱ፣ « ..... <u>እምቢተኛው ኤርትራን ለቅቆ መውጣቱ የሚጐዳው ራሱን እንጂ እኛን አይደለም</u> ..... » የሚል ቃል ስለተጠቀሙ፣ ፈቃዱ የተሰጠው በዚህ አስተሳሰብ ነው ማለት ይቻላል::

ታጋይ ወልደአብ ወልደማርያም ለአርባ ዓመታት፣ ከሁሉም ቀደምት ሆነው በባዕድ አገሮች ሲንከራተቱና ሲቃትቱ በቆዩበት ዘመን፤ ለኤርትራ የወደፊት ዕድል በእሳቸው የፖለቲካ እምነት የተቋቋመና በእሳቸው በቀጥታ ተመርቶ፣ አገራቸውን ለነፃነት ያበቃ ድርጅት አለመኖሩ ሳያሳዝናቸው አልቀረም:: ከእሳቸው

በኋላ በውጭው ዓለም ለኤርትራ ነፃነት እንዋጋለን ብለው ከተነሱት ከነ ፀጋዬ ካህሣይ፣ ከነ ዑመር ቃዲ፣ ከነ ኢድሪስ አዱም፣ ከነግልሀ ሳቤህ እና ከሌሎቹም ጋር አለሁ አለሁ ቢሉም በየፖለቲካው ድርጅት ውስጥ ግንባር ቀደም ሆነው ታይተው አያውቁም::

በእሳቸው የፖለቲካ ሕይወት ዘመን የተወለዱት እነ ኢሳያስ አፈወርቅ፣ የራሳቸውን እምነት መሥርተውና ተከታዮች አሰባስበው፣ በዱር በጫካ ተዋግተው የኤርትራን ነፃነት ሲመሠርቱ፣ ወልደአብ ሲመኙት የነበረውን የአገራቸውን የነፃነት ችቦ ለማብራት አልታደሉም::

እምቢተኛው፤ ከአርባ ዓመት ስደት በኋላ ወደ አገራቸው ሲመለሱ፤ « ..... አንቺ መሬት! የዛሬ አርባ ዓመት ለነፃነትሽ መስዋዕት እሆናለሁ ብዬ ስለይሽ፤ ደሜን እያፈሰስኩልሽ ነበር:: ዛሬ ደግሞ ከአርባ ዓመት በኋላ ነፃ ሆነሽ ስመለስልሽ፤ የደስታ እንባዬን አፈስልሻለሁ ..... » ብለው ተናገረው ነበር:: ውለው ሲያድሩና የኤርትራን ሁኔታ ሲመለከቱት፤ ምን ተሰምቷቸው ይሆን ተብሎ ቢጠየቅ፣ ምናልባት ሕይወታቸውን ሙሉ የታገሉበትን የኤርትራን ከኢትዮጵያ መገንጠል ለማየት ከመብቃታቸው በስተቀር፣ እሳቸው በተመኙት ዓይነት የተቋቋመና ለራሳቸውም የሚጠብቁትን ያገኙበት ለላልሆነ፤ ቅሬታና ሀዘን ሳይፈራረቁባቸው አልቀሩም::

የሕይወታቸውም ዘመን ፍጻሜው ላይ ሲደርስ፣ ምንም እንኳን የደረሰባቸውን ሁሉ፣ ተናዝዘው ባይሞቱ፤ ያች የመጀመሪያ እናቴ ነሽ ብለው ኋላ የከዷት ኢትዮጵያ፣ ያች ከጠላቶቿ ጋር ሆነው ሲጐዷት የኖከሯት ኢትዮጵያ፤ እሳቸው በደሏት እንጂ እሷ ምንም ዓይነት በደል እንዳልፈጸመችባቸው፣ ሳይረዱት እንዳልቀሩ ማሰብ ይቻላል::

## ድሮ ዳቦ

በ1953 ዓ.ም የተድላ ባይሩ መንግሥት የተወለደበትን የመጀመሪያውን ዓመት የሚፈጽመው፤ በተደራረቡና እጅግ አስቸጋሪዎች በሆኑ ፕሮብሌሞች ተወጥሮ ነው:: በተለይ የመጋቢትና የሚያዝያ ወራቶች ጨርሶ ፋታ ያልሰጡ ነበሩ::

እየተደራጀና እየተጠናከረ ለመሄድ ከፍ ያለ ጥረት የሚያደርገውን የተቃዋሚውን ክፍል መቋቋም ብቻ ሳይሆን፤ ከደጋፊዎቹ ከአንድነት ወገኖችም ጋር፣ የተድላ መንግሥት ሰምና ወርቅ ሆኖ ለመሥራት አልቻለም:: በዳቦ ላይ ሙልሙል እንደሚባለውም፣ የአዲስ አበባ መንግሥት ደግሞ፣ የፌዴሬሽኑን ሕግና መብት ለይቶ ባለማወቅ ይሁን ወይም በማወቅ፤ በተድላ ባይሩ የሥልጣን ክልል ውስጥ ጣልቃ እየገባ የሚያደርገው ዝብርቅ ተጨማሪ ፕሮብሌም ሆነበት:: በአሥመራ ከተማ « በቆንስል ጄኔራል » ስም ባንዲራ የሚያውለበልቡት የታላላቆቹ መንግሥታት ወኪሎች ደግሞ፤ የዲክታተሩ የተድላ ባይሩ አስተዳደር፣ ግቡ ፌዴሬሽኑን አፍርሶ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ለመገዛት ነው:: ..... » እያሉ፤ ለተቃዋሚዎቹ ድጋፍ በማሳየት አንድ ሌላ ችግር ፈጠሩበት::



ወልደአብ ወልደማርያም ከሠላሳ ስምንት ዓመታት የስደት ዘመን በኋላ ኤርትራ ሲመለሱ፥

*« ...... አንቺ የኤርትራ ምድር ለነፃነትሽ ለመታገል ስሰደድ ደሜን አፍስሼልሽ ነበር። ነፃ ሆነሽ ስመለስ የናፍቆት እንባዬን አፈስልሻለሁ ....... »*

(ሰኔ 1991)

ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ የአንድነት ወገኖች፣ የሰጠነውን ምክርና መምሪያ የተድላ መንግሥት አልተከተለልንም በማለት ቅሬታ ስለአደረባቸው፤ ተቃዋሚዎቹ ከያሉበት የሚያራግቡትን እሣት ለማጥፋት እርዳታ መስጠት አልፈለጉም:: የተድላ መንግሥት ሥራውን ሲጀምር ይህ ሁሉ ጣጣ የደረሰበት፣ መጀመሪያ ከአንድነት ወገኖች አስፈላጊውን ሕብረትና ድጋፍ ባለማግኘቱ፣ ሁለተኛ ከአዲስ አበባ የሚጠብቀው እርዳታ እንደአሰበው ሳይደርስለት በመቅረቱ ነው ብለው የሚያምኑ አንዳንድ ሰዎች፣ አስተያየታቸውን ለንጉሠ ነገሥቱ አቅርበዋል:: ከነዚህም አንዱ፣ በመንግሥቱ ንዋይ ኩ ዴታ ጊዜ የተገደሉት ብላታ ዳዊት ዕቁባእግዚእ፣ በዚያን ጊዜ ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩ ናቸው:: ብላታ ዳዊት አስተያየታቸው ለጃንሆይ እንዲደርስላቸው በሚያዝያ ወር 1953 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ፣ ላቶ መኰንን ሀብተወልድ የገንዘብ ሚኒስትር ባቀረቡት ማስታወሻ የሚከተለውን ገልጸዋል::

« ...... የተድላ ባይሩ መንግሥት እየተዳከመ ሲሄድ የተቃዋሚው ወገን እየበረታ እንደሚሄድ፣ የአንድነት የአገር ፍቅር ማህበር ዋና ዋና አባሎች፣ በተለይም እነ ፊታውራሪ አስፍሐ የተገነዘቡት አልመሰለኝም:: ይህ ጉዳይ አሳሳቢ ስለሆነ፣ አንድነቶች በተድላ አስተዳደር ውስጥ እየገቡ ችግር እንዳይፈጥሩ፣ ልጅ እክሊሉ፣ ለግርማዊነታቸውና ለጸሐፊ ትእዛዝ ደጋግሞ አመልክቶ ነበር:: አሁን ልጅ እክሊሉ በጉዞ ላይ ባለበት በዚህ ሰሞን፣ ሁኔታው እየተባባሰ መሄዱን አይቼ ስለተጨነቅኩ፣ ከዚህ ቀደም እንደማደርገው ሁሉ፣ ያለኝን ቅንና የግል አስተያየት በጌታዬ በኩል ለግርማዊ ጃንሆይ እንዲቀርብልኝ እለምናለሁ:: ...... በእኔ አስተያየት፣ ተድላ ባይሩ ወልደዓብ ወልደማርያም አይደለም:: ከዚህም በላይ አብርሃ ተሰማ ወይም ኢብራሂም ሡልጣን አይደለም:: ተድላ አንድም ጊዜ ሳያመነታ፣ ላንዲት ኢትዮጵያ ከልቡ የታገለና የሠራ መሆኑን በሚገባ ያስመሰከረ ነው:: ከእኔ ጀምሮ እንደማናችንም በአንዳንድ ረገድ የችሎታ እጥረት፣ ወይም የአሠራር ጉድለት የለውም ብዬ አልከራከርም:: ነገር ግን ለፍጹም ኢትዮጵያዊነቱና ለቅን አሳቢነቱ ጥያቄ የለውም ብዬ እቆማለሁ:: ጌታዬ እንደሚያውቁት ምንም እንኳን እንደ አስተዳዳሪ በሥራው አጀማመርና አመራር ብዙ ትችት ቢደርስበትም፣ በጥቂት ቀናት ኤክስፔሪያንስ ተመሥርቶ፣ እጥፊ ነው ብሎ ፍርድ መስጠት ተገቢ አይሆንም:: እኔ እንደዚህ ስናገር፣ ተድላ እስካሁን አንድም ስህተት አልፈጸመም:: ወደፊትም አይሳሳትም ብዬ ቃል ለመስጠት አይደለም:: እኔ የማሳስበው ተድላ በአሁኑ ሰዓት ብዙ ፕሮብሌሞች ስለከበቡት፤ ለአንድ ሰሞን ሠላም አግኝቶ ከችግሮቹ ለመውጣት እንዲችል እርዳታና ዕድል እንዲሰጠው ነው::

...... የአንድነት ሰዎች እየተሰበሰቡ <u>እንምራህ እያሉ ከሚያስቸግሩት፤ እንርዳህ ቢሉት ኖሮ</u>፣ በአሁኑ ሰዓት በኤርትራ ላይ ብዙ የተሻለ ሁኔታ በታየ ነበር:: ጌታዬ እንደሚያውቁት፣ ትናንት በባንዳነት ጠላትን በቅን ያገለግሉ የነበሩት ሰዎች፣ ዛሬ ከንጹህ ኢትዮጵያዊው የበለጠ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ለመታየት የሚያደርጉት ጥረት፣ ሊታመንም ሊደነቅም አይገባም:: የእነዚህ ሰዎች እጉል ጥረት፣ ያ ሁሉ ድካም የተደረገበትን ጉዳይ አደጋ ላይ እንዳይጥለው በቶሎ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል:: ይኸውም፣ 1ኛ/ <u>እነዚህን ፌዴሬሽኑን በችኮላ ለማፍረስ የሚታገሉትን ዋና ዋና ሰዎች ሩጫቸውን እንዲያቆሙ ማገድ</u>፣ 2ኛ/ <u>ፓርላማው በቅርብ ቀን ውስጥ ሲከፈት በጃንሆይ ስም በሚደረገው የመክፈቻ ንግግር፣ የተቃዋሚዎቹ ክፍሎች በያለበት የሚነዙት ወሬ ሁሉ ፈጽሞ መሠረት የሌለው መሆኑን ማረጋገጥ</u>፣ ነው::

እስካሁን ድረስ ልጅ አክሊሉ ደጋግሞ ያመለከተው፣ ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስም ከሙሉ ድጋፍ ጋር ያደረጉት ጥረት፣ በእነ ቢትወደድ አንዳርጋቸውና በእነ ፊታውራሪ አስፍሐ ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም ብዬ ደፍሬ ለመናገር በቅቻለሁ:: ስለዚህ፣ ለችግሩ መድኃኒቱን መስጠት የሚችሉት በቀጥታ ራሳቸው ጃንሆይ ብቻ ስለሆኑ፤ ጌታዬ ባለዎት ዘዴና መንገድ አስረድተው እንዲያስወስኑ፣ ከልብና ከንጹህ ኢትዮጵያዊ መንፈስ ጋር አመለክትዎታለሁ:: ... »

ይህን የብላታ ዳዊትን ማስታወሻ አቶ መኮንን ሲደርሳቸው የወሰዱት እርምጃ ምን እንደሆነ፣ የሚያመለክት መረጃ አልተገኘም:: ሆኖም የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትሩ፣ በጊዜው ላይ ያለው የኤርትራ ሁኔታ ምን ያህል አስጊ መሆኑን ብቻ ሳይሆን፣ የነ ፊታውራሪ አስፍሐም አቋም አደገኛነቱን ገልጠው አስተያየታቸውን ስለሰጡ፣ መኮንን ሀብተወልድ ባላቸው ልዩ አቀቤ ሰዓት ለጃንሆይ አቅርበው ማስረዳታቸውና አንዳንድ እርምጃዎች እንዲወስዱ ማድረጋቸው የማይጠረጠር ነው::

ከየካቲት እስከ ግንቦት 1953 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ መንግሥታቸውን ያጠነከሩና ያስከበሩ መስሏቸው፣ ኃይልን በመጠቀም በወሰዷቸው እርምጃዎች፤ ከወገኖቻቸው አንዳችም ድጋፍ አለማግኘታቸው እጅግ አሳዝኗቸዋል:: ቀደም ባለው ምዕራፍ በሰፊው እንደተገለጸው፣ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 46 የተደነገገውን ጥሰው፣ የወልደዓብን የፓርላማ ምርጫ ውጤት ሲሰርዙ፣ ሕገ ወጥ የሆነ የዲክታተር ተግባር ነው እያሉ በሰፊው የተቿቸው፣ ከተቃዋሚዎቹ አባሎች ይልቅ የአንድነት ወገኖች ነበሩ::

በዚሁ በመጋቢት ወር "SWAT - ERITREA" የተባለው በትግሪኛና በዓረብኛ የሚታተመው ጋዜጣ፣ የነ ኢብራሂም ሡልጣንን ፕሮፓጋንዳ በሰፊው በመደገፍ፣ የአገሩን ሠላም የሚያደፈርስ ጽሑፍ አትሟል በማለት ፖሊስ ልከው ሲዘጉት፤ ከአንድነት ወገኖች፣ ተድላ የሠራኸው የሚገባ ነው ብሎ የደገፋቸው አንድም ሰው አልነበረም:: " SWAT-ERITREA " በአቶ ተድላ ትእዛዝ ከመዘጋቱ በፊት፣ ለመጨረሻ ጊዜ አትሞ ያወጣው ጽሑፍ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት በአሠራሩ ፌዴሬሽኑን በማፍረስ ላይ ነው በማለት፣ እነ ኢብራሂም ሡልጣን እና እነ ዑመር ቃዲ ለተባበሩት መንግሥታት ያቀረቡትን ማመልከቻ ነበር:: የተድላ ባይሩ መንግሥት በተቋቋመ በስድስተኛው ወር፣ የተቃዋሚዎቹ ወገኖች ለተባበሩት መንግሥታት፣ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ያቀረቧቸው ክሶች ዋና ዋናዎቹ ነጥቦች የሚከተሉት ነበሩ::

« ..... በተባበሩት መንግሥታት ጥረትና ዝግጅት መስከረም 11 ቀን 1952 ዓ.ም የጸደቀው የኤርትራ የፌዴራል አክትና ሕገ መንግሥት፣ በተግባር ላይ መዋል አልቻለም:: ..... የኢትዮጵያ መንግሥት ለኤርትራ በሕግ የተሰጠውን የአስተዳደር መብት ነጥቆ፣ በቀጥታ የራሱን ሥልጣን በማስፈጸም ላይ ይገኛል:: ...... በኤርትራ መንግሥት የሥልጣን ክልል ውስጥ የሚገኙትን ስድስት ዋና ዋና የሥራ ዘርፎች፤ ኤርትራውያኖች ሊያካሂዱት ሲገባ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት በሥልጣኑ ከአዲስ አበባ ስድስት አማሮች መርጦ በመሾም በየመስኩ መድቧቸዋል::

| | |
|---|---|
| 1. ለፊናንስ | አቶ ሠይፉ ገብረዮሐንስ |
| 2. ለፖስታና ለመገናኛ | አቶ በፈቃዱ ወልደሚካኤል |
| 3. ለውጭ ንግድ | አቶ ፋንታዬ ወልደዮሐንስ |

4. ለምድብ — አቶ አበበ ቢተው (ኋላ ፊታውራሪ)
5. ለጉምሩክ — አቶ ተክሉ ድልነሣው
6. ለባቡር — አቶ ያዕቆብ ዛኒዖስ

...... እነዚህ ባለሥልጣኖች ቺፍ ኤግዚኩቲፉ ለመንግሥቱ እመራር ከሾማቸው ሴክሬተሪዎች (ሚኒስትሮች) የበለጠ ሥልጣን ይዘው ትዕዛዙን በቀጥታ ከአዲስ አበባ እየተቀበሉ የፈለጉትን በማድረግ ላይ ናቸው።

...... በተጨማሪ ደግሞ፣ የአቶኖሚውን ሕግ በመጣስ፣ ፓርላማው ሳይመክርበትና ሳያውቀው፣ በኤርትራ ላይ የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲቋቋም፤ ንጉሠ ነገሥቱ በሥልጣናቸው አውጀዋል። ...... እኛ የኤርትራ ሕዝብ እንደራሴዎች፤ ለኤርትራ ሕዝብ የተሰጠውን ነፃነትና የእስተዳደር መብት አለአግባብ በመግፈፍ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚፈጽምብንን ግፍ፣ የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ልኮ እንዲያይልን፣ ይህም የማይቻል ከሆነ መልዕክተኞቻችን በጉባኤው ላይ ተገኝተው ለማስረዳት እንዲፈቀድላቸው እንለምናለን ..... » የነ ኢብራሂም ሡልጣን ወገኖች ላቀረቡት ለዚህ ማመልከቻ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እንዳችም አርምጃ አልወሰደበትም። ከኢትዮጵያም በኩል ነገሩን በዝምታ ከማሳለፍ በስተቀር፣ ማስተባበያ ለመስጠት አልተፈለገም።

ከየካቲት መጀመሪያ አንስቶ ለዕረፍት የተዘጋው የኤርትራ ፓርላማ፣ የሁለተኛውን ወቅት ሥራውን ለመጀመር በመጋቢት ወር እጋማሽ ላይ መከፈት ሲገባው፤ በቺፍ ኤግዜኩቲፉ ሥልጣን እስከ ሚያዝያ 27 ቀን ድረስ እንዲቆይ ተደረገ። ተድላ ባይሩ የፓርላማው ሕንፃ በመታደስ ላይ ነው በሚል ሰበብ ይህን ያህል ጊዜ ያዘገዩት፣ ይጠቅመኛል ብለው በሚያስቡት በሁለት ምክንያቶች መሆኑን፣ የእንደራሴው ጽሕፈት ቤት ለንጉሠ ነገሥቱ ባቀረበው ራፖር አስረድቷል። ይኸውም 1ኛ/ በተሠረዘው በወልደአብ ወልደማርያም ምርጫ እና፤ በተዘጋው የ " SWAT-ERITREA " ጋዜጣ ምክንያት፣ ከመጋቢት 15 ቀን ጀምሮ በአሥመራ ከተማ አጅግ እየተሟሟቀ የሚነፍሰው ወሬ፣ ሚያዝያ ሲጋመስ ሊበርድ ይችላል ብሎ ተስፋ በማድረግ፤ 2ኛ/ በሚያዝያ ወር መጨረሻ ሰሞን፣ የእስላሞች የረመዳን ጾም ስለሚገባ፣ በፓርላማው ውስጥ ለረዥም ሰዓቶች ብዙ ክርክር እንዳይቀጥል፣ በየዕለቱ አኩለ ቀን ላይ እስላሞቹ የሚያደርጉት ስላት (ስግደት) ያቋርጠዋል በማለት ነው። በዚህ አኳኋን ቺፍ ኤግዜኩቲፉ፣ ከወዳጃቸው ከፓርላማው ፕሬዚዳንት ከዓሊ ሙሣ ራዳይ ጋር ሆነው፣ ምክር ቤቱ ሲከፈት ከየአቅጣጫው የሚነሳባቸውን ጦርነት በቆራጥነት እንገጥማለን ብለው ሲዘጋጁ ሰነበቱ።

ምክር ቤቱ በወግ የሚከፈተው በንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ ስለሆነ፣ ሚያዝያ 27 ቀን 1953 ዓ.ም ከእኩለ ቀን በፊት በአምስት ሰዓት፣ ከፍ ያለ ሥነ ሥርዓት በተዘረጋበት በፓርላማው አዳራሽ፣ ቢትወደድ እንዳርጋቸው መሣይ ያደረጉት የዘውድ ዲስኩር፤ <u>ከሚጠበቀው በላይ የተድላ ባይሩን ፍላጐት የሚያሟላ ሆኖ ተገኘ።</u>

በአንዳንድ ቦታዎች፣ መሠረት የሌላቸው የፈጠራ ወሬዎች የሚነዙ መሆናቸውን ቢትወደድ አንዳርጌ ከጠቀሱ በኋላ፤ ..... <u>የኤርትራ ፌዴሬሽን</u>

አስተዳደር ምንጊዜም የማይዳከምና፣ ያለ ኤርትራውያኖችም ፈቃድ ማንም ሊነካው የማይችል መሆኑን፣ በንጉሠ ነገሥቱ ስም አረጋገጡ። .......

የኤርትራ ተቃዋሚዎች ድርጅት ነን የሚሉ አንዳንድ ሰዎች፣ ለተባበሩት መንግሥታት ላቀረቡት ስፊ የክስ ማመልከቻ፣ ቢትወደድ በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ መልሱን ሲሰጡ፣ ..... ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለኤርትራ አስተዳደር የተሰጠው ሕገ መንግሥት ተከብሮ፣ ለሕዝቡ ደህንነትና ብልፅግና ፍሬያማ ውጤት እንዲሰጥ፣ ጽኑ ምኞታቸው ብቻ ሳይሆን፣ ስፊ ቸርነታቸውንም የሚለግሱ መሆናቸውን አስገነዘቡ። ከዚህም ጋር አያይዘው፣ የፌዴሬሽኑ አስተዳደር ከተጀመረ አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ባሉት ስድስት ወራቶች ውስጥ፣ በግርዊነታቸው ልዩ ትዕዛዝ ለኤርትራ ሕዝብ ሊገት ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር (በዚያን ጊዜ U.S.D 1,400,000) እርዳታ መስጠቱን አስታወቁ። ይህም ገንዘብ፣ 1ኛ/ በባቡር ትራንስፖርት ላይ ለደረሰው የበጀት እጥረት ማሟያ፣ 2ኛ/ ለትምህርት ቤቶችና ለሆስፒታሎች ማሠሪያ፣ እንዲሁም ለአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናትና መስጊዶች መጠገኛ እንዲሆን መደልደሉን ዘረዘሩ። ከዚህም በቀር የኤርትራ መንግሥት በሚያደርገው ጥረት የአገሩ ኤኮኖሚ እስከሚሻሻልበት ጊዜ ድረስ፣ ለዚህ ዓመት የንጉሠ ነገሥቱ የጦር ሚኒስትር አንድ ሺህ (1000) ኤርትራውያን ለውትድርና ሞያ እንዲቀጥር ከጃንሆይ መታዘዙን ገለጹ።

ቢትወደድ እንዳርጋቸው ንግግራቸውን በመቀጠል፣ የውጭ ጠላቶች፣ አንዳንድ ያገር ውስጥ ተንኮለኞችን በገንዘብ እየደለሉ የሚያስራጪቸው ወሬዎች ሁሉ፣ ምን ያህል ከእውነት የራቁ ለመሆናቸው በማስረጃ ጠቀሱ።

« ....... ኤርትራ ወደ እናት አገሯ በመመለሷ፣ በኤርትራ ውስጥ የሚኖሩት ጣልያኖች በሙሉ ለቅቀው ይወጣሉ ተብሎ በስፊው መወራቱን የሚክድ የለም። ይኸው ካለፉት ስድስት ወራቶች ጀምሮ እንደ አተኮርነው፣ እስከ ዛሬ ድረስ አንድም ጣልያን አገሩን የለቀቀ ወይም ለመልቀቅ ሻንጣውን የቀረቀበ አላየንም። ቀጥሎ ደግሞ፣ ከጣልያኖችና ከኤርትራውያኖች የተወለዱት ቁጥራቸው እስከ ሀያ ሺህ የሚደርሰው (20.000) ክልሶች፣ የኢትዮጵያ መንግሥት በሚፈጥርባቸው ችግር ምክንያት፣ የዜግነታቸው ጉዳይና የወደፊት መኖሪያቸው እጅግ አሳሳቢ ነው ተብሎ፣ በስፊው ሲተችበት እንደነበረ እናስታውሳለን። ካለፉት ስድስት ወራቶች ጀምሮ፣ እነዚሁ ክልሶች የጣልያንን ወይም የኢትዮጵያን ዜግነት መርጠው በሚፈልጉበት አገር እንዲኖሩ ዕድሉ ስለተሰጣቸው፣ እስካሁን ድረስ ወደ ጣልያን ዜግነት ያመሩት፣ ቁጥራቸው ከሁለት ሺህ መብለጥ አልቻለም። የቀሩት አስራ ስምንቱ ሺህ ግን፣ ኢትዮጵያዊነትን ስለመረጡ፣ የሠላምና የነፃነት ኑሮአቸውን እንዲጀምሩ መንገዱ ተከፍቶላቸዋል። እነዚህ ክልሶች በሙሉ፣ ከእነሱም ጋር የጣልያን ወታደሮች ሆነው ያገለገሉት ጡረተኞች፣ ኤርትራ ተመልሳ የጣልያን ቅኝ ግዛት እንድትሆን ምን ያህል የታገሉ እንደነበሩ፣ የአገሩም ሆነ የውጭው ዓለም ሕዝብ በትክክል ያስታውሰዋል። ...... ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በስብዓዊ አመለካከታቸው፣ ከዚህ ቀደም ለፋሽስት ርዝራዦች እንዳደረጉት ሁሉ፣ ዛሬም በእነዚህ የባለጋራችን ወገኖች በነበሩት ሰዎች ላይ፣ አንዳችም የቂም በቀል አስተያየት እንዳይሞከርባቸው በሰጡት ጥብቅ ትእዛዝ መሠረት፣ ዛሬም ሆነ ነገ የእነዚህ ሰዎች መብት በሚገባ እንደሚጠበቅላቸው እናረጋግጣለን ...... »ቢትወደድ እንዳርጋቸው መሣይ ንግግራቸውን ሲፈጽሙ፣ የኤርትራ ፌዴሬሽን አስተዳደር ተከብሮ እንዲቀጥል የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት መሠረታዊ ዓላማ መሆኑን

ዐድጋሚ [illegible] በኋላ፣ « ...... ለዚች አገር የወደፊት ሕይወት የሚጠቅማትን ለይቶ [illegible]ብንላት፣ የኤርትራ ሕዝብ ብቻ ነው...... » ብለዋል::

ፓርላማውን ለመክፈት አርባ አምስት ደቂቃ የፈጀው የዘውድ ዲስኩር፣ በዚያን ሰዓት በተድላ ባይሩ መንግሥት ላይ የወደቀውን ችግር ለማቃለል፣ ተጠንቶ የተዘጋጀ መሆኑን ያሣያል:: የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት፣ የኤርትራን ፌዴሬሽን ማንም ሊያፈርሰው እንደማይችል ከማረጋገጡም በላይ፣ ለኤርትራ ልማት በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር መስጠቱ ሲነገር፣ ተቃዋሚዎቹ ምንም እንኳን ደስታቸውን በጭብጨባ ይገልጣሉ ተብሎ ባይጠበቅ፣ በጃንሆይ መንግሥት ላይ ለማልቀስና ከፍተኛ ሮሮአቸውን ለማሰማት ያሰቡትን፣ ይህ የዘውዱ ዲስኩር ዕድል ሳይሰጣቸው ቀረ::

የፓርላማው መክፈቻ በዓል ላይ ተካፋይ የሆኑት፣ የኤርትራን ጉዳይ በጥብቅ የሚከታተሉት የታላላቅ መንግሥታት ቆንስሎችም፣ የቢትወደድ አንዳርጋቸው መሣይ የዘውድ ዲስኩር፣ ለተቸገርንባቸው ጉዳዮች ለዋና ዋናዎቹ፣ መልስ አግኝተንበታል በማለት መደሰታቸውን ገለጡ:: የአንድነት አጥባቂ ወገኖችም፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለኤርትራ ሕዝባቸው ልማት የገንዘብ እርዳታ በመስጠታቸውና እንዲሁም በኢትዮጵያ ጦር ውስጥ አንድ ሺህ ኤርትራውያኖች እንዲቀጠሩ በማዘዛቸው ሲደሰቱ፣ የኤርትራ ፌዴሬሽን ተከብሮ እንዲቆይ ይደረጋል የተባለው መልዕክት፣ ከዕምነታቸው ጋር የሚሄድ ሆኖ አላገኙትም::

ተድላ ባይሩ እና ዓሊ ራዳይም፣ 1ኛ/ በወልደዓብ ጉዳይ ሆነ በ "SAWT" ጋዜጣ ምክንያት በምክር ቤቱ ከፍ ያለ ትርምስ ሊፈጠር ይችላል ብለው የፈሩት ምንም ሳይደርስ በመቅረቱ፣ 2ኛ/ የኢትዮጵያ መንግሥት ተድላን አስገብሮ ፌዴሬሽኑን ሊያፈርስ ነው ለተባለው ወሬ፣ ሕገ መንግሥቱ እንዲከበር የዘውዱ ዲስኩር ዋስትና በመስጠቱ፣ በጠላቶቻችን ላይ ትልቅ ድል መታን ብለው ፈነደቁ:: የዘውዱ ዲስኩር <u>መንግሥቱ ተድላን</u> የሚደግፍና የተቃዋሚዎቹን ዕቅድ የሚያከሽፍ ሆኖ ጥሩ ውጤት የሰጠው፣ በጽሕፈ ትእዛዝ ከፍተኛ እርዳታ ስለሆነ፣ ከእንግዲህ ወዲህ « ዕድሜ ለወልደጊዮርጊስ » የአንዳርጌንና የአስፍሐን ተንኮል ለመስበር አቅማችን ብርቱ ነው፤ በማለት ተድላና ዓሊ ሞራላቸውን አዳበሩ::

እዚህ ላይ፣ ብላታ ዳዊት እቁበእግዚእ ከሶስት ሳምንት በፊት በአቶ መኰንን ሀብተወልድ በኩል፣ ለጃንሆይ እንዲቀርብላቸው የገለጹት አስተያየት ሊታወስ ይገባል:: የተድላን ካቢኔ ለማዳን፣ የጽሕፈ ትእዛዝ ሙሉ ድጋፍና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጥሬት ተቀባይነት አለማግኘቱን ከገለጹ በኋላ፣ <u>ዳዊት እቁበእግዚእ፣ ለችግሩ መድኃኒቱን መስጠት የሚችሉት ራሳቸው ጃንሆይ ብቻ ናቸው ብለዋል::</u> በመጨረሻ ተድላ ባይሩ የተደሰቱበት ውጤት እንዴት እንደተገኘ፣ ጥቂት ምርምር ሲደረግ፣ « የወልደጊዮርጊስ ድጋፍ » ነው ብሎ መቆም አልተቻለም:: በ 1993 ዓ.ም ስለዚሁ ጉዳይ ቢትወደድ አስፍሐ ሲጠየቁ፣ « ... <u>ምንም እንኳን የብላታ ዳዊትን አይገቡ ገብቶ ትችት የሰማሁት፣ በጭምጭምታ ሆኖ ትክክለኛ ዝርዝሩን ባላውቀውም፤ የዚያን የ1953 ዓ.ም የፖርላማ መክፈቻ ዲስኩር ጃንሆይ ራሳቸው ይከታተሉት እንደነበረ፣ ዝግጅቱም የተከናወነው አዲስ አበባ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል መሆኑን አስታውሳለሁ</u> ...... » ብለዋል:: ስለዚህ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በታማኛቸው በመኰንን ሀብተወልድ በኩል የቀረበላቸው የዳዊት እቁበ እግዚእ ሀሳብ፣ ጠቃሚ ሆኖ

አግኝተውት በዚሁ እንዲፈጸም ትእዛዝ ባይሰጡ ኖሮ፣ « የኤርትራን ፌዴሬሽን ማንም አይነካውም » የሚለው ቃል በዲስኩሩ ውስጥ አይገለጽም ነበር።

ለብዙ ጊዜ ተዘግቶ የከረመው የሕዝብ ምክር ቤት፣ ያለአንዳች ችግር በሥርዓትና በወግ በመከፈቱ፣ ተድላ ባይሩ ቢደሰቱም፣ በመንግሥታቸው አመራር ላይ የተከማቹት ፕሮብሌሞች ሁሉ መፍትሔ አገኙ ማለት አልነበረም።

ለፓርላማው የቀረበው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሣዊ መልዕክት፣ ባንድ ወገን ለተድላ ባይሩ መንግሥት ድጋፍ ሰጭ ሆኖ ቢታይም፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ፣ በተሰጠው የሕገ መንግሥት ሥልጣን ላይ፣ ከኢትዮጵያ በኩል ምንም ዓይነት እንቅፋት እንደሌለበት አጋልጦታል። ከዚህም በላይ፣ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ፌዴሬሽኑን ጠባቂ፣ የሕዝቡን የዴሞክራሲ መብት አክባሪ፣ ሆኖ በይፋ ቀርቧል። እንግዲህ የኢትዮጵያ አቋም እንደዚህ ከሆነ፣ የተድላ ባይሩ ችግር እምን ላይ ነው ? እያሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች ማውጠንጠን ጀመሩ። ብዙዎቹ በተለይም ሞዴሬቶቹ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ በችሎታ እጥረትና በመንፈስ ደካማነት ካልሆነ በስተቀር፣ የኤርትራ ሕገ መንግሥት የሰጠውን መብት ተከትሎ አገሪቱን በሚገባ ለመምራት፣ የሚቸገርበት ምክንያት አይታየንም አሉ። በአሥመራ ያሉት የታላላቆቹ መንግሥታት ቆንስሎችም፣ ፓርላማው ሲከፈት የተሰጠው ንጉሣዊ መግለጫ፣ ምንም እንኳን ልባዊነቱን በአንዳንድ ረገድ ቢጠራጠሩም፣ ከእንግዲህ ወዲህ የተድላ ባይሩ ካቢኔ ሕገ መንግሥቱን ተመርኩዞ፣ በሥልጣን ለመሥራት መቁረጡን ካላሳየን፣ እንዲሁ በደፈናው ችግር አለብኝ ማለት በቂ አይደለም፣ የሚል አስተያየት ያዙ።

ተቃዋሚዎቹ የእሥላም ሊግ አባሎችም፣ ምንም እንኳን በረመዳን ጾም በተዳከመው ድምፃቸው ብዙ ለመጮህ ባይችሉም፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ፌዴሬሽኑን በአሠራር ዘዴ ለመሠረዝ ጥረቱን እንደቀጠለ ነው የሚል እምነታቸውን አልተዉም።

ዋና ዋናዎቹ የአንድነት አጥባቂ ወገኖችም፣ ለጊዜው የገነተ ልዑል ቤተ መንግሥትን አዝማሚያ እየተከተሉ ፀጥ ያሉ መስለው ቢታዩም፣ የፌዴሬሽኑ ሕይወት እየረዘመ፣ በዚሁ አሠራር የተድላ መንግሥትም እየጠነከረ እንዲሄድ፣ ከእምነታቸው ውጪ ስለሆነ፣ ድጋፍ ለመስጠት አይሞክሩም።

እነዚህን በመሳሰሉ ችግሮች፣ ድሮ ዳቦ ሆኖ ከየአቅጣጫው እሣት የሚነድበት የተድላ ባይሩ መንግሥት፣ የሚያዝያን ወር በሥጋት ጨርሶ፣ ግንቦትን በሠላም ለመፈጸም ሲያልም፣ ባልጠበቀው ሰዓት የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ሳያማክረው፣ ወይም ቢያንስ ቀደም አድርጎ ሳያስጠነቅቀው፣ አንድ ተጨማሪ የፖለቲካ ችግር የሚፈጥር ውሳኔ ወረወረበት። ይኸውም የፌዴራል ክሶችን በይግባኝ እያየ ፍርድ የሚሰጥ የከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ በኤርትራ ተቋቁሞ እንዲሠራ መደረጉን የሚያበስረው ዜና ነበር።

በመሠረቱ የፌዴራሉ መንግሥት የሆነው ኢትዮጵያ፣ ይህንን የከፍተኛ ፍርድ ቤት አሥመራ ላይ ማቋቋሙ፣ የኤርትራን የአቶኖሚ ሥልጣን በቀጥታ የሚነካ አለመሆኑን ተድላ ባይሩና ዓሊ ሙሣ ራዳይ ይገነዘባሉ። ነገር ግን፣ 1ኛ/ ለወጉም ሆነ ለሥርዓቱ በሕግ የተቋቋመው የኢትዮጵያና የኤርትራ ፌዴራል ካውንስል ሳይመከርበት፣ 2ኛ/ ስለ ፍርድ ቤቱ ሥልጣንና አሠራር በሕግ አዋቂዎች

ተዘጋጅቶ ለሕዝቡ ተብራርቶ ሳይገለጽለት፣ 3ኛ/ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ጉዳዩ በቅድሚያ ተነግሮት፣ ተቃዋሚዎቹን ለመከላከያ አስፈላጊውን ዝግጅት ሳያስናዳ፣ በድንገት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የመቋቋሙና የመክፈቻው በዓል በአንድነት ተጣምሮ በመደረጉ፣ ተድላንና ካቢኔውን እጅግ አድርጐ አሳዘነ:: ከዚህ ቀደም ሲል የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በኤርትራ ላይ ስለሚያቋቁመው ስለዚሁ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ በነጋሪት ጋዜጣ መታወጁ በተሰማ ጊዜ፤ የተቃዋሚው ክፍል ለተባበሩት መንግሥታት ካቀረባቸው ክሶች ውስጥ፣ አንዱ አርእስት እንደነበረ ይታወሳል:: የግርማዊነታቸው እንደራሴም ሚያዝያ 27 ቀን 1953 ዓ.ም ፓርላማውን በከፈቱበት ጊዜ ስለዚሁ ጉዳይ አንስተው ሲናገሩ፣ « ..... <u>በኤርትራ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ለማቋቋም የታሰበው፤ አንዳንድ ተቃዋሚዎች እንደተናገሩት ከሕግና ከሥርዓቱ ውጪ ሆኖ የአቶኖሚውን መብት የሚነካ አይደለም:: ..... የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ ፍርድ ቤት መቋቋም፣ ከተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ እና፣ የፌዴራሉን አክት ተመርኩዞ ከወጣው የንጉሠ ነገሥቱ አዋጅ ጋር የሚግባባ መሆኑ ስለተረጋገጠ፤ የታሰበው ከሕግ ውጭ ነው ማለት አይቻልም:: .... ሆኖም፣ ይህ ፍርድ ቤት የሚከፈተው የኢትዮጵያና የኤርትራ የሕግ አዋቂዎች ከመከሩበት በኋላ ነው</u> ...... » ሲሉ ማረጋገጫ ሰጥተው ነበር::

ይህ ቃል በተነገረ በሶስተኛው ሳምንት፣ የተሰጠው ተስፋ ሁሉ ተዘንግቶ ምንም ዓይነት ምክክር ሳይደረግበት፣ በጥድፊያ የከፍተኛው ፍርድ ቤት መክፈቻ በዓል በእንደራሴው ተዘጋጅቶ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ በእንግድነት እንዲጋበዙ ጥሪ ደረሳቸው:: ይህ ድርጊት የተፈጸመባት ያች የግንቦት 15 ቀን 1953 ዓ.ም ምሽት፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉን ምን ያህል እንዳበሳጨች መገመት ይቻላል:: ከአዲስ አበባ ውሳኔ ይበልጥ፣ በእንደራሲው በቢትወደድ አንዳርጋቸውና በምክትላቸው በፊታውራሪ አስፍሐ የተፈጸመው ሥራ፣ ተገቢ አለመሆኑን የታዘቡና ያዘኑ፣ ተድላ ባይሩ ብቻ አልነበሩም::

መቼም በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ የነበረው አሠራር፣ ትክክለኛ ምሥጢሩና ግቡ ምን እንደሆነ በቀላሉ ለመረዳት ያስቸግራል:: በግንቦት 15 ቀን ተድላ ባይሩን የሚያበሳጭና የሚያሳዝን ሥራ ከተሠራ በኋላ፣ «ይውጋህ ብሎ ይማርህ» እንደሚባለው ዓይነት፣ በማግሥቱ <u>ግንቦት 16 ቀን 1953 ዓ.ም በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መልካም ፈቃድና ትዕዛዝ፣ አቶ ተድላ ባይሩ « ደጃዝማች » ተብለው የኢትዮጵያን የክብር ኮከብ ታላቅ ኮርዶን ኒሻን አነገቱ::</u> ይህ ከፍተኛ ሹመትና ሽልማት ተደራርቦ በአንድ ጊዜ ከስለሞናዊው ዙፋን የወረደላቸው ተድላ ባይሩ፤ ሀዘናቸውን በደስታ ለመለወጥና ብስጭታቸውን አውልቀው ለመጣል፣ ብዙ ችግር አላጋጠማቸውም:: በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ልዩ ትዕዛዝ፣ ከአቶነት በአንድ ጊዜ ደጃዝማችነትን የተጐናጸፈው የመጠሪያ ስማቸው፣ ከትከሻቸው እስከ ወገባቸው የሚንዠረገገው ታላቁ ኒሻናቸው፣ ክብሩ ለተድላ ብቻ ሳይሆን፤ ለኤርትራ ሕዝብ ጭምር ነው በሚል ስሜት እጅግ ተደሰቱ::

ሹመት ያዳብር ለማለት እቤታቸው ከመጡት ታላላቅ ሰዎች መካከል፣ ማዕረጉ « <u>የራስነት</u> » መሆን ነበረበት የሚሉ አንዳንድ ሰዎች ቢኖሩም፣ አብዛኛዎቹ ደጃዝማችነቱ ትልቅ ሹመት ነው ብለው ደስታቸውን ገልጸውላቸዋል:: ተድላም ከራስ በፊት ደጃዝማችነት መቅደም እንዳለበት ተገንዝበዋል::

# ደጃዝማች ፌዴራሊስት

የኢትዮጵያና የኤርትራ መቀላቀል የመጀመሪያው ዓመት በዓል በሚከበርበት ዋዜማ ሰሞን፣ « የመንግሥቲ ተድላ » አቋምና አሠራር ፌዴሬሽኑን ሕያው አድርጐ ለማኖር ፈልጓል ፀማለት፣ የአንድነት አጥባቂ ወገኖች ሥጋት አደረባቸው:: የፌዴሬሽኑ አስተዳደር ፀቀየ ቁጥር ሕዝቡ ነገሩ እየገባው፣ ከሌላው ኢትዮጵያ የተሻለ ዴሞክራቲክ የሆነ ሕገ መንግሥት አለን ብሎ ለማሰብ እንደሚችልና፣ ኋላ ለማፍረስ አስቸጋሪ እንደሚሆን አንድነቶች ገና ከመጀመሪያው እንደተጨነቁ ይታወሳል:: ተድላ ባይሩ ግን፣ በእርጋታና ቀስ በቀስ በመራመድ ወደ ግባችን እንደርሳለን እያሉ፣ ይሰነዝሩት የነበረውን አስተያየት ከደጃዝማችነቱ ሹመት በኋላ ጨርሶ የረሱት ሆነው ይታዩ ጀመር:: ከሕዝቡም ይልቅ ተድላ ባይሩ ራሳቸው ቀስ በቀስ የመሪነቱን ሥልጣን ሲላመዱት፣ ክብርና ወግ እያገኙበትና እየጣማቸው ስለሄዱ፣ የፌዴሬሽኑን ማፍረስ ጉዳይ ከአንድነቶች ጋር መነጋገሩ የማይጥማቸው ነገር ሆኖ ታየ:: አንድነቶችም ምንድነው የሞቀውን ውሃ እንደዚህ በቶሎ ያበረደው ? እያሉ በጥያቄ ሲወጥሯቸው፣ « ...... ሚያዝያ 27 ቀን ስለፌዴሬሽኑ ጉዳይ፣ ለፓርላማው የተገለጸው ንጉሣዊ መልዕክት መከበር ስለአለበት፣ የማፍረሱን ዕቅድ ለማሰብም ሆነ ለማጥናት ጊዜው አይደለም ...... » የሚል መልስ ወረወሩ:: በመሠረቱ ይህ መልስ አንድነቶችን የሚያስቆጣ ወይም የሚያሳዝን ይሆናል ለማለት አያስደፍርም:: ትናንት « የኤርትራን ፌዴሬሽን ማንም አይነካውም » በሚለው የዘውድ ዲስኩር ከታወጀ በኋላ፣ ዛሬ ለማፍረስ እንነጋገርበት ማለት የጨዋ ተግባር አለመሆኑ ትክክል ነው:: በዚህ ጉዳይ ቢትወደድ አስፍሐ ተጠይቀው፣ በሰጡት አስተያየት፣ « ...... በዚያን ጊዜ አንድነቶችም ቢሆኑ፣ የዘውዱን ዲስኩር በማግሥቱ መሻር እንደማይቻል ከማንም የበለጠ እንደሚያውቁ ጥርጥር አልነበረውም:: አንድነቶች የሰጉት፣ ተድላ ባይሩ የደጃዝማችነቱን ካባ ከለበሱ በኋላ፣ በአገር ፍቅር ማህበር ዋና ዋና መሪዎችና፣ በተለይም በእንደራሴው ላይ የሚያሳዩት የትዕቢት መንፈስ፣ አቋማቸውን ለመለወጥ ያዘነበሉ ሆነው ስለታይዋቸው ነው:: ስለዚህ፣ ሰውየውን በመተንኳኰስ ትክክለኛ ሀሳቡን ለማወጣጣት፣ « ፌዴሬሽኑን የምናፈርሰው መቼ ነው ? » በሚል ጥያቄ ማዋከባቸውን ቀጠሉበት:: ሆኖም የቺፍ ኤግዜኩቲፉ ዓላማ ፌዴሬሽኑ ሳይነካ እንዲኖር፣ እሳቸውም « ቀዳማይ መራህ መንግሥቲ » (የኤርትራ ቀዳማዊ መሪ) እየተባሉ እስከ ዕድሜ ልካቸው ለመቆየት መሆኑን ለመረዳት፣ ተድላ በዲስኩር እስኪገልጹት ድረስ መጠበቅ አላስፈለገም:: ከዚህም በቀር አዲስ አበባ፣ ትልቁን ባለሥልጣን ወልደጊዮርጊስን በመማፀን የምፈልገውን ሁሉ አስፈጽማለሁ ብለው ሙሉ ተስፋ ማሳደራቸውን ያልተገነዘበ የለም ..... » ብለዋል::

በንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴና በቺፍ ኤግዜኩቲፉ፣ እንዲሁም በምክትል እንደራሴውና በቺፍ ኤግዜኩቲፉ መካከል እየገቡ፣ ያንዱን ሀሳብ ለአንደኛው በማቀባበል የሚያምታቱና የሚያጋጩ፣ የሶስቱ ምዕራባውያን ኃያላን መንግሥታት ቆንስሎች መሆናቸው ዘግይቶ ተደረሰበት:: በተለይ የእንግሊዝና የፈረንሣይ ወኪሎች፣ የኤርትራን ጉዳይ በጥብቅ ለመከታተልና፣ ለአገሩም ስለሚያስፈልገው እርዳታ ሀሳብ እንድናቀርብ ከየመንግሥታችን ስለተጠየቅን፣ በአስተዳደሩም ሆነ በልማቱም በኩል ያለባችሁን ችግር ገልጣችሁ ንገሩን እያሉ፣ የሚፈተፍቱት ተንኮል የሚያሳዝን ነበር:: ለምሣሌ ያህል የአሠራራቸውን ዘዴ ለመጥቀስ፣ አንዱ ቆንስል የንጉሠ ነገሥቱን እንደራሴ ቀጠሮ ይጠይቅና « ቺፍ ኤግዜኩቲፉን አነጋግሬ፣ ቢትወደድ አንዳርጋቸው በኤርትራ መንግሥት ሥልጣን ውስጥ እየገቡ

በሚፈጥሩብኝ ችግር ምክንያት መሥራት አልቻልኩም » ብሉኛል። የርስዎ አስተያየት ምንድን ነው ? ብሎ ይጠይቃቸዋል። በማግሥቱ ደግሞ ወደ ደጃዝማች ተድላ ቢሮ ይመለስና፣ ቢትወደድ እንደነገሩኝ፣ « ..... ተድላ ባይሩ የመሪነት ችሎታና ቆራጥነት ስለአጠረው ነው እንጂ፣ ሕገ መንግሥቱ የሰጠውን መብት ተከትሎ ለመሥራት ምንም ዓይነት ችግር የለበትም ...... » ተብያለሁ ይላል። ተድላ ግልፍ ይላቸውና፣ እንደራሴውና ምክትላቸው ከተሰጣቸው ኃላፊነት ውጭ በአስተዳደሩ ውስጥ እየገቡ፣ የኤርትራን ፌዴሬሽን ለማፍረስና ሥልጣኑን ለራሳቸው ለማድረግ የሚሠሩትን ሁሉ፣ በዝርዝር ይተነትናሉ። ከዚያ ደግሞ ቆንስሉ ቀጠሮ ይጠይቅና ምክትል እንደራሴው ቢሮ ይሄዳል። « ...... ቺፍ ኤግዜኩቲፉን አነጋግሬው፣ እኔ የአንድነቶች ወይም የፌዴራሊስቶች ወገን በመሆን፣ በንትርክ ጊዜዬን አላባክንም። ሕገ መንግሥቱን ተመርኩዤ የኤርትራን ሕዝብ ለማገልገል ወስኛለሁ ...... » ብሉኛል። ምን ይመስልዎታል ? ብሎ ይጠይቃል። ፊታውራሪ አስፍሐም፣ « ..... ቺፍ ኤግዜኩቲፉ የማንም ወገን አይደለሁም ብሎ ከገለጠልዎ፣ በዴሞክራሲ አሠራራችን ቢፓርላማው ውስጥ በማን ወገን ተደግፎ መንግሥቱን ለመምራት እንደሚችል፣ እሱ ራሱ ቢያስረዳዎ ይሻላል..... » ብለው ያስናብቱታል። እነዚህ በአሉባልታ ዲፕሎማሲ የሰለጠኑ ቆንስሎች፣ በእንደራሴው ጽሕፈት ቤትና በተድላ ባይሩ መንግሥት መካከል እያግቱ የሚቃርሟቸውን ወሬዎች፣ ለየመንግሥታቸው ሲያቀርቡ፣ የኤርትራ ፌዴሬሽን ሕይወት፣ በወር የሚቆጠር እንኳን ዕድሜ የሌለውና፣ ቀብሩም የተዘጋጀለት አድርገው ነበር።

መስከረም 11 ቀን 1953 ዓ.ም (በኢት. መስከረም 1 ቀን 1946 ዓ.ም) ኤርትራ በፌዴራሲዮን ከኢትዮጵያ የተቀላቀለችበት የመጀመሪያው ዓመት፣ አሥመራ ላይ እጅግ ከፍ ባለ የደመቀ ሥነ ሥርዓት እንዲከበር፣ ቢትወደድ አንዳርጋቸውና ፊታውራሪ አስፍሐ ሰፋ ያለ ፕሮግራም ማዘጋጀት ጀመሩ። ደጃዝማች ተድላ ይህንን መሰናዶ ሲሰሙ፣ የመጀመሪያውን ዓመት ትልቁ በዓላችንን ማክበር ያለብን፣ ለዚህ ዕድል ላበቁንና ነፃነታችንን ባስገኙልን በንጉሠ ነገሥታችን ዙፋን ፊት ተሰብስበን ነው ሲሉ፣ በወዳጃቸው በጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ በኩል ለጃንሆይ አመለከቱ።

የቢትወደድን እና የፊታውራሪን ምኞት አሰናክሎ ማበሳጨት ደስታው የደጃዝማች ብቻ ስላልሆነ፤ በጽሕፈት ሚኒስትሩ አማርኛ አምሮና ተቀምሞ የቀረበው የተድላ ባይሩ ማመልከቻ የጃንሆይን መልካም ፈቃድ እንዳገኘ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ወዲያውኑ ወደ አዲስ አበባ ፈተለኩ። በአሥመራ የኤርትራው መንግሥት መሪ በሌለበት እንደታሰበው በዓሉን በዲስኩር ለማድመቅ ስላልተቻለ፣ እንደራሴውና ምክትሉ የወጠኑት ፕሮግራም ባለመሳካቱ በማዘን፤ ለተድላ ብድር መላሽ እንዲያደርጋቸው እየጸለዩ አውደ ዓመቱን ብቻቸውን አሳለፉ።

ደጃዝማች ተድላ ወደ አዲስ አበባ የመጡት፣ በዓሉን ከእንደራሴው ጋር ከማክበር ይልቅ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር የሚያደርጉት የዲስኩር ልውውጥ፣ የተለየ ክብር የሚሰጣቸውና የሚያስደስታቸውም ከመሆኑም በላይ፣ በዚሁ አጋጣሚ ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮችን አስፈጽሞ ለመመለስ ከፍተኛ ተስፋ አድርገው ነው። ይኸውም፣ 1ኛ/ የመጀመሪያውን ዓመት የእናትና ልጆች መገናኘት በዓል ምክንያት በማድረግ፣ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለኤርትራ ሕዝባቸው አንድ ልዩ ችሮታ እንዲያደርጉ፤ 2ኛ/ ቢትወደድ አንዳርጋቸው እና ፊታውራሪ አስፍሐ፣ በሥራቸው ላይ ጣልቃ እየገቡ ከባድ ችግር ስለሚፈጥሩባቸው፣ በጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ

እርዳታ ሁለቱም ባለሥልጣኖች ከአሥመራ እንዲዛወሩ ለማመልከት ነበር። በበዓሉ ዋዜማ ወደ ገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ሄደው ንጉሠ ነገሥቱን እጅ ሲነሱ፣ « ተድላ እንዴት ሰነበትክ ? » ተብለው ፈካ ያለ አስተያየት ከተደረገላቸው በኋላ፣ስለ በዓሉና ስለመጡበት ጉዳይ ዝርዝሩን ለመነጋገር፣ ወደ ጽሕፈት ሚኒስትሩ ቢሮ ሄዱ። የበዓሉ አከባበር፣ በየዓመቱ ሐምሌ 16 ቀን የጃንሆይ ልደት በሚከበርበት ዓይነት በገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ቅጥር ግቢ እንዲፈጸም ስለተወሰነ፤ ዝርዝር ሥነ ሥርዓቶቹ የሚከተሉት ነበሩ።

- ከጠዋቱ በሶስት ሰዓት ጃንሆይና እቴጌ በአገር ባሕል ልብስ፣ ከንጉሣዊ ቤተሰቦቻቸው ጋር ሆነው፣ እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሳችሁ ! ለማለት የሚመጡትን መሣፍንቶችና መኳንንቶች፣ ሚኒስትሮችና የጦር ሹማምንቶች፣ በአረንጓዴ ሳሎን ተቀብለው እጅ ያስነሳሉ። <u>ደጃዝማች ተድላ ባይሩም</u> ከእነዚሁ ታላላቆች መካከል የፕሮቶኮል ሥፍራ ተሰጥቷቸው ይገኛሉ።

- ከሶስት ሰዓት ጀምሮ የመንግሥት ሠራተኞችና ወታደሮች፣ ቤተክህነቶችና ነጋዴዎች፣ መምህራኖችና ተማሪዎች፣ በጠቅላላውም የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ግቢ ይሰበሰባሉ።

- በአራት ሰዓት ተኩል፤ የኤርትራው መሪ ክቡር ደጃዝማች ተድላ ባይሩ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከቆሙበት ስገነት ፊት ለፊት ባለው፣ ሕዝብ በተሰበሰበበት አደባባይ ማህል፣ በተዘጋጀላቸው ልዩ መድረክ ላይ ወጥተው፣ በኤርትራ ሕዝብና በራሳቸው ስም ንግግር ያደርጋሉ።

- ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መልስ ይሰጣሉ።

- በቤተ መንግሥቱ ግቢ የተሰበሰበው ሕዝብ ደስታውን ከገለጸ በኋላ የበዓሉ ፍጻሜ ይሆናል።

ፕሮግራሙ እንደሚያሳየው፣ ዋናው አክተር ተድላ ባይሩ እንዲሆኑ የተሰጣቸው ክብርና ወግ፣ የሚጠብቁትን የመጀመሪያውን ግባቸውን አርክቶላቸዋል። ሁለተኛው ጥያቄ፣ ለኤርትራ ሕዝብ የሚሰጥ « ንጉሣዊ ችሮታ » እያሉ ደጃዝማች ተድላ የሚደጋግሙት ቃል፣ ትክክለኛው ትርጉም ምን እንደሆነ ለመረዳት ጸሐፊ ትዕዛዝ ተቸግረው ነበር። በመጨረሻው የቺፍ ኤግዜኩቲቭ ሀሳብ፣ የኤርትራ መንግሥት በበጀት እጥረት ምክንያት ብዙ ችግር ስለገጠመውና፣ በአንዳንድ ቦታም ለሠራተኞች ደሞዝ ለመክፈል ስለሚያቅተው፣ የገንዘብ እርዳታ እንዲደረግ መሆኑን፣ የጽሕፈትና የፍርድ ሚኒስትሩ ሲረዱት፣ በቀጥታ የገንዘብ ሚኒስትሩን አቶ መኩንን ሀብተወልድን አማከሩ።

« ...... የዛሬ ዓመት እንግሊዞች የኤርትራን አስተዳደር ለነ ደጃች ተድላ ሲያስረክቡ፣ እንድንከፍላቸው ካስገደዱን ወደ ስባት ሚሊዮን ከሚጠጋው ሂሣብ ጋር ሲደመር፣ በዚሁ ዓመት ውስጥ ጃንሆይ ለኤርትራ ሕዝባቸው የሰጡት ችሮታ <u>ወደ አሥራ ሁለት ሚሊዮን ብር</u> ይደርሳል። ይህ ወጪ ከኢትዮጵያ አቅም በላይ ነው። <u>እስከ ዛሬ ድረስ፣ አሥራ ሁለቱ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች በአንድነት ሆነው፣ በአንድ ጊዜ አሥራ ሁለት ሚሊዮን ብር የማግኘት ዕድል አጋጥሟቸው አያውቁም።</u> ይህንን የምጠቅሰው ጃንሆይ ለኤርትራ ሕዝባቸው ያደረጉት እርዳት

አይገባም ብዬ ለማዘን ሳይሆን፣ <u>በጣም ብዙ መሆኑን ለማስረዳት ነው::</u> ..... ከሚቀጥሉት ሶስት ወራቶች በኋላ፤ ጃንሆይ ኤርትራ ሄደው እንደሚሰነብቱ ታውቋል:: በየአውራጃውና በየወረዳው እየተዘዋወሩ ሲጉበኙ፣ ለሕዝቡ አንድ ነገር ካላደረግኩለት ማለታቸው የማይቀር ነው:: በዚህ ጊዜ ምን ያህል ወጪ እንደሚጠብቀን ስለማናውቅ፣ ከአሁኑ ለድንገተኛ ወጭ የሚሆነውን ማሰብ አለብን:: ስለዚህ በአሁኑ ሰዓት የገንዘብ ችሮታ ለማድረግ የገንዘብ ሚኒስቴር ቋቱ ስለአጠረው፣ ደጃች ተድላ በዓሉን በደህና አኳኋን አክብሮ ወደ ሥራው ቢመለስ ይሻላል ...... » በማለት አቶ መኰንን ሀብተወልድ የተጠየቀው የማይቻል መሆኑን አስታወቁ::

ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ካቶ መኰንን ሀብተወልድ አስተያየት ጋር የሚተባበሩ ቢሆንም፣ በአንድ በኩል ተድላ ባዶ እጁን አሥመራ ሲመለስ፣ የቢትወደድ አንዳርጌን ግልምጫ፣ በተለይም የነ እስፍሐን አሽሙር፣ መመከት አይችልም፤ ብለው ተጨነቁ:: የገንዘብ ሚኒስትሩ የማይቸገርበት፣ ዛሬውኑ የገንዘብ ክፍያ የማይጠይቅ ችሮታ ለመወሰን ሲያሰላስሉ፤ የመላ ኢትዮጵያ የትምህርት ሚኒስትሩ ጃንሆይ በመሆናቸው፣ ለበዓሉ መታሰቢያ እንዲሆን ለኤርትራ ሕዝባቸው አንድ ከፍተኛ የተግባረዕድ ወይም የእርሻ ትምህርት ቤት እንዲቋቋም ችሮታ ቢያደርጉ፣ የተሻለ መስሎ ታያቸው:: ወዲያውም አቶ መኰንን ሀብተወልድን ምን ይመስልሀል ? ብለው ጠየቁ:: የገንዘብ ሚኒስትሩ ሀሳቡ በጣም ጥሩ መሆኑን ከገለጹ በኋላ፣ 1ኛ/ ደጃች ተድላ የሚቋቋመውን የተማሪ ቤት ዓይነት እንዲመርጥ ክብሩ እንዲሰጠው፣ 2ኛ/ የተመረጠው ተማሪ ቤት (የርሻ ሆነ የቴክኒክ) በንጉሠ ነገሥቱ ቸርነት እንዲቋቋም፤ <u>በኤርትራ ሕዝብ ስም ሆኖ ልመናውን በዲስኩሩ ውስጥ እንዲያቀርብና፣</u> ጃንሆይም በይፋ በሚሰጡት መልስ <u>በደስታ መፍቀዳቸውን እንዲገልጹለት ቢደረግ ይሻላል አሉ::</u> በዚህ ካቶ መኰንን ሀብተወልድ በቀረበው ሀሳብ፣ ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስ ተስማምተው ወዲያውኑ ለንጉሠ ነገሥቱ አቅርበው አስፈቀዱ::

መስከረም 11 ቀን 1953 ዓ.ም ( በኢት. አቆ. መስከረም 1 ቀን 1946 ዓ.ም ) በጎተ ልዑል ቤተመንግሥት ግቢ ውስጥ፣ ሥፍር ቁጥር የሌለው ሕዝብ በተሰበሰበበት የተካሄደው ሥነ ሥርዓት፤ በየዓመቱ የሚከበረውን የሐምሌ 16 የንጉሠ ነገሥቱን ልደት በዓል የሚያስታውስ ሆኖ ይታያል:: በየዓመቱ ሐምሌ 16 ቀን፣ በዚያን ዘመን የታወቁት የአዲስ አበባ ከተማ ገዥ ፊታውራሪ ደምሴ ወልደአማኑኤል፤ (ኋላ ደጃዝማች) በሞርኒግ ልብስ በሕዝብ ማህል በተዘጋጀ መድረክ ላይ ወጥተው፣ ለኢትዮጵያ ብርሃን እንደሚያቀርቡት መልካም ምኞት፤ ደጃዝማች ተድላም በጥበብ ኩታ አደግድገው፣ የኤርትራ ሕዝብ ለንጉሠ ነገሥቱ ያለውን ባለውለተኛነት የገለጹት ተመሳሳይ በሆነ ሥነ ሥርዓት ነበር::

ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌይቱ ከንጉሣውያን ቤተሰቦቻቸው ጋር ሆነው፣ በቤተመንግሥቱ ሰገነት ላይ ብቅ ሲሉ፣ ያ በወልደጊዮርጊስ ተጸንሶ በመኰንን ሀብተወልድ የተቀናበረውን ሀሳብ፣ የኤርትራው መሪ በዲስኩራቸው ያቀረቡት እንደሚከተለው ነበር::

« ..... ግርማዊነትዎ እንደሚያውቀው፣ የኤርትራ ሕዝብዎ በመከራው ዘመን የጠፉ ንብረቱን ለማቋቋም በመታገል ላይ ነው:: ነገር ግን ለእርሻ የሚሆነው ለም መሬት እጅግ ያነሰ ስለሆነ፣ በድካሙ መጠን የሚያገኘው ፍሬ፤ ከችግሩ የሚያድነው አልሆነም:: <u>ግርማዊነትዎ ይህን ተመልክቶ በተለመደ ቸርነቱ፣ እዚያው አገሩ ላይ አንድ የእርሻ ትምህርት ቤት ተከፍቶለት፣ በዘመናዊ የእርሻ</u>

<u>ጥበብ ዘዴ የመሬቱን ጠባይ ለማሻሻል የሚፈቅድለትን ትምህርት እንዲያገኝ በታላቅ ትህትና እለምናለሁ</u> ...... » በሚል ቃል ዝቅ ብለው እጅ ነሱ:: ወዲያው ንጉሠ ነገሥቱም በሰጡት መልስ « .... <u>በኤርትራውያን ዜጐቻችን ስም ሆነህ እንድናቆምላቸው የለመንከውን የርሻ ትምህርት ቤት በታላቅ ደስታ ፈቅደንልሃል</u>.... » አሉ::

በዚህ የንጉሠ ነገሥቱ የችሮታ ቃል በዓሉ ሲፈጸም፣ ትችቱ በያለበት መቀጣጠል ጀመረ:: አንዳንዶቹ ለመላው ኢትዮጵያ ያሉት የርሻ ትምህርት ቤቶች ሁለት ብቻ ሲሆኑ (አምቦ እና ጅማ) በምን ምክንያት ለአሥመራ ቅድሚያ ተሰጠ ? በማለት ሲያጉረመርሙ፤ ሌሎች ደግሞ ጃንሆይ በአደባባይ ልመና ሲቀርብላቸው፣ እምቢ ማለት አይችሉም እያሉ ይከራከሩ ነበር:: ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ የመኰንን ሀብተወልድ ሥጋት በአንድ በኩል ሕዝቡ ምን ይላል ? ብሎ በማሰብ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ « ...... <u>እናት ከብዙ ዘመን መለያየት በኋላ ልጇን ስትቀበል፣ ያላትን ሁሉ አራቁታ አንተ ትብስ በማለት ለማስደሰት ብትሞክርም፣ ከአቅሟ በላይ በየቀኑ ምን ሳድርግለት ? እያለች መጨነቅና መጠበብ የለባትም</u> ..... » የሚል ነበር::

እንደሚታወሰው የቺፍ ኤግዜኩቲፉ ሁለተኛው ምኞት፣ በኤርትራ ያሉት የግርማዊነታቸው እንደራሴና ምክትላቸው እንዲነሱላቸው፤ ሁለቱንም በአንድነት ማንሳት ካልተቻለ ደግሞ፣ <u>ዋና ቀንደኛ አድርገው የሚቆጥሯቸው ፊታውራሪ አስፍሐ ወደ አዲስ አበባ እንዲዛወሩላቸው ነበር::</u> ሀሳቡን ጸሐፊ ትዕዛዝ ቢደግፉትም በእሳቸው በኩል የልዕልት ተናኘወርቅን ባለቤት ከሥልጣን ይነሱ ብሎ ለጃንሆይ ማቅረቡ ስለሚያስቸግራቸው፣ ቢትወደድና ፊታውራሪ አላሠሩኝም በማለት ተድላ ባይሩ በቀጥታ ለአባ ጠቅል እንዲያመለክቱ አደፋፈሯቸው:: ደጃዝማችም ሲፈሩ ሲቸሩ፣ ስም ለመጥቀስም ሳይደፍሩ፣ በደፈናው <u>የእንደራሴው ቢሮ እኔን በማገዝ ፋንታ እኔ እንድጉዳ ይሠራል፣</u> የሚል ለከስከስ ያለ አቤቱታ አቀረቡ:: ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በእንደራሲያቸውና በቺፍ ኤግዜኩቲፉ መካከል፣ እንዲሁም ከአስፍሐ ጋር ያለው አለመግባባትና መቃቃር በምን ምክንያት እንደሆነ ደህና አድርገው ያውቁታል:: በመሠረቱ በጃንሆይ የአመራር ጥበብ፣ ሁለቱም ወገኖች እንዲተባበሩና እንዲወዳጁ አይፈለግም:: አንዳንድ ጊዜም ውስጥ ውስጡን የሚያጫጭኗቸው እራሳቸው ባለቤቱ ስለሆኑ፣ በፍርዳቸው የነ አንዳርጌ ወይም የተድላ ደጋፊ ሆነው አይታዩም:: የደጃዝማቹም አቤቱታ በሌላ አነጋገር፣ እንዳርጌና አስፍሐ ይሻሩልኝ እንደሆነ በትክክል ገብቷቸዋል:: ስለዚህ ለቀረበላቸው አቤቱታ፣ « <u>.... እኛ እያለን ሥራህ አይበላሽም:: ባለጋራም አያጠቃህም::</u> የእንደራሴያችን ጉዳይና ያንተም ኃላፊነት እየታየ፣ ወደፊት እንደሚሆን እናደርገዋለን .... » በሚል ትክክለኛ ትርጉሙ አስቸጋሪ በሆነ ቃል፣ የኤርትራውን መሪ ጫማ አስመው አሰናበቷቸው:: የዚህን አነጋገር ምሥጢሩን ለመረዳት፣ ለደጃዝማች አማርኛ እጅግ የሚጠጥር ቢሆንም፣ « ...... እኛ እያለን ሥራህ አይበላሽም፣ ባለጋራም አያጠቃህም ...... » ብለው፣ ንጉሠ ነገሥቱ የተናገሩት፣ የተድላን ሞራል ከፍ እንዳደረገው ይነገራል:: ይሁን እንጂ፣ ተድላን ያስደሰታቸው ምኑ እንደሆነ ሊታወቅ አልቻለም:: በኤርትራ ሕገ መንግሥት መሠረት የተድላ ኃላፊነት ቢታይ፣ ፓርላማው ቺፍ ኤግዜኩቲፉን ለመደገፍ ወይም ለመሻር በሚወስደው እርምጃ የጃንሆይ ሥልጣን አይገባበትም:: ስለዚህ እኛ እያለን .... ባለጋራ አያጠቃህም ..... የተባለው፣ ምናልባት የአንድነት አጥባቂ ወገኖችን ለማስታገስ ስለሚችሉ ነው ተብሎ ካልታሰበ በስተቀር፣ ተድላ ባይሩን ከሌሎች ባለጋራዎች ጥቃት፣ ንጉሠ ነገሥቱ የሚያድኑበት ሥልጣን እንደሌላቸው ግልጽ

ነው:: በመጨረሻው ..... <u>የእንደራሴያችን ጉዳይና ያንተም ኃላፊነት ..... እንደማሆን እናደርገዋለን</u> ብለው የተናገሩት ምን ለማለት እንደሆነ፣ እንኳንስ ተድላ ባይሩ፣ የገነተ ልዑል አካባቢ ሰዎችም ቢሆኑ ሊገባቸው አይችልም:: የጽሕፈት ሚኒስቴር ሰዎች እንደተረጎሙት፣ « <u>ያቀረብከው ወደፊት ታይቶ ይወሰናል</u> » ለማለት ብቻ የተነገረ ቃል ነው ብለዋል:: ለማናቸውም ደጃዝማች እንደተመኙት ቢትወደድ አንዳርጌንና ፊታውራሪ አሰፍሐን ለማሻር አልሆነላቸውም::

የዘመን መለወጫና የኤርትራ መቀላቀል በዓል የዋለው አርብ ቀን ስለሆነ፣ በዚያን ዕለት ንጉሠ ነገሥቱ ግብር አልሰጡም:: ደጃዝማች ተድላ ከበዓሉ ፍጻሜ በኋላ ወደ ማረፊያቸው ወደ ራስ ሆቴል ሲመለሱ፣ ከቤተመንግሥቱ የተላከላቸው መስተንግዶ በሚያምር መልክ ተዘጋጅቶ ጠበቃቸው:: ደጃዝማች በወትሮአቸው፣ የአርብንና የረቡዕን ጉዳይ ባይከታተሉም፣ ከተሰናዱላቸው የጾም ምግቦች ውስጥ፣ የሽንብራው አሣ ወጥ፣ ስልጆውና የሱፍ ውሃ ፍትፍቱ በጣም እንደተስማማቸው አቅራቢዎቹ ያስታውሳሉ:: በዚሁ ዕለት ከእኩለ ቀን በኋላ ጀምሮ እስከ ማግሥቱ ምሣ ስዓት ድረስ፣ ደጃዝማች ፕሮግራማቸውን የመደቡት፣ አዲስ አበባ የሚኖሩትን ኤርትራውያን ታላላቅ ሰዎች እየተቀበሉ ስለ ኤርትራ ፌዴሬሽንና ስለ አንድነት ጉዳይ የሚሰጣቸውን ምክር በማዳመጥ ነበር::

በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ከፍተኛ ሥልጣን ላይ የሚገኙት ኤርትራውያኖች፣ በጣም አብዛኛዎቹ (ወይም ዘጠና በመቶው) የፌዴሬሽኑ አስተዳደር እንዲቀጥል የሚያተጉ ናቸው:: በእነሱ አስተያየት፣ ኤርትራ የኦቶኖሚ መብት በማግኘቷ፣ ኢትዮጵያዊነቷን አይቀንስም:: ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ በፌዴራል ሲስተም የሚተዳደር ነው:: ሕዝቡ ግን አሜሪካዊ ነው:: ለኤርትራ የተሰጠው ሕገ መንግሥት በትክክል እንዲሠራ ከተደረገ፣ ጥቅሙ ላገሩ ተወላጅ ብቻ ሳይሆን፣ ለሌላውም በአሥራ ሁለት ጠቅላይ ግዛቶች ተደልድሎ ለሚተዳደረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥሩ ምሣሌ የሚሆን ነው:: የኤርትራ ሕዝብ ሳያስበውና ሳይጠይቅ፣ በተባበሩት መንግሥታት ተዘጋጅቶ የተሰጠው የፌዴሬሽን አስተዳደር መብት፣ በተዓምር የመጣለት ዕድል ስለሆነ፣ እንዲጠነክርና ፍሬውን እንዲያሳይ መጣር ያስፈልጋል:: አሰበለዚያ ፌዴሬሽኑ ቢፈርስና ፍጹም መዋሀድ ቢደረግ፣ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደደረሰበት ሁሉ፣ ኤርትራውያኖችም በአዲስ አበባ የአገር ግዛት ሚኒስቴር የጭለማ አስተዳደር ውስጥ፣ ተጨፍልቀው እንደሚሰቃዩ ማሰብ ያስፈልጋል:: ስለዚህ፣

1ኛ/ የፌዴሬሽኑ አስተዳደር ኢትዮጵያዊነትን የሚጠብቅ እንጂ የሚያዳክም አለመሆኑን፤

2ኛ/ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን የንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣን በምንም ረገድ እንደማይቀንሰው፤ ደህና አድርጉ በማስረዳት፣

የፌዴሬሽኑ ሕይወት እንዲቀጥል ከመታገል በስተቀር፣ ለቺፍ ኤግዜኩቲፉ ሌላ ምርጫ እንደማይኖራቸው፤ የአዲስ አበባዎቹ ኤርትራውያኖች የጠበቀ ምክራቸውን ሰጧቸው::

ከጥቂት ወራቶች ጀምሮ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ የፌዴራሊስትነትን ሸሚዝ በይፋ ለማጥለቅ ዳርዳሩን ይሞካክሩ ስለነበረ፣ በዚህ በአዲስ አበባው ጉዞአቸው

ከወገኖቻቸው ያገኙት ምክርና አስተያየት፣ ሀሳባቸውን በበለጠ ሊያጠናክርላቸው ቻለ:: ከንጉሠ ነገሥቱና ከጸሐፌ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ጋር ለረዥም ሰዓቶች ሲነጋገሩ፤ አንድም ጊዜ ፌዴሬሽን ስለማፍረስ ሆነ ስለማላላት ጥያቄ አለመነሣቱ፣ አዲሱ ፌዴራሊስት የሆነውን ዕቅዴን ከግቡ ለማድረስ ችግር አይገጥመኝም ብለው አመኑ::

በጣም ያስቸግሩኛል የሚሏቸው ቢትወደድ አንዳርጋቸውና ፊታውራሪ አስፍሐ፣ እንዲሻሩላቸው የተመኙት ባይፈጸምላቸውም፤ ከጃንሆይና ከወልደጊዮርጊስ የተሰጣቸው ክብርና መልካም አስተያየት እጅግ አድርጉ አስደስቷቸዋል:: በዚህ አኳኋን ተድላ ባይሩ የአዲስ አበባ ጉብኝታቸውን ፈጽመው አሥመራ የተመለሱት፣ የኤርትራ ፌዴሬሽን እንዲጠነክርና፣ ለመቼውም እንዲቆይ ለማድረግ ስለሆነ፣ የአንድነት አጥባቂ ወገኖቻቸውን ችላ ማለት የመጀመሪያው እርምጃቸው ሆነ::

## ያዝልቅልዎ !

እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በዘመነ ማርቆስ 1946 ዓ.ም (በአውሮፓ 1953-1954) ደጃዝማች ተድላ ባይሩ የኤርትራን ፌዴሬሽን አጠንክሮ ለማቆየት የወሰኑት፣ አንዳችም የፖሊሲ መግለጫ ሳያደርጉ፣ በአሠራር ዘዴ ብቻ በመጠቀም እንዲሆን ነበር:: ከዚህም ግብ ለመድረስ፣

1ኛ/ ከአንድነት አጥባቂ ወገኖች ጋር፣ ፌዴሬሽኑ ይፍረስ ወይም አይፍረስ የሚል ንትርክ ሳይከፈት፤

2ኛ/ የፌዴሬሽኑ አስተዳደር ስለሚሰጠው ጥቅም፣ የቺፍ ኤግዜኩቲፉ አስተያየት በዲስኩርም ሆነ በጋዜጣ ሳይገለጥ እንዲከናወን፤ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረባቸው::

ደጃዝማች እንደተመከሩት፤ ድምፃቸውን ፀጥ አድርገው ለአቀዱት ዓላማ በሚጥሩበት ጊዜ፣ ከአንድነቶች በኩል እንዳችም እንቅፋት እንዳይደነቀርባቸው፣ « ..... ለኤርትራ እናቷ ኢትዮጵያ ነች:: ..... መሪዋም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ናቸው:: ...... » እያሉ በየዲስኩራቸውና በየመግለጫቸው ጉላ አድርጉ ለማቅረብ ፕሮግራም አቀዱ:: በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ውስጥ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ የሚገኙት የአዲስ አበባዎቹ ኤርትራውያኖች፣ በትምህርትም ሆነ በሥራ ኤክስፔሪያንስ እጅግ የላቁና የታወቁ በመሆናቸው፣ ከእነሱ የተሰጠው የፖለቲካ ቴክኒክ ፍቱን መድኃኒት ነው ብለው ከልብ አመኑበት:: ይሁን እንጂ አሥመራም ያሉት የማህበረ ፍቅረ ሀገር አባሎችና፣ በተለይም የአንድነት አጥባቂ ወገኖች በቀላሉ የሚበገሩ አለመሆናቸውን፣ ደጃዝማች አልተረዱትም:: ከአዲስ አበባ ጠቅላላ የመንፈስ እደሳ ተደርጉላቸው፣ አሥመራ በተመለሱ በሁለተኛው ሳምንት መጀመሪያ ላይ፤ ከአንድነት አጥባቂ ወገኖች ለቺፍ ኤግዜኩቲፉ በተጻፈላቸው ልዩ ማስታወሻ የሚከተለው አስተያየት ቀረበላቸው::

« ...... ከሉኒያሊስት ጣልያን ከኢትዮጵያ የነጠላት አገራችን ኤርትራ፤ ተመልሳ ከእናቷ ጋር እንድትዋሀድ ከእኛ ጋር ሆነው፣ ከአሥር ዓመታት በላይ ያደረጉትን ከፍተኛ ተጋድሎ ለመመስከር እኛ ወንድሞችዎ ወደ ኋላ አንልም::